

“ኢትዮጵያን” ከአዲስ አበባ ውጭ ፈልጌ አጣኋት!

መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

ኢትዮጵያዊው “የአሜሪካ የምርጫ ዘመቻ መሀንዲስ”

ብሩክ መኮንን

“አዲሱ ኢህአዴግ እኔን ማጥቃትና ሥራዎቼን ማሰናከልን ተልዕኮው አድርጓል”



(ኤርሚያስ አመልጋ ከቂሊንጦ  እስር ቤት)

ለግዮን መፅሔት


መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 69 ነሐሴ 2011 ዓ.ም

ዋጋ 14.99


“ስለ ሴቶች ብለን የጀመርነው ስራ ካሰብነው በላይ አስደንጋጭ ነገር ያየንበት ነው”

ወ/ሮ መቅደስ ዘለለው

የተቀናጀ የቤተሰብ አገልግሎት ድርጅት መስራችና ዳይሬክተር

# “ምርጫ ቦርድ ማነው?!”

## አዲሱ አዋጅ፣ ምርጫ ቦርድ እና የፓርቲዎቹ ውዝግብ





“የፀረ ሽብር ሕጉ የክስ መሠረት መሆኑ ፈፅሞ አግባብ አይደለም”

ዶ/ር ዳንኤል በቀለ

(የኢትዮጵያ ሰብኣዊ መብት ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር)



“ጥራት ያለው ትምህርት፤ ለታላቅ ስኬት”

አቶ ሞገስ ግርማ

/የኮሌጁ ማኔጂንግ ዳይሬክተር/

“በሰማይ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ በምድር ዛይ ራይድ አፍሪካን ይቆጣጠራሉ”



አቶ ሐብታሙ ታደሰ /የዛይ ራይድ መሥራችና ዋና ሥራ  አስኪያጅ/

**የአርታኢያን ማኅበር መመስረት አነጋጋሪ ጉዳዮችን እያስነሳ ነው**

**2**

**“ቱባ ባህሎች” ለፖለቲካ ጥቅም መዋላቸው ወቀሳ ቀረበበት!**

**3**

**የኢሕአዴግ ዕርቅ ከራሱ? ወይስ ከፖለቲካ ፓርቲዎች እና ከሕዝብ?**

**4**

**“ምርጫ ቦርድ ማነው?!”**

**አዲሱ አዋጅ፣ ምርጫ ቦርድ እና የፓርቲዎቹ ውዝግብ**

*መሳክ ቢ.*

**5**

**የውጭ ግንኙነታችን ጥቅምና ጉዳትን ማስላት ካልቻለ አደጋው ከባድ ነው!**

*አስማየሁ ባዘዘው*

**8**

**“ጥራት ያለው ትምህርት፤ ለታላቅ ስኬት”**

*አቶ ሞገስ ግርማ*

**9**

**ማገጣበር - አገር አቀፍ ችግር**

**“ስንት አስጫርህ?”**

*በአያሌው አስረስ*

**10**

**ሰሞነኛው የሱዳን አክራሞት**

*ኄኖክ ገስታው*

**11**

**“ኢትዮጵያን” ከአዲስ አበባ ውጭ ፈልጌ አጣኋት!**

*መታሰቢያ መልአከ ሕይወት*

**12**

**ቅምሻ -አንደበት**

**13**

**“የፀረ ሽብር ሕጉ የክስ መሠረት መሆኑ ፈፅሞ አግባብ አይደለም”**

*ዶ/ር ዳንኤል በቀለ*

**14**

**የአገር አንድነት አደጋ ላይ በወደቀበት ወቅት**

**“የተደበቀው ማስታወሻ”**

*ጌታቸው ስሜ (ኢንግላንድ)*

**17**

**ጉስታቭካርል ጉስታቭ ቮን ሮሰን**

**ሲውድናዊው የኢትዮጵያ አየር ኃይል መስራች!**

*ብሩክ መኮንን*

**19**

**የ25 ዓመት ጉዞ**

**“ስለ ሴቶች ብለን የጀመርነው ስራ ካሰብነው በላይ አስደንጋጭ ነገር ያየንበት ነው”**

*ወ/ሮ መቅደስ ዘለለው*

*የተቀናጀ የቤተሰብ አገልግሎት ድርጅት መስራችና ዳይሬክተር)*





**21**




ቁጥር 68 ዕትም

**ግዮን**

**ቀጣይ ዕትም ቅዳሜ ነሐሴ 25 ይጠብቁን!**


**አዲሱ ደምሴ**

**ኢትዮጵያዊው “የአሜሪካ የምርጫ ዘመቻ መሀንዲስ”**

*ብሩክ መኮንን*

**24**

**“አዲሱ ኢህአዴግ እኔን ማጥቃትና ሥራዎቼን ማሰናከልን ተልዕኮው አድርጓል”**

*(ኤርሚያስ አመልጋ ከቂሊንጦ እስር ቤት)*

**25**

**ሳውዲ አረቢያ የፋትቦል ጦርነት ጀምራለች**

ፍቅሩ ኪዳኔ

**26**

**“በሰማይ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ በምድር ዛይ ራይድ አፍሪካን ይቆጣጠራሉ”**

*አቶ ሐብታሙ ታደሰ*

**27**

**ታላቁ አፍሪካዊ የስፖርት ሰው ይድነቃቸው ተሰማ**

*ጴጥሮስ አሸናፊ*

**28**

# የአርታኢያን ማኅበር መመስረት አነጋጋሪ ጉዳዮችን እያስነሳ ነው

በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ባለሙያዎች "የአርታኢያን ማኅበር" በሚል አዲስ የሙያ ማህበር ማቋቋማቸውን በይፋ ያሳወቁ ሲሆን፣ የዚህን ማኅበር መመስረት ተከትሎ በርካታ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች አነጋጋሪ ነጥቦችንና ምላሽ የሚሹ ጥያቄዎችን እያነሱ መሆኑ ታውቋል።

በአዲስ አበባ ጎልደን ሮያል ሆቴል ነሐሴ 13 ቀን 2011 ዓ.ም በተጠራ ጉባዔ መመስረቱ ይፋ የሆነው የአርታኢያን ማኅበር አባላቱንና ጋዜጠኞችን ከሚደርስባቸው ማንኛውም ጫና እና ጥቃት የመከላከል፣ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ የመረጃ ነፃነትና የመደራጀት መብት እንዲከበር የማድረግ፣ ሙያዊ ብቃትን ለማሳደግ በተደራጀ መልኩ መስራት የሚሉ አላማዎች ያሉት መሆኑና አባላቱም ከህትመት፣ ብሮድካስትና የኢንተርኔት መገናኛ ብዙሃን ተቋማት የተውጣጡ እንደሆኑ ተመልክቷል።

ይሁንና ከዚህ የአርታኢያን ማኅበር መመስረት በኋላ በበርካታ የግልና የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን ውስጥ የሚሰሩ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች በማኅበሩ ምስረታ ሂደት ላይ ከወዲሁ ጥያቄዎችን በማንሳት ላይ እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል።

እየተነሱ ከሚገኙ ጥያቄዎች መካከል "ማኅበሩ የተመሰረተው ሁሉንም የመገናኛ ብዙሃት ተቋማትና ባለሙያዎች ባሳተፈ መልኩ ነው?" የሚለው በቀዳሚነት የሚጠቀስ ሲሆን፣ መስራች ጉባዔውን የጠሩትና ማኅበሩን በቀጣይነት ለመምራት የተመረጡት፣ "ቀደም ሲል የጠበቀ የርስ በርስ ግንኙነት በነበራቸው ሰዎች በመሆኑ፤ ይህ ማኅበር ብዙሃኑን የዘርፉ ባለሙያ መወከል አይችልም" የሚል ትችትና ተቃውሞ እየቀረበበት ይገኛል።

"የጋዜጠኞች ሙያ ማኅበራት በመንግሥት ተፅዕኖ እንዲፈርሱና እንዲዳከሙ፣ የማኅበራቱ አመራሮችም ከሀገር እስከመሰደድ የሚያደርስ ብርቱ ጫና እንዲደርስባቸው ሲደረግ በቆየበትና ምንም ዓይነት ተቆርቋሪና ተሚጋች ነፃ የጋዜጠኛ ማህበር በሌለበት ሀገር የሚተዋወቁ ሰዎች፣ ድንገት ተጠራርተው በጋዜጠኛው ስም ማኅበር መሰረትን ማለታቸው ታሪካዊ ስህተት ነው" በማለት አስተያየት የሰጠ አንጋፋ ጋዜጠኛ "በተለይም የአርታኢያኑ ማኅበር የአንድ ቤተሰብ አባል የሆኑ ወንድማማቾችን በሥራ አስፈፃሚነት መምረጡ ከሙያ ማኅበር ይልቅ የቤተሰብ ጉባዔ መልክ እንዲኖረው አድርጎታል" ብሏል።

"የዴሞክራሲና የፍትሕ ጥያቄን አንግበው ስለዜጎች መብትና ነፃነት ለዓመታት የዘለቀ የብዕር ሙያዊ ተጋድሎ ሲያደርጉ የቆዩትን፤ በዚህም ለከፋ ስቃይ፣ ዕስር፣ ድብደባ፣ ዛቻ፣ መገለል፣ ሞት እና ስደት የተዳረጉትን የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞችን ገሸሽ ባደረገ መልኩ የተቋቋመ መሆኑ የአርታኢያን ማህበሩ ነፃነትና ገለልተኛነት ጥያቄ ላይ ይጥለዋል" ያሉ ሌላ ነባር ጋዜጠኛ በበኩላቸው፤ "ማኅበሩ ለጋዜጠኞች መብትና ጥቅም መከበር የመስራት ዓላማ ይዞ ሳለ፣ ስያሜውን የአርታኢያን ማኅበር ማለቱ ጥቂቶችን ብቻ ተጠቃሚ ለማድረግ ማለሙን በበቂ መልኩ ያሳያል" ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

"የሙያ ማኅበርን ከመመስረት በፊት ለሁሉም በሀገሪቱ ለሚገኙ ጋዜጠኞች ጥሪ ማድረግና በማኅበሩ ደንብና መተዳደሪያ ህጎች ላይ መወያየት መቅደም ነበረበት" በማለት የአርታኢያን ማኅበሩን መመስረት በበጎ ጎኑ እንደማይቀበሉት የገለፁ ሌላኛው አንጋፋ ጋዜጠኛ በበኩላቸው "የአርታኢያን ማኅበሩ፤ በማኅበሩ ደንብና ህጎች ላይ ተወያይቶ ማሻሻያዎችን ከማድረጉ በፊት ምስረታውን ለማብሰር መጣደፉ ከበስተኋላው አንዳች ድብቅ ዓላማ ስለመኖሩ እንድንጠራጠር ያደርጋል" ብለዋል።

በአርታዒያን ማኅበር ምስረታ ጉባዔው ላይ ተገኝተው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ጌታቸው ድንቁ የማኅበሩ መመስረት ያስደሰታቸው መሆኑን ገልጸው፤ መንግሥት በቀጣይነት ማኅበሩን ለማጠናከር ድጋፍ እንደሚያደርግ አስታውቀዋል።

# ኢዮሃ እቁጣጣሽ ኤክስፖ 2012 ብዙዎች እየጎበኙት ነው

350 የአገር ውስጥ አምራቾች እና 98 የውጭ ድርጅቶች የተሳተፉበት "ኢዮሃ እንቁጣጣሽ ኤክስፖ 2012" በኤግዚቢሽን ማዕከል ባለፈው ሣምንት በታላቅ ድምቀት ተከፍቶ እየተጎበኘ ነው። ክብርት ዶክተር ሂሩት ካሳው፣ ከቡር ኢንጅነር እንዳወቅ አብቴ፣ አቶ ታምራት አድማሱ፣ እና አቶ ሲራጅ፤ እንዲሁም የኢዮሃ አዲስ ኢንተርቴይመንት ባለቤት እና ምክትል ሥራ አስኪያጅ በተገኙበት የዘንድሮው "ኢዮሃ እንቁጣጣሽ" 2012 ኤክስፖና ፌስቲቫል በይፋ ሲከፈት፤ የኤግዚቢሽን ማዕከሉ ስራ ከጀመረበት ዘመን ጀምሮ የነበረውን የተለመደ አሰራር በመቀየር፣ ደረጃውን ከፍ በማድረግም፣ ለመጀመሪያ ግዜ የግቢውን ዲዛይን በአዲስ መልክ በመቀየር እና ባለ አንድ ፎቅ ግንባታ በማከናወን ዓለም አቀፍ የባዘርና የፌስቲቫል ስታንዳርድ እንዲይዝ መደረጉን ተመልክተናል። ኢዮሃ እንቁጣጣሽ 2012፣ በቀን ከ10ሺህ በላይ ሰው እየጎበኘው መሆኑ እየተነገረ ነው።

በመዝናኛው ዘርፍ በ4 ባንዶች በመታገዝ ከ40 በላይ ታዋቂ ድምፃዊያን ልዩ የሆነ ኮንሰርታቸውን በየቀኑ የሚያቀርቡ ሲሆን፣ ከወጣት እስከ አንጋፋ ድምፃውያንን ባሳተፈ መልኩ ለ26 ቀናት ተከታታይ ኮንሰርቶች ይከናወናሉ። ለአካል ጉዳተኞች ልዩ የመቀመጫ ቦታ ተዘጋጅቷል፤ የሴባስቶፖል መድፍም ታሪክን ለማስታወስ በመክፈቻው ዕለት ተተኩሷል። ኤክስፖና ፌስቲቫሉን ሄይንከን በልዩ ሁኔታ ምርቶቹ በሆኑት ዋልያ ቢራ፣ በደሌ ቢራ፣ ሀረር ቢራና ሀረር ሶፊ ምርቶች ስፖንሰር አድርጎታል። ፖሎ ትሪፕ፣ አባይ ባንክ፣ ሼፍ ሉካ፣ ጉለሌ 555 ሳሙና፣ ጤና ዘይት፣ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በተለያዩ ደረጃዎች ስፖንሰር ያደረጉት ሲሆን፤ ኢቢኤስ ቲቪ የባዛሩ የሚዲያ አጋር ነው።

# በቶቶት የባህልና የምግብ አዳራሽ አረጋዊያን የፊትል ጋቢ ስጦታ ተበረከተላቸው

የቡሄ በዓልን ምክንያት በማድረግ ሜሪጆይ የበጎ አድራጎት ማህበር ባዘጋጀው እና 200 ሰዎችን ምሣ በጋበዘበት የ25ኛ ዓመት ክብረ በዓል ፤ የቶቶት የባህልና የምግብ አዳራሽ ባለቤት አቶ ጠንከር ለ20 አረጋዊያን የፊትል ጋቢ ሲያለብሱ፣ ለ20 ህፃናት የትምህርት ቁሳቁሶችን አበርክተዋል። በዕለቱ በርካታ አርቲስቶችና ጋዜጠኞችም ተገኝተዋል። የሜሪ ጆይ መስራች ሲስተር ዘቢደር ዘውዴ በዕለቱ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ከማድረግ ባሻገር በማኅበሩ 25 ዓመት ጉዞ ላልተለዩ ሁሉ ምስጋናቸውን አቅርበዋል። አረጋዊያንም ለተደረገላቸው ድጋፍ ምርቃታቸውን አድርሰዋል።

## በአዲሱ የትምህርት ፍኖተ ካርታ፥-

# ዲግሪ የሌላቸው መምህራን እንደማይኖሩ ይፋ ሆነ

ለአመታት በሥራ ላይ ከቆየው የትምህርት ፖሊሲ ጋር በተያያዘ "የትውልድ ክስረት አስከትሏል" በሚል ይቀርብ የነበረውን ትችትና ተቃውሞ መነሻ በማድረግ የትምህርት ሚኒስቴር ለወራት ሲያዘጋጅ የቆየውን አዲስ የትምህርት ፍኖተ ካርታ ይፋ አደረገ።

ነሐሴ 15 ቀን 2011 ዓ.ም ትምህርት ሚኒስቴር በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ይፋ እንደተደረገው በዚህ አዲስ ፍኖተ ካርታ ወጣት ዜጎችን ገና በለጋ እድሜያቸው "ለስራ ፈትነትና ለአጉል ሱስ ተጋላጭ እንዲሆኑ አድርጓል" በሚል ትችት ሲቀርብበት የቆየው የ10ኛ ክፍል ብሔራዊ መልቀቂያ ፈተና ከመጪው ዓመት ጀምሮ እንደሚቀርና መንግሥት የሚያስተዳድራቸው መዋዕለ ሕፃናት በብዛት እንደሚከፈቱ ተመልክቷል።

"የትምህርት ስርዓቱ ከተማሪው ጋር በተጣጣመና ሀገር በቀል ዕውቀቶችን መነሻ ባደረገ መልኩ እንዲሆን ይደረጋል" ያሉት ሚኒስትሩ አቶ ጥላዬ ጌጤ በአዲሱ የትምህርት መዋቅር ከ1ኛ - 6ኛ የአንደኛ ደረጃ ት/ት፣ 7ኛ እና 8ኛ የመለስተኛ ሁለተኛ የደረጃ ት/ት፣ ከ9ኛ - 12ኛ ክፍል ደግሞ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተብለው በሶስት ክፍሎች እንደረዋቀሩ አስታውቀዋል።

ሚኒስትሩ ከዚሁ ጋር አያይዘውም የመምህራንን ብቃት በሚመለከት በአዲሱ ፍኖተ ካርታ ለአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ዲግሪ ያላቸው መምህራን፣ ለሁለተኛ ደረጃ በማስተርስ የተመረቁ፣ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርስቲዎች) ደግሞ ከማስተርስ ዲግሪ በላይ ያላቸው መምህራን የሚመደቡ መሆኑን አመላክተዋል።

# “ቱባ ባህሎች” ለፖለቲካ ጥቅም መዋላቸው ወቀሳ ቀረበበት!



በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተለይም በትግራይና አማራ ክልል በተለያየ መልኩ የሚከበረውን አመታዊ የልጃገረዶች በዓል ለፖለቲካ ጥቅም እንዲውል የማድረግ አዝማሚያ በስፋት መስተዋሉ አግባብ አለመሆኑ ተጠቆመ፡፡

በየዓመቱ ከነሐሴ 16 የፍልሰታ ፆም ፍቺ ጀምሮ እስከ ጳጉሜ ወር መጨረሻ ድረስ በሰሜን ኢትዮጵያ ልጃገረዶች ዘንድ “አሸንዳ፣ አሸንድዬ፣ ሻደይ፣ ሶለል…” በሚሉ ልዩ ልዩ ስያሜዎች የሚከበረውን ህዝባዊ በዓል የአማራ እና የትግራይ የፖለቲካ መሪዎች ለፖለቲካ ጥቅም ማስገኛነት ሊጠቀሙበት ሲራወጡ መታየታቸው ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ቱባ ባህል ከመመረዝና ከማዳከም የዘለለ ትርፍ እንደማይኖረው በበርካታ ምሁራን፣ የሀይማኖት አባቶችና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን አስተያየት እየተሰጠበት ይገኛል፡፡

የትግራይ ክልል መስተዳድር ከአስር ዓመታት በፊት ጀምሮ በዓሉን ለማስተዋወቅና የክልሉ ዋነኛ የቱሪዝም ሀብት እንዲሆን ለማድረግ በቀዳሚነት ሰፊ ስራ ሲሰራ መቆየቱንና ይህ የተጠናከረ ዘመቻው አሁን ላይ ፍሬ አፍርቶ መታየት መቻሉ በስፋት እየተነገረ ሲሆን፣ የባህሉ ተጋሪ የሆነው የአማራ ክልል መስተዳድር ዘግይቶም ቢሆን ይህን የልጃገረዶች ባህል ለማስተዋወቅና ተደራሽነቱን ለማስፋት ሰፊ ዘመቻ መጀመሩ ተመልክቷል፡፡

እንደ አስተያየት ሰጪዎች ከሆነ ግን በሁለቱ ክልሎች የፖለቲካ መሪዎች መካከል ባህሉን “የእኔ ብቻ” በሚል እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ ከአጠቃላይ የሀገራችን ተጠቃሚነት አንፃር ያልተቃኘና ግለኝነትን ያስቀደመ በመሆኑ ከሀገራዊ ጥቅሙ ይልቅ ባህሉን የመጉዳት አዝማሚያው ከፍተኛ እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡

“ከአመት በፊት በነበረው የፖለቲካ ተፅዕኖ የአሸንዳ በዓልን የትግራይ ብቻ የማድረግ ብርቱ ዘመቻ ነበር፡፡ በዓሉን ከክልሉ አልፎ በአዲስ አበባም የሚታወቅና በስፋት የሚከናወን ለማድረግ ተሞክሮ ነበር፡፡ ይህ በራሱ ጥፋት ባይሆንም የሌሎቹን ብሔሮች ባህል ባከበረና ባልተጫነ መልኩ አለመሆኑ ግን አሁን ለተፈጠረው ችግር ምክንያት የሆነ ይመስለኛል” በማለት የተናገሩ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ምሁር “በዓሉ አሸንዳም ተባለ አሸንድዬ፣ ሻደይም ተባለ ሶለል ሁሉም ተመሳሳይነት ያላቸው የኢትዮጵያ ልጃገረዶች ባህል በመሆኑ የሁለቱ ክልሎች የፖለቲካ ልሂቃን በዚህ ላይ የጋራ መግባባት ፈጥረው ይህን የዜጎች ቱባ ባህል ማበልፀግ ላይ ቢሰሩ ጥቅሙ ለሁላችንም ይሆን ነበር” ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

“የአማራ ክልል የፖለቲካ መሪዎች በአመት አንድ ጊዜ ብቻ ሴት ልጃገረዶች በአደባባይ ሲቦርቁ የሚታዩበትን ጥንታዊ ባህል ከትግራይ አስተዳዳሪዎች ጋር ለገቡበት እሰጥ አገባና ጡንቻ መለካካት ለማዋል መሞከሩ የጥንታዊውን ባህል መልክና መንፈስ የመበረዝ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል” ሲሉ ሀሳባቸውን የሰነዘሩት ደግሞ የታሪክ ምሁሩ ዶ/ር ከተማ አሸናፊ ሲሆኑ፣ ከዚሁ ጋር አያይዘውም “ክልሎቹ ይህን ባህል በዩኔስኮ የማይዳሰሱ የአለም ቅርሶች ዝርዝር ለማስመዝገብ በየፊናቸው መንቀሳቀሳቸው ለእነርሱም ሆነ ለአጠቃላይ ሀገራችን ጉዳት እንጂ ጥቅም አያመጣም፡፡ ዩኔስኮ እንደ ሀገር እንጂ እንደ ክልል ለሚቀርብ ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ የመስጠት አሰራር ስለሌለው የተናጠል ጥያቄዎቹ የውስጥ ልዩነታችንን ለአለም ከማጋለጥ ውጪ ምንም ፋይዳ አይኖራቸውም” ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል በየዓመቱ መስከረም አጋማሽ ላይ በመላው የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ዘንድ በድምቀት የሚከበረው የኢሬቻ በዓል በመጪው 2012 አዲስ ዓመት በአዲስ አበባ እንደሚከበር የተገለፀ ሲሆን፣ የዚህ በዓል አስተባባሪ ኮሚቴም የበዓሉን ዝርዝር አፈፃፀም በሚመለከት ከሰሞኑ መግለጫ ሰጥቷል፡፡

እንደ አስተያየት ሰጪዎች ከሆነ የኢሬቻ በዓል በአዲስ አበባ መከበር ከዚህ ቀደም ያልተለመደ በመሆኑ ሁኔታው ምናልባትም ከአዲስ አበባ የባለቤትነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ በብሔሮች መካከል ለተፈጠረው የአቋም ልዩነት አንዱ ማሳያ ሆኖ የሚጠቀስ መሆኑ እየተነገረ ይገኛል፡፡

## ሲፒጄ “የጋዜጠኞች ዕስር ወደ ቀደመው አፈናና እመቃ የሚመልስ ነው” አለ

ዓለም አቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተሟጋች (CPJ) ይፋ ባደረገው መግለጫ መንግሥት የኢትዮጲስ ጋዜጠኛ ምስጋናው ጌታቸውን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈታ ጠየቀ፡፡ የሲፒጄ አፍሪካ ተወካይ ሙቶኪ ሙሞ እንዳስታወቁት፤ “ድርጊቱ መንግሥትን ወደቀደመው አፈናና እመቃ የሚመልስ መልዕክት የታየበት ነው” ብለዋል፡፡

ተቋሙ በጉዳዩ ላይ የፌደራል ፖሊስንና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግን ማነጋሩን ጠቅሶ፤ ዕስሩ ከጋዜጠኝነት ጋር እንደማይገናኝና ተጠርጣሪዎቹም ሰኔ 15 በአማራ ክልል ከተከሰተው ችግር ጋር ተጠርጥረው የተያዙ ስለመሆናቸው እንደተነገረው ጠቅሷል፡፡

የሲፒጄው ሙቶኪ ሙሞ ግን የታሰሩ ጋዜጠኞች በአስቸኳይ እንዲለቀቁና በክስ ሂደት ላይ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የፀረ ሽብር አዋጅም እንዲቆም በመጠየቅ መንግሥት ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ መብትን እንዲጠብቅ አሳስበዋል፡፡

## የቁልቢ ገብርኤል ገዳም አስተዳዳሪ ሞተው ተገኙ

በምሥራቅ ሐረርጌ ዞን የቁልቢ ገብርኤል ገዳም አስተዳዳሪ መልዓከ ኃይለ ቆሞስ አባ ዕንቁስላሴ እንደሞቱ ተሰማ፡፡ አስተዳዳሪው ሞተው የተገኙት በቅዳሴ ቤታቸው ውስጥ ነው፡፡

የታላቁ ገዳም አስተዳዳሪ ሞተው መገኘትን ከተቃወሙ ሰዎች ደግሞ አንድ ሠው ሲገደል፣ አምስት ሰዎች ቆስለዋል፡፡ ቆሞስ እንቁስላሴ የቁልቢ አስተዳዳሪ ሆነው ከተሾሙ አራት ወራትን ብቻ ነው ያስቆጠሩት፡፡

መልዓከ ኃይለ ቆሞስ አባ ዕንቁስላሴ ወደ ቁልቢ ገዳም በኃላፊነት ከመጡበት ጊዜ አንስቶ፤ ከሕዝብ ጋር የቀረበ ግንኙነት ፈጥረው የሚሰሩ በመሆኑ ፣ ሞታቸውን የሰማው የከተማው ነዋሪ አደባባይ በመውጣት ተቃውሞውን በይፋ አሰምቷል፡፡በዚህም ከፖሊሶች ጋር በተፈጠረ ግጭት፣ የ8 ዓመት ህፃን ሲሞት፣ አምስት ሰዎች ደግሞ መቁሰላቸውን ቪኦኤ ዘግቧል፡፡

ቁልቢ ከተማ ሀያ ሰባት ዓመታት ሳይለማ ቢቆይም፤ አዲሱ አስተዳዳሪ ከመጡ በኋላ ግን ትልቅ መሻሻል ከመታየቱ ባሻገር፣ ለዘመናት በቤተ ክርስቲያኑ ላይ ይካሄድ የነበረውን ዝርፊያ በሦስት ወር ውስጥ በማስቆማቸው ጥርስ ተነክሶባቸዋል የሚሉት የአካባቢው ነዋሪዎች፤ የአስተዳዳሪው ግድያ ሆን ተብሎ የተቀነባበረ ነው የሚል ዕምነት እንዳላቸው ይናገራሉ፡፡ በጉዳዩ ላይ አስተያየታቸውን ለቮኦኤ የሰጡ የቁልቢ አካባቢ ተወላጆች፣ መልዓከ ኃይለ ቆሞስ አባ ዕንቁስላሴ ለቁልቢ ገዳም የሚመጥኑ ትክክለኛው አስተዳዳሪ እንደነበሩ መስክረዋል፡፡

## “ብዕሲት ኢትዮጵያ ሽልማት” በሕዳር ወር ያካሂዳል

“ብዕሲት ኢትዮጵያ” የሽልማት መርሃ ግብር በዓይነቱም ሆነ በአተገባበሩ ልዩ ጥንቃቄ ተደርጎበት እንደሚካሄድ የዮቤግ ኮሚኒኬሽንና ሚዲያ ፐብሊሺንግ በቤስት ዌስተርን ፕላስ ሆቴል ጋዜጣዊ መግለጫ አስታውቋል፡፡ በዕውቀታቸው፣ በተሰለፉበት የሥራ መስክ ውጤታማ የሆኑ፣ በአርአያነት አገራቸውንና ሕዝባቸውን እያገለገሉ ያሉ ግለሰቦችን የወለዱ ፣ ያሳደጉ እና ለቁም ነገር ያበቁ እናቶችን በይፋ ዕውቅና ለመስጠት፣ ለመሸለም እንደታሰበ ነው የሠማነው፡፡ “ብዕሲት ኢትዮጵያ ሽልማት” እናቶች ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገበት ምክንያት በርካታ ኢትዮጵያዊት እናቶች ለአደባባይ ክብር እንዲበቁ ለማበረታታት ጭምር ታስቦ ነው ተብሏል፡፡ የሽልማት ሥነ ሥርዓቱ በቀጣይ ዓመት፤ ህዳር 20 ቀን 2012 ዓ.ም እንደሚከናወን ታውቋል፡፡

# የኢሕአዴግ ዕርቅ ከራሱ? ወይስ ከፖለቲካ ፓርቲዎች እና ከሕዝብ?

የዜጎች መፈናቀል በየክልሎቹ በተንሰራፋበት፣ የመንደር ጎረምሶች ራሳቸውን እንደ "ነፃ አውጪ" ኃይል በመቁጠር ዝርፊያ እና ጥቃት መፈፀምን የአደባባይ ተግባር ባደረጉበት፣ ብሔራዊ ስሜትና የሀገር ፍቅር "ብን" ብሎ በጠፋበት በዚህ ወቅት፤ የይቅርታ፣ የሠላም እና የአንድነት ፌስቲቫል ሊዘጋጅ መሆኑን ሰማን፡፡ ዓላማው "እሰየው" የሚያስብል መሆኑ ባያጠራጥርም፣ የዕርቁ መዳረሻ ምን ድረስ ነው? የሚለው ግን በእጅጉ አጠያያቂ ነው፡፡

ጳጉሜ 2 እና 3 2011 ዓ.ም ይካሄዳል የተባለው ይህ የሠላም ፌስቲቫል በፖለቲካዊ ሥርዓቱ ክፍተት የተስተዋለባቸውን ክልሎች ባወቀረ መልኩ እንደሚካሄድ፣ የዘጠኙም ክልል መሪዎች በጋራ በመታደም፣ ለይቅርታ እና ለአንድነቱ መሰናዷቸውን አጠናቅቀዋል ቢባልም ፤ ከመንግሥታዊ ሥርዓቱ እንዳፈነገጠ ደጋግሞ ያሣየው ህወሓት ግን ግብዣውን የተቀበለ አይመስልም፡፡

ድርጅቱ በሚያስተዳድረው የክልሉ ቴሌቪዥን የሚያቀርባቸው ዘገባዎች በሙሉ ት.ህ.ነ.ግ ለሠላም ፌስቲቫሉ እንዳልተዘጋጀ የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ በጉዳዩ ላይ አስተያየት የሚሰጡ የትግራይ ክልል ባለሥልጣናት እና ነዋሪዎችም የአፈንጋጩን ህወሓት ባህሪ ከማስተጋባት ባሻገር፣ በቅድሚያ የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶችም ሆኑ ክልሎች የትግራይ ክልል መንግሥትን ይቅርታ ሊጠይቁ ይገባል ሲሉ ይከራከራሉ፡፡ በዘርፈ ብዙ ወንጀሎች የሚፈለጉ ሹማምንት ከመሸጉበት መቀሌ የሚናፈሰው ፖለቲካ ይህን መሠል መሆኑ ፌስቲቫሉን ጎዶሎ ሊያደርገው ይችላል፡፡

አልያም እንደፈለጉ የሚገለባበጡት ዶ/ር ደብረፂዮን ገ/ሚካኤል የተለመደ የአርቲስትነት ባህሪያቸውን ሊያሣዩን ይችላሉ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ዕርቅ እና ይቅርታ የሚፈልገውን ዘለቄታዊ ሠላምም ሆነ አንድነት ሊያመጣ አይችልም፡፡ ከዚህ ቀደም ለፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ ሲባል "ታርቀናል" ብለው ሲተቃቀፉ ያየናቸው አቶ ገዱ አንዳርጋቸው እና ዶ/ር ደብረፂዮን ፤ አሁን የለየለት የሚመስለውን የአዴፓ እና የህወሓት ውዝግብ እንዳይከሰት ማድረግ አልቻሉም፡፡

በእውነተኛ መተማመን እና መግባባት ላይ ያልተደረገ ስምምነት አንድ ዕርምጃ ወደ ፊት መሄድ አይችልም፡፡ ከለውጡ ወዲህ በአማራ፣ ትግራይ፣ ሶማሌ፣ ኦሮሚያ፣ ቤኒሻንጉል፣ ደቡብ፣ ጋምቤላ ፤ ሁሉም ክልሎች (ከአዲስ አበባ ውጪ) ለማለት በሚያስደፍር መልኩ አንዱ ከሌላው ሲላተም ሰንብቷል፡፡ በዚህ መሰሉ የብሔርተኝነት ፖለቲካ ደግሞ ሠርክ ተጠቂዎቹ ንፁሃን ዜጎች መሆናቸው አያጠያይቅም፡፡

ከኹለት ሣምንት በኋላ የሚከናወነው የይቅርታ፣ የአንድነት እና የሠላም ፌስቲቫል ትኩረቱን በክልል መሪዎች ላይ ማድረጉ በአንድ በኩል የችግሮች ሁሉ ምንጭ ኢሕአዴግ ራሱ መሆኑን አምኖ ክፍተቱን ለመሙላት እየጣረ መሆኑን ሲያሳይ፤ በሌላ በኩል ድርጅቱ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር ዘወትር ከመወነጃጀል ወደ ሠላም መንገድ ለመምጣት ያለውን ቁርጠኛ ፍላጎት ግን አላመለከተም ማለት ይቻላል፡፡

ብሔር ተኮር ሆነው የተወቀሩ አክራሪ ብሔርተኛ ድርጅቶች የሚያራግቡት ፖለቲካ ሥር ሰድዶ ብዙ ጥፋት ማስከተሉን ልብ ካልን ኢሕአዴግ ከምንም በላይ ቅድሚያ ሠጥቶ መሥራት ያለበት ኢትዮጵያዊ አንድነትን ሸርሽረው ፣ ጎጠኝነትን ለመትከል ከሚፈልጉ ኃይሎች ጋር እውነተኛ ዕርቅ ከማድረግ ባሻገር፣ በሥጋት ለሚዋትተው ሕዝብ የሠላምን ንፁህ አየር እንዲያጣጥም ዕድል መፍጠር ይኖርበታል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በራሱ ፍላጎት እና ተነሳሽነት ሕዝብ ከሕዝብ ተጋጭቶ አያውቅም፡፡ "የእኔነት" ስሜት እንዲንሰራፋ የሚፈልጉ ብሔርተኛ ልሂቃን እና ፖለቲከኞች በሚቀሰቅሱት ሁከትና በሚያናፍሱት ፕሮፓጋንዳ እየተነዳ የሚበጣበጠው፣ ጥቂት ሕብረተሰብ ከዚህን መሰሉ የጥፋት ጉዞ እንዲገታ ከተፈለገ፤ ኢሕአዴግ በቅድሚያ የራሱን ውስጣዊ ችግር ፈትቶ፣ በቀጣይ ከፖለቲካ ድርጅቶች እና ከሕዝብ ጋር መታረቅ ይኖርበታል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎችም እርስ በርስ ከመጠላለፍ ወጥተው፣ ልዩነቶቻቸውን በማጥበብና በመታረቅ ከመሪው ፓርቲ እንዲሁም እያናከሱት ካለው ሕዝብ ጋር ዕርቅ ሲያደርጉ ብቻ የምናልመውን ሠላም በመዳፋችን መጨበጥ እንችላለን፡፡

ሰሞኑን በሱዳን ሠላም ላይ ዋነኛውን የሽምግልና ሚና የተጫወቱት፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እና ወታደራዊ ኃይሉ ሥልጣን እንዲጋሩ ያፈራረሙት ጠቅላይ ሚኒስትር በውስጣዊ ችግሮቿ የተበተበቸው ሀገራችን ከጎረቤቷ የሠላም መንገድ ብዙ መማር እንደምትችል ተገንዝበው፣ የይቅርታ ፣ የሠላም እና አንድነቱን መን ገድ ዕውን ለማድረግ ትኩረት ሠጥተው መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡


## ግዮን መጽሔት

**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**
**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ

**ማኔጂንግ ኤዲተር**
ኄኖክ ገለታው

አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ ወረዳ 2
የቤት ቁጥር 475

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
አለማየሁ ባዘዘው
ብሩክ መኮንን

**አዘጋጅ**
ፍቅርተ ተሾመ
ሙሉጌታ አክሊሉ

**አምደኞች**
ፍቅሩ ኪዳኔ **(ከሲውዘርላንድ)**
ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ
ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ
መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ፍፁም ንጉሴ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 2ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁ. 207
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661 +251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011meg@gmail.com
Facebook
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013

**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ
0911223335/ 0911420506


በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም

# “ምርጫ ቦርድ ማነው?!”

## አዲሱ አዋጅ፣ ምርጫ ቦርድ እና የፓርቲዎቹ ውዝግብ

መለክ ቢ.

ብዙዎች እንደሚስማሙበት በደርግ እና በኢህአዴግ መካከል ዴሞክራሲን በተመለከተ ያለው አንድ ልዩነት ደርግ ዴሞክራሲን በሃሳብም በተግባርም “የማይታሰብ” አድርጎ መክልከሉ ሲሆን ኢህአዴግ ደግሞ በተቃራኒው ዴሞክራሲን በመርህ ደረጃ ፈቅዶ በተግባር ግን “ላም አለኝ በሰማይ” አድርጎ 27 ዓመታት መዝለቁ ነው። በድምር ንጽጽር ሲታዩ የቀደመውም ሆነ የተከተለው መንግሥት ዴሞክራሲን “የለም” እና “አለ” ከማለት በዘለለ እንካችሁ ያላሉ ናቸው።

ደርግ እውነተኛ ማንነቱን አውጥቶ በማሳየት የተቃወሙትን ሁሉ በግልጽ ፊት ለፊት ተጋፍጦ መደፍጠጡ የመንግሥትነት ባህሪውን ምንነት ለማወቅ ረድቷል። ለዚህም ነው ፍጹም አምባገነን መንግሥት ተብሎ ይጠራ የነበረው። ኢህአዴግ በተቃራኒው ዴሞክራሲን የሥርዓቱ ማጠንጠኛ ማዕከል እና የሕጋዊ ሥርዓቱ ድር አድርጎ ሲያበቃ በተግባር ለመፈጸም ፍቃደኛ አለመሆኑ ግን የመንግሥትነት ባህሪውን ለመለየት አዳጋች አድርጎታል። ብዙዎች “ኢህአዴግ የመንግሥትነት ባህሪው ዴሞክራሲያዊ ወይም አምባገነናዊ ነው” ብለው የማንነት ውሉን ለመረዳት ያላስቻላቸውም ፓርቲው ባለው ተለዋዋጭ ባህሪ ሳቢያ ነው።

ሁለቱን ፓርቲዎች (የደርጉ ኢሰፓ እና ኢህአዴግ) የፖለቲካ ተንታኞች በዴሞክራሲ ሚዛን ሲሰፍሯቸው “ደርግ የማይፈጸም ህግ ደንግጎ ዴሞክራት መንግሥት ከመባል ይልቅ ዴሞክራሲን በይፋ ከልክሎ አምባገነን መባሉ በህግ አለማላገጡን የሚያመላክት ነው” በማለት ይገልጹታል። በተቃራኒው ኢህአዴግ ራሱ በሕገመንግሥቱ ያሰፈራቸውን የዴሞክራሲ ሕጎች ለመተግበር ምጥ የሚይዘው መንግሥት መሆኑ ራሱ ባወጣው ህግ የሚያላግጥ አሿፊ መንግሥት መሆኑን ያመላክታል ይሉታል ።

ዛሬ ስለዴሞክራሲ የምናወራው ከሁለቱ የሰለሰ መንግሥት ኖሮ ሳይሆን ሁለተኛው መንግሥት [ኢህአዴግ] ራሴን አድሻለሁ በማለቱ ምናልባት በዴሞክራሲ ጆርባ ላይ ጭኖ ባያሳፍረንም ጭራውን ያስይዘን እንደሆን ለመፈተሽ እንዲረዳን ነው።

የዴሞክራሲ መሠረታዊ መገለጫ ነጻ እና ፍትሃዊ ምርጫ ነው ከተባለ ኢትዮጵያ ዛሬ ባለችበት የፖለቲካ ሽግግር ኢህአዴግ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ መርህ ውስጥ የሰነበተ አቅሙን አቅንቶ የሚመራትን ሃገር እና ሕዝቡን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማሸጋገር ይችላል ወይ የሚለውም ጥያቄ ይነሳል።

ያለፈው አንድ ዓመት ብዙዎች ተስፋ ያደረጉበት የዴሞክራሲ ጅምር ዳግም ወደነበረበት ሲከለስ መታየቱ አስጊ ቢሆንም ቢያንስ በዶክተር ዐብይ እና በለውጥ አጋሮቹ ኢትዮጵያ ላለፉት 27 ዓመታት ከኖረችበት የስም ዴሞክራሲ ወጥታ በተግባር የሚመነዘር የዴሞክራሲ ፍሬ እንድታፈራ የተጀመረ የሚመስለው መንገድ ተስፋው አልቀጨጨም።

የዶክተር ዐቢይ ኢህአዴግ ዴሞክራሲ አለ ብለው ሃሳባቸውን በነጻነት የገለጹ ፣ ነገር ግን የተፈቀደላቸውን መብት በመጠቀማቸው ሳቢያ እንደአጥፊ ተቆጥረው በየእስር ቤቱ የታጎሩ ዜጎችን ከፈታ በኋላ በውጭ ያሉ፣ ለኢትዮጵያ ህዝቦች ጥቅም ነፍጥ አንስተውም ይሁን በሃሳብ ተግተው የታገሉ የፖለቲካ ድርጅቶችን ወደሃገር ቤት ገብተው ትግላቸውን በሰላማዊ መንገድ እንዲያካሂዱ ጋብዟል። ይህም እጅግ ስኬታማ በሚባል ሁኔታ ሁሉንም (እንደአርበኞች ግንቦት ሰባት፣ ኦነግና ኦብነግ ያሉ) በትጥቅ ትግል ጭምር የታገዘ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ያደርጉ የነበሩትንና በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉ ፓርቲዎችን ወደሃገር ውስጥ በማምጣት ተጠናቋል።



የብሄራዊ የምርጫ ቦርድ ፕሬዝዳንት ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ

ከዚህ በኋላ የቀረው ምን ነበር ? በኢትዮጵያ ነጻ እና ፍትሃዊ ምርጫ አካሂዶ ህዝብ የመረጠው ፓርቲ አገር እንዲያስተዳድር ማድረግ። ይህንን ለማካሄድ ግን የፖለቲካ ውግንና ባላቸው ግለሰቦች ከአፍ እስከገደፉ ሞልቶ የነበረው ምርጫ ቦርድ ዳግም ተዋቅሮ የፓርቲዎችን አመኔታ እንዲያገኝ ሆኖ መቀረጹ ግድ ነበር። የቀድሞ የቅንጅት ለአንድነት እና ዴሞክራሲ ሊቀመንበር የነበረችው እና በዚህ ሳቢያ ለእስር እና እንግልት የተዳረገችው ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን እንድትመራ ስትሾም በሁሉም ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች ዘንድ ማለት በሚቻል መልኩ ታላቅ ተስፋ አድሯል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐብይ በተለያዩ መድረኮች ላይ “የኔ ብቸኛ ግብ በኢትዮጵያ ነጻ እና ፍትሃዊ ምርጫ በማካሄድ እውነተኛ ዴሞክራሲ መስፈኑን ማረጋገጥ ነው “ በማለት በውጭ ሃገር የሚኖሩ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደሃገር ቤት ገብተው ሁለት ዓመት ለቀረው የ2012 ምርጫ እንዲዘጋጁ ጥሪ ባቀረቡት መሰረት ያንን ቃል አምነው እና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ይካሄዳል የሚል ተስፋን ሰንቀው የየራሳቸውን ዝግጅት በማድረግ ላይ ያሉ ፓርቲዎች ቁጥር ጥቂት አይደለም።

### ‘አዲሱ’ ምርጫ ቦርድ

“ፍሪደም ሃውስ” የተባለው በዓለም ዙሪያ በየአገሮቹ የሚታየውን የነፃነትን ሁኔታ የሚከታተለው ተቋም በአንድ ወቅት ባደረገው ጥናት መሠረት በኢትዮጵያ የተካሄዱትን ምርጫዎች ሁሉ “ነፃ ያልሆነ” (not free) በሚል ገልጾዋቸዋል። ዶክተር ዐብይ ደግሞ ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያ የሚካሄደው ምርጫ ነጻ እንደሚሆን ከራሳቸው ዓላማ ጋር ▶

አስተሳሰረው ቃል ገብተዋል።

ባለፉት 27 ዓመታት በኢትዮጵያ ‹‹አለ›› የሚባለውን ዴሞክራሲ የሚያረጋግጡ ናቸው ተብለው የተቋቋሙት የዴሞክራሲ ተቋማት ህዝብ የሚጠብቅባቸውን ተግባር ሳይሆን መንግሥት ያዘዛቸውን ብቻ ሲተገብሩ አይተናል። ይህ ደግሞ ህዝብ በመንግሥት አስፈጻሚ አካላት ቢበደል አቤት የሚልበት ቦታ ቢኖርም ፍትህ እንዳያገኝ ግን አድርጎታል። በ1997 ዓ.ም ምርጫ ወቅት ኢህአዴግ በግልጽ የህዝብ ድምጽ አጭበርብሯል ተብሎ ክስ እየቀረበበት ምርጫ ቦርድ ግን የኢህአዴግ የራሱ ስለሆነ የኢህአዴግን አሸናፊነት ከማጽናት በቀር የወሰደው አንዳች እርምጃ አለመኖሩ ለዚህ ነጻና ገለልተኛ አለመሆን አንዱ መገለጫው ተደርጎ ይወሰዳል። ምርጫዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል ከ134 ሐገራት በላይ እንደሚንቀሳቀሰው “The International Foundation for Electoral Systems” የተሰኘ ተቋም አንድ ጥናት ከሆነ በዘመነ ኢህአዴግ በተካሄዱት በመጀመሪያዎቹ ሦስት ምርጫዎች የተቃዋሚዎች የመወዳደር አቅም እጅግ ደካማ የነበረ በመሆኑ ኢህአዴግ በምርጫዎቹ ዴሞክራሲያዊ መሆን ወይም አለመሆን ብዙም አልተጨነቀም ነበር ይላል። በአራተኛው ወይም በምርጫ 97 ተቃዋሚዎች ተጠናክረው ሲቀርቡ ግን ኢህአዴግ ምርጫውን አጭበረበረና ‹‹ዓይኔን ግንባር ያድርገው›› አለ። ለዚህ የተባበረው ደግሞ በርሱ ሳንባ የሚተነፍሰው ምርጫ ቦርድ በመሆኑ ከዚያ በኋላ ባሉት ጊዜያት ኢህአዴግን ተቃውመው የሚንቀሳቀሱት የፖለቲካ ፓርቲዎች አንድም ቀን ምርጫ ቦርድን ተዓማኒ ተቋም አድርገው ሊቀበሉት አልቻሉም።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በግልጽ በሚታይ አድልዎ በሃገሪቱ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ ጥፋት ሲፈጽምና ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ሥልጣኑን ተቆናጦ እንዲጨፍር እገዛ ሲያደርግ የኖረ ተቋም ስለመሆኑ ራሱ የአሁኑ ኢህአዴግ አመራር ጭምር የሚያምነው ሃቅ ሆኗል። በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ግለሰቦች ከነበራቸው የፖለቲካ ተሳትፎ እንዲያፈገፍጉ ምክንያት ከሆኗቸው ጉዳዮች አንዱ የምርጫ ቦርድ ግልጽ አድልዎ መሆኑን ሲናገሩ ተሰምቷል። የኢትዮጵያ ህዝብ በምርጫ ቦርድ ላይ የነበረውን የገለልተኛ ተቋምነት ዕምነቱን ያነሳው ደግሞ በ1997 ዓ.ም በተደረገው ምርጫ በቀድሞ ሊቀመንበሩ ፕሮፌሰር መርጋ በቃና በኩል ኢህአዴግን ‘አሸንፏል’ ብሎ እውቅና ደፍሮ በመስጠቱ ነው። ለዚህ ነው ይህ ምርጫ ቦርድ ራሱን እስካልለወጠ ድረስ ከኖረበት ኢህአዴጋዊ አድልዎ አስተሳሰብ ተላቅቆ ፍትሃዊ ዳኛ ይሆናል ብሎ ለማመን ችግሮ የቆየው።

## “ምርጫ ቦርድ” ዳግም ለውዝግብ?

ከሰሞኑ አዲሱ የምርጫና የፖለቲካ ፓርቲዎች ረቂቅ አዋጅ ከመውጣቱ አስቀድሞ የፖለቲካ ፓርቲዎች ኢህአዴግን ጨምሮ ሰፊ ጊዜ የወሰደ ውይይት አካሂደው የቃል ኪዳን ሰነድ ተፈራርመው ነበር። በዚያ ስምምነታቸው የምርጫ ሂደቱ ምን መልክ ሊኖረው እንደሚገባ ተነጋግረው ምርጫ ቦርድም ይህንኑ ለማስፈጸም የሚያስችል መዋቅር ይዞ እንዲደራጅ ተነጋገረው እና የቀድሞው የምርጫ ሕግም ተከልሶና ተስተካክሎ እንዲመጣ ሃሳብ ሰጥተው ተስነባብተው ነበር። የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በአባልነት ከመዘገባቸው 130 በላይ ፓርቲዎች የተስማሙበትን ከ60 ገጽ በላይ ሰነድ ፈርመው ሲጠባበቁ ለውይይት የቀረበው አዲሱ ረቂቅ ህግ ግን የሚያጯጩሃቸው ሆኖ ተገኝቷል። ለዚህም ነው በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በዚህ ረቂቅ ሕግ ላይ የህዝብ ውይይት ሲካሄድ የምርጫ ቦርድ ሃላፊዎች ሕጉን በመደገፍ ዘብ መቆማቸውን ያዩ ብዙ ፓርቲዎች ስብሰባውን ረግጠው ለመውጣት የበቁት። ምርጫ ቦርድ ማነው የሚለው ጥያቄም ከነዚሁ ፓርቲ አመራሮች አፍ ተደጋግሞ መሰማት የጀመረውም ከዚህ ጊዜ በኋላ ነው።

> ኢህአዴግ ምርጫው አሁን እንዲደረግ የሚፈልገው ሆን ብሎ ‘የተዘጋጁ ፓርቲዎች የሉም’ በሚል ህዝቡን በማሳሳት ለመመረጥ እንጂ በርግጥም ሕገመንግሥቱን ለማክበር ፍላጎት አድሮበት አይደለምም ባዮች ናቸው

## የፓርቲዎቹ መግለጫ

33 የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ቦርዱን ገለልተኝነት በሚጠይቅ ሁኔታ አዲስ የወጣው የፓርቲዎች እና የምርጫ ረቂቅ አዋጅ በኢትዮጵያ ተጀምሮ የነበረውን ለውጥ ወደኋላ የሚጎትት እና ዳግም ወደቀደመው ዘመን የሚመልስ አካሄድ እንደሚያሰፍን በመግለጽ በፍጹም እንዳይጸድቅ ማስጠንቀቂያ አዘል መግለጫ አውጥተዋል።

“በአፋኝ እና አፍራሽ አንቀጾች የተሞላው ረቂቅ አዋጅ ሳይሻሻል እንዳይፀድቅ አጥብቀን እንጠይቃለን” በሚል ርዕስ የወጣው የፓርቲዎቹ መግለጫ ከበድ ያሉና የፓርቲዎቹን የስሜት መነካት የሚያሳብቁ ቃላቶች የታጨቁበት ነው። “ሃገራችን ላለፉት 27 ዓመታት ውስብስብ የሆነ የሴራ ፖለቲካና በርካታ የግፍ ዕዋ ስትጨልጥ መቆየቷ አይዘነጋም። ይሁን እንጂ ያሳለፍናቸው መራራ የትግል ወቅቶች አሁንም ከዓመት እረፍት በኋላ ወደ የቦታቸው ሊመለሱ እንደሆነ የሚያሳዩ ብዙ ምልክቶች እያየን ነው” ብለዋል ፓርቲዎቹ። ለዚህ ደግሞ በዋናነት ያቀረቡት መገለጫ በመንግሥት የተቋቋመው የሕግ ማሻሻያ ም/ቤት እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አሻሻልኩት ያለው የምርጫና የፖለቲካ ፓርቲዎች ረቂቅ አዋጅን ነው። እንደፓርቲዎቹ መግለጫ ሁሉም በምርጫና የፖለቲካ ፓርቲዎች ረቂቅ አዋጅ ላይ በስፋት በመመካከር በከፊል የተስማሙበትን በፅሁፍ አስገብተዋል። ነገር ግን በረቂቅ አዋጁ ላይ የተደረጉ ስምምነቶችንና ማሻሻያዎችን ወደጎን በመተው ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የቀረበው ረቂቅ አዋጅ የህግ ማሻሻያ ም/ቤቱንም ሆነ የምርጫ ቦርድን ገለልተኝነት ከወዲሁ ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ሆኖ አግኝተነዋል ነው ያሉት። እንደፓርቲዎቹ መግለጫ ይህ አካሄድ አንድ ፓርቲን [ኢህአዴግን] ለመጥቀም ሆን ተብሎ የተሰራ ሥራ ነው።

## የተቃውሞ ነጥቦች

33ቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለፓርቲዎች ምዝገባ መመዘኛነት እና ለእጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበው መስፈርት በፍፁም ተቀባይነት የሌለውና የመድብለ ፓርቲ ሥርዓትን የሚጨፈልቅ ነው በማለት ሲተቹ የተጠቀሱት አሣዞች በረቂቅ ህጉ ማሻሻያም ሆነ በጋራ ስምምነት ላይ የተወያዩባቸውን አለመሆናቸው በመግለጽ ነው። የምርጫውን አሸናፊ አስቀድሞ የሚበይን የፀረ ዲሞክራሲ ፅንሰ ሀሳብ የያዘ ነው ያሉት ይኸው መስፈርት ለዚህም ማሳያው አንድ ሃገር አቀፍ ፓርቲ ቢያንስ 10ሺህ ደጋፊዎች ፊርማ ማሰባሰብ እንዳለበት የሚያዝ መሆኑ ነው ብለዋል።

የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ከረቂቅ አዋጁ ውስጥ 20 አንቀጾች እንዲሻሻሉ ፣ ቀሪ 13 አንቀጾች ደግሞ እንዲሰረዙ ጥያቄ አቀርበዋል። ከስምምነት ላይ ሳንደርስ ረቂቅ አዋጁ መፅደቅ የለበትም ሲሉም አቋማቸውን ገልጸዋል።

ይህንን መሰረት በማድረግም ባወጡት ባለአምስት ነጥብ የአቋም መግለጫ ላይ አሁን ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የቀረበው የምርጫና የፖለቲካ ፓርቲዎች የረቂቅ አዋጅ ይዘት የዜጎችን የመደራጀት፣ የመምረጥና የመመረጥ መብት የሚገድብ እንዲሁም የመላው ሕዝብ ጥቅምም ሆነ የፓርቲዎችን ሕልውና የሚጋፋ መሆኑን አስምረውበታል።

ፓርቲዎቹ እንዲሻሻሉ የጠየቋቸው 13 አንቀጾች አንቀጽ 4፣ 13፣ 17፣ 18(ሐ)፣ 25፣ (3)፣ 31፣ 33 (ሐ)፣ 34፣ 44፣ 46፣ 64 (ሀ)፣ 80 (2) እና 160 (2) ሲሆኑ፣ እንዲሰረዙ የጠየቋቸው 20 አንቀጾች ደግሞ አንቀጽ 32፣ 64፣ 65፣ 66፣ 71፣ 74(1)፣ 74(3)፣ 75፣ 78 (1)፣ 82 (3 እና 4)፣ 91(3)፣ 93፣ 96 (2)፣ 98 (1 እና 2)፣ 100 (1)፣ 100 (3)፣ 102፣ 111(1)፣ 160(2) እና 160 (3) ናቸው፡ ፡ ፓርቲዎቹ በረቂቅ አዋጁ ላይ በግልጽ የሚታዩ የሕግ ክፍተቶችና ‹አፋኝ› አንቀጾች ተለይተው ሳይስተካከሉና ሳይሰረዙ፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ረቂቁን ወደ ውሳኔ እንዳያቀርበው ጠይቀዋል።

በመገናኛ ብዙኃን ተደጋግመው የሚሰሙትና ምርጫ ቦርድ እና የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ተከራከሩበት የተባሉት አንቀጾች ሁለት ቢሆኑም ፓርቲዎቹ ግን እነዚያ ሁለት አንቀጾች ብቻ ተለይተው የወጡትና የተራገቡት ሆን ተብሎ የነርሱን ጥያቄ ለማኮሰስ እና በህዝቡ ዘንድ ውዥንብር በመንዛት የፓርቲዎቹን መልካም ስም ለማጠልሸት መሆኑን ይናገራሉ።

ሃገራዊ ፓርቲዎች ለምርጫ ውድድር ምዝገባ 10 ሺህ ደጋፊ አስፈርመው እንዲመጡ መጠየቃቸው አግባብ አለመሆኑን ብቻ ሳይሆን ‹‹ይህ ቁጥር ሳንወያይበት ለምን በህጉ ውስጥ

ገባ?›› የሚል ጥያቄም አላቸው:: ምርጫ ቦርድ ከስምምነቱ ውጪ በሕግ ማሻሻያ ምክር ቤቱ የገባው አ'ንዝ ላይ ደጋፊ ሆኖ መቅረቡ ደግሞ በገለልተኝነቱ ላይ ጥያቄ እንድናነሳ አድርጎናል ሲሉም ይጠቅሳሉ::

"ዋና ጥያቄያችን 10ሺህ የድጋፍ ፊርማ አሰባስቡ መባሉ አይደለም፣ ይህ አ'ንዝ ከየት መጣ የሚል ነው:: ስንወያይ እንዲህ ዓይነት አ'ንዝ አልተቀመጠም ነበር:: ይህ ኢህአዴግን ሆን ብሎ ለመጥቀም የተካሄደ ሥራ መሆኑን ለመገመት አስችሎናል:: አሁን በሃገሪቱ ባለው የጸጥታ ችግር 10ሺህ ሰው የድጋፍ ፊርማ ለማሰባሰብ በየክልሉ መዞር አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል:: በእሳት ውስጥ ተራምደህ ና ብሎ መጠየቅ ሆን ብሎ አትምጣ እንደማለት ይቆጠራል:: ይህንን ስንቃወም ሚዲያ ላይ አውጥተው 'አንድ ሃገራዊ ፓርቲ 10ሺህ ሰው ካላስፈረመ እንዴት ሃገራዊ ነኝ ይላል የሚል ጥያቄ አስነሱ:: ይህ ሆን ተብሎ ህዝብ በሃገሪቱ ባሉ ፓርቲዎች ላይ ያለው ዕምነት እንዲላላ እና እንደቀድሞው ለዚህች ሃገር ኢህአዴግ መኖሩ አስፈላጊ ነው የሚል የዕምነት ውኸ'ንብር ውስጥ እንዲገባ የተሸረበ ሴራ ነው:: ሌሎች ያነሳናቸው ብዙ ጥያቄዎች ተድበስብሰው ቀርተዋል :: ይህ ደግሞ አስቆጥቶናል" ብለዋል የፓርቲ አመራሮቹ ለመገናኛ ብዙኀን በሰጡት መግለጫ::

በዚህ መሃል ለውጥ ሲመጣ ተበተነ:: አሁን ተመልሶ አብላጫ ድምጽ ሥርዓት ሲመጣ እና ፓርቲዎቹ እንዲሻሻል ሲጠይቁ "ሕገመንግሥታዊ ማሻሻያን የሚፈልግ በመሆኑ እና ህገመንግስቱን ማሻሻል ደግሞ ጊዜ ስለሚወሰድ" በማለት ምርጫ ቦርድም ይሁን የሕግ ማሻሻያ ምክር ቤቱ አልተቀበሉትም:: ፓርቲዎቹ ግን ኢህአዴግ በርግጥም ፍላጎቱ ዴሞክራሲያዊ እና ፍትሃዊ ምርጫ እንዲካሄድ ከሆነ ይህንን አንቀጽ ለማሻሻል አያዳግተውም ባይ ናቸው::

## ምርጫ ቦርድ ምን ይላል?

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ይህንን መሰል ጥያቄዎች ሲቀርቡበት እና ከዚያም አለፍ ብሎ የገለልተኝነት ጥያቄዎች ሲነሱበት የራሱን ምላሾች በድረገጹም ይሁን በመገናኛ ብዙኀን ላይ በተካሄዱ ክርክሮች ሰጥቷል:: በዋናነት የፓርቲዎች የድጋፍ መጠን እንዲጨምር የተወሰነው ካላቸው ብዛት አንጻር ስማቸው እንኳን የማይታወቅ በመሆኑ ከህዝቡ ጋር እንዲገናኙ እንዲሁም የመታወቅ ዕድላቸውን እንዲያሰፉ፣ እንዲሁም የገቢ ምንጫቸው ከአባላት በሚሰበሰብ መዋጮ በመሆኑ ብዛቱ እንደሚጠቅማቸው፣ ማኀበራዊ መሰረታቸው እንዲጠናከር ወዘተ በማሰብ መሆኑን ገልጿል::

የፓርቲዎቹ ስጋት ደግሞ በአጠቃላይ ከ29 ፓርቲዎች የቀረበው 48 አንቀጾች ላይ ማሻሻያ በረቂቅ ሕጉ ውስጥ ይካተት አይካተት ሳያውቁ ሕጉ ወደሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊላክ እየተቃረበ በመሆኑ ሕግ ሆኖ ከጸደቀ በኂላ ሊያመጣ የሚችለውን መጓተት በመስጋት እንዳይጸድቅ እና ዳግም ውይይት እንዲደረግበት ጠይቀዋል:: በተለይም ከቀረቡት የማሻሻያ ሃሳቦች ውስጥ የትኞቹ ተቀባይነት አግኝተዋል የትኞቹስ ወደቁ የሚለው ሳይታወቅ ሕጉ ጸድቆ መምጣት የሌለበት መሆኑን አጥብቀው አሳስበዋል::

## ኢህአዴግ ዳግም አፋኝ ይሆናል?

"ኢህአዴግ ባህሪው ነውና መቼም ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ መሆን አይቻለውም:: አሁንም ምርጫው ሲቃረብ አፋኝ መሆኑን ከወዲሁ መገመትም አያዳግትም" ይላሉ ጥያቄ ካቀረቡ 33 ፓርቲ ተወካዮች አንዱ:: ኢህአዴግ መጪው ምርጫ በተያዘለት የጊዜ ገደብ እንዲካሄድ ተስማምቷል:: ለዚህ ደግሞ ዝግጅት እያደረግኩም ነው ብሏል:: ፓርቲዎቹ በበኩላቸው መጪው ምርጫ ይራዘም ባዮች ናቸው::

ምክንያታቸው ደግሞ የቀረው ጊዜ አጭር በመሆኑና የፖለቲካ ፕሮግራምን ለማሳወቅ እንኳን የማይበቃ በመሆኑ ነው:: ኢህአዴግ ምርጫው አሁን እንዲደረግ የሚፈልገው ሆን ብሎ 'የተዘጋጁ ፓርቲዎች የሉም' በሚል ህዝቡን በማሳሳት ለመመረጥ እንጂ በርግጥም ሕገመንግሥቱን ለማክበር ፍላጎት አድሮበት አይደለምም ባዮች ናቸው :: በሃገሪቱ ያለው የጸጥታ ሁኔታ አለመመቸት፣ እጩዎች ተዘዋውረው ህዝብን ለመቀስቀስ፣ የፖለቲካ ፕሮግራሞቻቸውን ለማሳወቅ አለማስቻሉ፣ የፋይናንስ እጥረት መኖሩ፣ የአባላት ምልመላ ለማድረግ ጊዜ መፈለጉ እና ወዘተ ብዛት ካላቸው ፓርቲዎች አንጻር በዚህ አጭር ጊዜ ሊከወን ስለማይችል መድረኩ ላይ ያለው ኢህአዴግ ብቻ ነው የሚል አስተሳሰብ ጭኖ በህዝብ ዘንድ የተስፋ መቁረጥ እሳቤ እንዲሰርጽ ይፈልጋል በማለትም ኢህአዴግን ይከስሱታል:: ይህ በርግጥም ፓርቲዎቹን ባያሳስብ እና ይካሄድ ቢባል እንኳን በምን ሁኔታ ምርጫው ፍትሃዊ ሆኖ ሊካሄድ ይችላል የሚል ጥያቄ ያስነሳ ሆኗል::

ጠቅለል ባለ አነጋገር ገና ሃገር አንድ ዓመት በለውጥ ሂደት ኖራ እንፋሎቷ ሳይበርድ ዳግም የዴሞክራሲ ተቋማት ላይ የገለልተኝነት ጥያቄ መነሳቱና ምርጫው ላይ ከወዲሁ የጥርጣሬ ጥላ ማርበቡ የሃገራችን የዴሞክራሲ ሂደት ዳግም ወደኂላ ሊጓዝ ይሆን የሚል ስጋት ይጭናል:: ዴሞክራሲ በባህሪው ጭቅጭቅ ያለበት ቢሆንም የቀደመ ስዕል ይዞ አሁንም እዛው ላይ መንገፋደፍ የሃገሪቱ ዴሞክራሲ መዳበር ዕድል ላይም ጥያቄ ያጭራል:: ኢህአዴግ ለምርጫው ተዘጋጅቻለሁ ቢልም በርግጭም በዚህ ሁኔታ እንዴት ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ሀገራዊ ምርጫ ማካሄድ እንደሚቻል ብዙዎች ስጋት አላቸው:: የአብዛኛው ዕምነት ኢህአዴግ እችላለሁ ብሎ የሰጠው መግለጫ ገና መዋቅር ላይ ያለው ምርጫ ቦርድ ምርጫውን በጊዜው ለማካሄድ እንደማይሳካለት በማወቅ የፖለቲካ የበላይነት ለማግኘት ያደረገው የአስመሳይነት ቴክኒክ ነው የሚል ነው:: በርግጥስ እንደታሰበው ምርጫው በ2012 ሊካሄድ ይችል ይሆን?

**...በአፋኝ እና አፍራሽ አንቀጾች የተሞላው ረቂቅ አዋጅ ሳይሻሻል እንዳይፀድቅ አጥብቀን እንጠይቃለን" በሚል ርዕስ የወጣው የፓርቲዎቹ መግለጫ ከበድ ያሉና የፓርቲዎቹን የስሜት መነካት የሚያሳብቁ ቃላቶች የታጨቁበት ነው። "ሃገራችን ባለፉት 27 ዓመታት ውስብስብ የሆነ የሴራ ፖለቲካና በርካታ የግፍ ፅዋ ስትጨልጥ መቆየቷ አይዘነጋም...**

ፓርቲዎቹ ከዚህ ባሻገር በዋናነት የሚያነሱት ጥያቄ በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 4 ላይ የተዘረዘረው "የአብላጫ ድምጽ" አሸናፊነት ጉዳይ ነው:: በሕገመንግሥቱ መሠረት አንድ ፓርቲ 51 ድምጽ ካገኘ የአካባቢውን አሸናፊነት ይወስዳል:: ይህ አሰራር 49 ድምጽ ያላቸውን ፓርቲዎች ዜሮ እንዳገኙ ቆጥሮ የሚደፈጥጥ ነው የሚሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች በተገኘው ደምጽ መሠረት ሥልጣንን የመጋራት ጥያቄ ያነሳሉ:: ምክንያታቸው ደግሞ ያ 49 ድምጽ የሰጠው ህዝብ በማይፈልገው ፓርቲ መተዳደር የለበትም ከሚል መነሻ ነው::

በዚህ ጉዳይ ላይ የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ይህ ለውጥ ከመምጣቱ አስቀድሞ ለሁለት ዓመታት ሲከራከርበት ኖሮ ኢህአዴግም ተስማምቶና አሸናፊነትን በአብላጫ ከማድረግ ይልቅ በቅይጥ ለማድረግ ወስኖ ነበር::

ከዚህ ባሻገር ያለው ‹‹የመንግሥት ሰራተኞች በምርጫ ሲወዳደሩ ሥራ መልቀቅ አለባቸው›› የሚለው አዋጅ ቁጥር 10/46 አንድ የመንግሥት ሰራተኛ የምርጫ ተወዳዳሪ እጩ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ በጊዜያዊነት መልቀቅ አለበት ቢልም የቀድሞውም ይሁን የአሁኑ ሕግ የፖለቲካ ተሳትፎን ስለሚገድብ የዓመት ፍቃዳቸውን ተጠቅመው ደሞዛቸው ሳይነካ ምርጫ ላይ እንዲሳተፉ መወሰኑን፣ የዓመት እረፍት ካልበቃ ከሚቀጥለው አመት የሚታሰብ ወይም ከክፍያ ነጻ ፍቃድ እንዲያገኙና ሲሸነፉ መስሪያ ቤታቸው ተመልሰው የሚገባቸውን ጥቅም እንዲያገኙ በሚል መስተካከሉን ተናግሯል:: በአጠቃላይ ቅሬታ ከቀረበባቸው አንቀጾች መሃል አንቀጽ 31 ፣32 ፣64 ፣65 ፣100 ፣160 ወዘተ ላይ የቀረቡ ሃሳቦች ተካትተዋል ብሏል ምርጫ ቦርድ::

# የውጭ ግንኙነታችን ጥቅምና ጉዳትን ማስላት ካልቻለ አደጋው ከባድ ነው!

**አለማየሁ ባዘዘው**

ለዘመናት ሲነገር እንደቆየው ኢትዮጵያ የምትገኝበት የአፍሪካ ቀንድ ከባቢ ሁሌም ቢሆን የኃያላኑ አገራት ትኩረት ተነፍጎት አያውቅም፡፡ የምዕራቡና ምስራቁ ዓለም ኃያላን አካባቢውን በዓይነ ቁራኛ የሚጠብቁበትና ወቅታዊ ሁኔታዎችን በየዕለቱ እየገመገሙ አካሄዳቸውን የሚያስተካክሉበት የየራሳቸው ምክንያት ቢኖርም፤ በአካባቢው ላይ የሚፈጠር ለውጥ ከህልውናቸው ጋር የተያያዘ በመሆኑ ከባቢውን በትኩረት ከመቃኘት ለአፍታ እንኳ አይዘናጉም፡፡ የአካባቢው አገራት እንቅስቃሴ ከፍላጎታቸውና ከቁጥጥራቸው ውጪ እንዲሆንም አይፈቅዱም፡፡

ይህ ሁኔታ ለቀንዱ ሀገራት በተለይም ለሀገራችን ኢትዮጵያ፣ ጥቅምና ጉዳትን ያዘለ ነው፡፡ በአፍሪካ ቀንድ የተሻለ መረጋጋትና ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር፣ እንዲሁም ተጽዕኖ ፈጣሪ መንግሥትና ወታደራዊ ኃይል ያላት አገራችን ኢትዮጵያ ከሌሎች የአካባቢው ሀገራት በበለጠ በኃያላኑ ዓይን ሥር ሆና መቆየቷ በዚህ ምክንያት ቢሆንም በአፍሪካ ቀንድ ያላት ሁለንተናዊ የበላይነት ግን የጠቀሜታውን ያክል ጉዳት ያስከተለባት ሆኖ አያውቅም፡፡ ኃያላኑ በሚፈልጉትና በፈቀዱት መንገድ መጓዟ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ተጠቃሚ እንድትሆን የማገዙን ያህል ፤ ለኃያላኑ በሚጎረብጥ ጎዳና በተራመደች ቁጥር ለከፋ ችግርና ምስቅልቅል መዳረጓ አልቀረም፡፡ ይህን እውነታ በተጨባጭ ለማረጋገጥ ብዙ መጓዝ አይጠበቅም፡፡ የቀዳማዊ ኃ/ሥላሴን ንግሥና እና ውድቀት፣ የደርግ ሥርዓትን አመጣጥና የመጨረሻ ዕጣ፣ እንዲሁም የህወሓት/ኢሕአዴግን የ‹‹አሸናፊነት›› ታሪክ ማስታወስ ብቻ የኃያላኑ ተጽዕኖ የት ድረስ እንደሚለጠጥ ለማወቅ በቂ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ለዘመናት በቆየችባቸው የአገር አስተዳደር መርሆዎቿና የውጭ ግንኙነት ፖሊሲዎቿ፣ ከአካባቢውና ከአህጉሩ ሀገራት፣ ከምዕራቡና ምስራቁ ዓለም ኃያላን እንዲሁም ከመካከለኛውና ሩቅ ምስራቅ ወዳጆቿ ጋር የሚኖራትን ግንኙነት በሚመለከት ግልፅ በሆነ መርህ ላይ የተመሰረተ አቀጣጫን ስትከተል መኖሯ በብዙ መልኩ ተጠቃሚ አድርጓት መቆየቱን መታዘብ ይቻላል፡፡ በየጊዜው ከሚለዋወጠው የዓለም ኃይል አሰላለፍ ጋር ራሷን አስማምታ መቆየቷ እንደሀገር ለመቀጠል እንደረዳት መካድ አይቻልም፡፡ ከመስመሩ የመውጣት አዝማሚያ ባሳየችባቸው ወቅቶች ደግሞ የገጠማትን ችግርና የደረሰባትን ጉዳት አለማመንም ከታሪክ እውነታ ጋር ግጭት ከመፍጠር ውጪ ትርጉም የለውም፡፡

ይህን እውነታ አምነን ተቀብለን እንነጋገር ከተባለ የዛሬዋ ኢትዮጵያ ከትናንቱ የተለየች ሆና ነው የምናገኛት፡፡ በተለይም በዶ/ር ዐቢይ አህመድ የሚመራው አዲሱ የለውጥ መንግሥት በትረ ሥልጣኑን ከጨበጠ ወዲህ የአገራችን የውጭ ግንኙነት መልክ ትንሽ ግራ የሚያጋባ ይመስላል፡ ፡ የዓለምን ነባራዊ ሁኔታ የተረዳ ግልፅ አሰላለፍ የማይስተዋልበት ከመሆኑም ባሻገር ከሁሉም ጋር ወዳጅ ለመሆን የሚደረገው ጥረትም ከጥቅሙ በላቀ የሚያስከትለው አደጋ አሳሳቢ ነው፡፡

የዛሬይቱ ዓለም በብዙ ጎራዎች የተከፋፈለች ናት፡፡ በኃያሏ አሜሪካ ጎራ የተሰለፉት ምዕራባውያንና በእነ ቻይና ረድፍ የቆሙት ተቀናቃኞች ዓለምን በጎራ የተከፋፈለች አድርገዋታል፡፡ ከወዳጃችን ሳዑዲ አረቢያ ጎን የቆሙትና ከሌላኛዋ እየተወዳጀችን ካለችው ኳታር ጋር ያበሩት የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ለዓለማችን የጎራ ልዩነት ቀለማትን አበጅተውለታል፡፡ በአህጉራችንና በምንገኝበት የአፍሪካ ቀንድ ቀጠና ያሉ አገራትም የየራሳቸውን ጎራ አበጅተው እርስ በርስ የሚነታረኩ ናቸው፡፡ በዚህ መሀል ኢትዮጵያ እንዴት እና ከእነማን ጋር መራመድ እንዳለባት "አለማወቋ" ወይም መንገዷን የሚመራ ግልፅ የግንኙነት ፖሊሲዋን ይፋ አለማድረጓ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንዳያመዝን ስጋት ይጭራል፡፡

የዐቢይ መንግሥት የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ለማምጣትና የአገርን ህልውና ከአደጋ ለመጠበቅ ኃያሏ አሜሪካን መጠጋቱ ተጠባቂ ቢሆንም ቻይናን ከመሰሉ ሀገራት ጋር የፈጠረው ሁለንተናዊ ወዳጅነት ግን መንገዱን የተደላደለ እንዳያደርግለት ያሰጋል፡፡ ተራቁቶ የነበረ ካዝናችንን አርጥባ ከውድቀት አፋፍ ለመለሰችን ሳዑዲ አረቢያ ልባችንን ከፍተን "እንደፈቀድሽ ዋኚበት" ማለት ከውለታዋ አንፃር የሚበዛባት ባይሆንም "ጠላቴ" ብላ ጥርስ ከነከሰችባት ኳታር ጋር "እፍ ያለ ፍቅር ውስጥ መውደቅ" ግን መዘዙ በቀላል የሚመዘን ላይሆን ይችላል፡፡ ሰሞኑን የኳታሩ ልዑክ አዲስ አበባ በተገኙበት ዕለት የሳዑዲው አልጋወራሽ ለዶ/ር ዐቢይ ስልክ ስለመደወላቸው የተሰማው ጉዳይም ነገሩን በዋዛ እንድናልፈው አይጋብዝም፡፡

እርግጥ ነው ለዘመናት ተደጋግሞ ሲነገር እንደሰማነውና በተጨባጭም እንደምናየው "በፖለቲካ ዓለም ዘላቂ ጠላትም ሆነ ዘላቂ ወዳጅ የለም!" በዚህ ስሌት አሜሪካም ሆነች ሳዑዲ አረቢያ፣ ኳታርም ሆነች ቻይና ከጊዜው ጋር የሚወደዱና የሚጠሉ እንጂ ግንኙነታቸው በዘላለማዊ የማይሻር ፊርማ የታሰረ አለመሆኑን መረዳት አይገድም፡፡

ይህ ማለት በአንድ ጊዜ ከሁሉም ጋር ወዳጅ ወይም በተመሳሳይ ጊዜ ከሁሉም ጋር ባላጋራ መሆን ይቻላል ማለት ባይሆንም የኢትዮጵያችን ሁኔታ ግን እንደዚያ እየመሰለ ነው፡፡ ወዳጃችን አሜሪካ ለውጡ እንዳይቀለበስ ሁለንተናዊ ድጋፍ እያደረገችልን ስለመሆኗ ከተጨባጭ እገዛዎቿ እየተመለከትን ባለበት በአሁኑ ጊዜ የሩቅ ምስራቋ ቻይናም ከልብ መወዳጀታችንም አሌ የማይባል ሆኗል፡፡ የሚቹ ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ መንግሥት አሜሪካንን "በኒዮ ሊበራል" ወንጅሎ እያጣጣለ ከቻይና ጋር የመወዳጀት አዝማሚያ ይታይ በነበረበት የመጨረሻው ዘመን ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን አምጥቶ እንደነበር ብንታዘብም ጠ/ሚኒስትሩ እስከ ሞት ለደረሱበት አሳዛኝ ዕጣ ፈንታ የአሜሪካ እጅ የለበትም ብሎ ማሰብ ግን አይቻለንም፡፡ ለዚህ ጉዳይ ተጨባጭ ማስረጃ ማቅረብ ባንችልም ብርቱ ጥርጣሬያችንን መሸሸግ ግን አይሆንልንም፡፡

እናም አሁን ሁኔታዎች ፍፁም ግራ የሚያጋቡ ሆነዋል፡፡ የዶ/ር ዐቢይ መንግሥት ከሁሉም ጋር በፍቅር፣ በትብብር፣ በአጋርነትና በወዳጅነት ለመዝለቅ የጀመረው መንገድ እንደሰው ካሰብነው አንዳች ስህተት የሚገኝበት ባይሆንም የዓለም ነባራዊ ሁኔታ ግን ለዚህ ምቹ አይደለም፡፡ መንግሥታት ጎራቸውን መለየት፣ አሰላለፋቸውን ማሣመርና መንገዳቸውን የመምረጥ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን አምነው ይህን በግልፅ ለመተግበር የሚገደዱበት እንጂ ከሁሉም ጋር በፍቅር ‹‹እፍ›› ብለው መዝለቅ የሚችሉበት ምህዳር የለም፡፡ አሜሪካና ቻይናን በእኩል የሚያስተናግድ መንግሥታዊ ሳሎን ውሎ አድሮ ችግር ማስተናገዱ አይቀርም፡፡ ሳዑዲ አረቢያንና ኳታርን እኩል ልቀፍ የሚል ክንድ ‹‹ዛልኩኝ›› ብሎ ለመሰብሰብ እንጂ የፍቅሩን ጥልቀት ማረጋገጥ የሚችል አቅም አይኖረውም፡፡

ነገሩን በአህጉራዊ ንፍቀ-ክበብ ደረጃ እንመልከተው ካልንም ከአንዳንድ አገራት፣ በተለይም ከምሥራቅ አፍሪካ ተጋሪዎች ጋር የጀመርነው ግንኙነትም ከችግር የፀዳ ነው ብሎ መደምደም ይቸግራል፡፡ በ‹‹ግዛት ይገባኛል›› ሰበብ ጡንቻ ሲለካኩ የቆዩት ኤርትራ እና ባለወደቧ ጅቡቲ በኢትዮጵያ ግራና ቀኝ ክንዶች ታቅፈው በፍቅሯ ሙቀት እንደተማረኩ ይቆያሉ ማለት ተምኔታዊ ነው፡፡ ለሱዳን ሰላም እንቅልፍ አጥቶ በመባዘን ከግብፅ ጋር የተጀመረውን በንግግር ላይ የተመሰረተ ሠላማዊና መልካም ግንኙነት ማቆየት አይታሰብም፡፡ ሱማሊያና ኬኒያን በእኩል ፍቅር ማርኮ የነፍስ አባት ለመሆን መታተርም ‹‹ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ›› ነው፡፡ የዐቢይ መንግሥት ግን ይሄን የተረዳ አይመስልም፡፡ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲው ወጥነት ያለውና በግልፅ የሚታወቅ አለመሆኑ በራሱ ችግር ቢሆንም ከእግዜሩም ከሰይጣኑም በፍቅር ለመዝለቅ መሞከር ግን ፊፅሞ ክስረት ነው ፤ ሊያም አርስቶትል እንዳስቀመጠው ከአቅም በላይ ሽክም የፖለቲካ መዘረርን እንደሚያስከትል መረዳት ነው፡፡

አበው ሲተርቱ "ሁለት እግር አለኝ ተብሎ ሁለት ዛፍ አይወጣም" እንዲሉ የዐቢይ መንግሥት አሰላለፉን ማሳመር፣ የወዳጅነት ምስረታውም ጥቅምና ጉዳትን ባሰላ መልኩ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ አለዚያ ሳዑዲንም ኳታርንም ለማስደሰት መሞከር ቂም ከማስቋጠርና እልህ ውስጥ አስገብቶ አቅምን ለማሳወቅ ከማነሳሳት አይመለስም፡፡ የውጭ ግንኙነታችን ጥቅምና ጉዳትን በሚያሰላ ቀመር ላይ ተመስርቶ መጓዝ ካልቻለ አደጋው ከባድ ነው፡፡ ተጽዕኖውንም አሁን ያለችው ደካማዋ ኢትዮጵያ ልትቋቋመው አቅም ያላት አይመስልም፡፡

# “ጥራት ያለው ትምህርት፤ ለታላቅ ስኬት”

**አቶ ሞገስ ግርማ /የኮሌጁ ማኔጂንግ ዳይሬክተር/**

በ1995 ዓ.ም በከፍተኛ ትምህርት ሥልጠና ቦሌ አካባቢ በሚገኘው ሜጋ ሕንፃ ሳይ ሥራውን ጀመረ፡፡ በቀድሞው ሥርዓተ ትምህርት ከ10+1 እስከ 10+3፣ ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 4 ለአስር ዓመታት ያህል በዲፕሎማ መርሃ ግብር ብቻ ሲያሰለጥን ቆይቷል፡፡ በሂደት በኢትዮጵያ ከሚገኙ አንጋፋ የትምህርት ተቋማት መካከል አንዱ የሆነው ጌጅ ኮሌጅ፤ ከምስረታው ጀምሮ አሁን እስካለበት አጠቃላይ ሁኔታ ሲያወጉን የኮሌጁ ማኔጂንግ ዳይሬክተሩ አቶ ሞገስ ግርማ ጋር በዚህ መልክ ቆይታ አድርገናል፡፡



አቶ ሞገስ ግርማ

**ግዮን፡- ጌጅ ኮሌጅ ከ10 ዓመታት በኋላ ምን ደረጃ ላይ ደረሰ?**

አቶ ሞገስ፡- በነገራችን ላይ በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ መጠሪያ ስሙ “ጌጅ አይቲ ኮሌጅ” ነበር፡፡ ከዚያም የቢዝነስ ት/ት ክፍሎችን ማስተማር ስለጀመረ፣ “ጌጅ አይቲ ኤንድ ቢዝነስ ኮሌጅ” ተባለ፡፡ በ2005 ዓ.ም ደግሞ በዲግሪ ፕሮግራም ሲያሰለጥን “ጌጅ ኮሌጅ” ተብሎ አሁን ላይ ያለውን መጠሪያ ያዘ፡፡ ላለፉት ስድስት ዓመታት በኮምፒውተር ሳይንስ እና ቢዝነስ አድሚኒስትሬሽንን ጨምሮ በዘጠኝ የዲግሪ መርሃ ግብሮች እውቅናና ፈቃድ አለው፡፡ በ2009 ዓ.ም ደግሞ በማስተርስ ኦፍ አካውንቲንግ ኤንድ ፋይናንስ፣ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን እንዲሁም በ2010 በርቀት መርሃ ግብር በ5 የትምህርት ዘርፎች በማስተማር ላይ እንገኛለን፡፡ በአጠቃላይ ከPHD በስተቀር በዲፕሎማ፣ በዲግሪና በማስተርስ ፕሮግራሞች በቀን፣ በማታና በርቀት ትምህርት እየሰጠን ነው፡፡

**ግዮን፡- ምን ያህል ተማሪዎች አሏችሁ? ለስንት ሠራተኞችስ የሥራ ዕድል ፈጠራችሁ?**

አቶ ሞገስ፡- በ2002 ዓ.ም የተማሪዎች ቁጥር 120 ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ ከ30 ሺህ በላይ ደርሷል፡፡ አሁን ላይ በጠቅላላው ከ1500 በላይ ሠራተኞች አሉን፡፡

**ግዮን፡- የሠራተኞቻችሁን አቅም ለማሳደግ ምን እያደረጋችሁ ነው?**

አቶ ሞገስ፡- “ስታፍ ዴቨሎፕመንት” አለን፤ ይህ “ስታፍ” የሠራተኞችን ብቃት በማሳደግ ላይ ይሠራል፡፡ ለምሳሌ ዲፕሎማ ያላቸው ወደ ዲግሪ፣ ዲግሪ የያዙትን ወደ ማስተርስ፣ ማስተርስ ያላቸውን ደግሞ ወደ “ፒኤችዲ” እንዲያሳድጉት በማበረታት እና በማገዝ፣ የገቢ ምንጫቸውንም በማሳደግ ተፎካካሪ እንዲሆኑ ከፍተኛ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

**ግዮን፡- ለምን ያህል ተማሪዎች የትምህርት ዕድል ሰጥታችኋል?**

አቶ ሞገስ፡- በየዓመቱ የተማሪዎቹ ቁጥር ይለዋወጣል፡፡ ለምሳሌ ያህል በ2010 ዓ.ም 4500 ተማሪዎችን ስናስመርቅ 420ዎቹ ስኮላርሺፕ የተሰጣቸው ናቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ 100 ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ነፃ የት/ት ዕድል ያገኙ ሲሆን፣ 320ዎቹ ግማሽ የት/ት ዕድል የተሰጣቸው ናቸው፡፡ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ተማሪዎች ደግሞ ከ30 እስከ 40 በመቶ ቅናሽ ተደርጎላቸዋል፡፡

በ2011 ዓ.ም ካስረመቅናቸው 6554 ተማሪዎች መካከል 1800 የሚሆኑት የስኮላርሺፕ ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ እነዚህን ተማሪዎች በማገዛችን የምንደሰትበት፣ የምንኮራበት፣ ማህበራዊ ግዴታችንን እንደተወጣን አድርገን የምናስብበት፣ አንድ ቁምነገር ለሀገራችን እንደሰራን የምንቆጥርበት ነው፡፡

**ግዮን፡- “ጌጅ ኮሌጅ” የሚለውን መጠሪያ እንዴት አስቀጠላችሁት?**

አቶ ሞገስ፡- በርከት ያሉ ዓመታትን ሲሠራ የቆየ ተቋም በመሆኑ ሌላ አዲስ ስያሜ መሰየም ሳያስፈልገን፤ “GAGE” የሚለውን አህፅሮተ ቃል በመቀየር፣ “ግሬት አቺቭመንት ዊዝ ጉድ ኢዱኬሽን” ወይም ከመግቢያችን ላይ እንደ መሪ ቃል በወሰድነው “ጥራት ያለው ትምህርት ለታላቅ ስኬት” ብለነዋል፡፡

**ግዮን፡- ጌጅ ኮሌጅ በጥናት እና ምርምሩ ዘርፍ ምን ያህል ተጉዟል?**

አቶ ሞገስ፡- ብዙ ይቀረናል፡፡ ቢሆንም ግን እየሠራን ነው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ በሀገር አቀፍ ደረጃ ብሔራዊ ኮንፍረንስ ነሐሴ 18 ቀን 2012 ዓ.ም እናካሂዳለን፡ ፡ በኮንፈረንሱ የሚቀርበው ጥናታዊ ጽሑፍ ሀገራዊ ፋይዳ ያለው፣ ሥራ ፈጠራን የሚያበረታታ፣ እንደ ሀገር ህዝብን እያሳተፈ ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው፡፡ አነስተኛ ሆነው ወደ ተግባር የሚለወጡ ጥናታዊ ጽሑፎች እና ሴሚናሮች በሲዲ በመስራት ለማሳተፍ ተሞክሯል፡፡ በርካታ ጥናታዊ ጽሑፎችን አወዳድረን፣ ስድስት ያህሉን መርጠን ለውይይቱ አቅርበናል፡፡ እነዚህ ችግር ፈቺ የሆኑ የምርምር ፕሮጀክቶች ለሀገራችን አንድ ፋይዳ፣ ተቋማችንንም ለትልቅ ስኬትና ስም ያበቃሉ ብለን እናስባለን፡፡

**ግዮን፡- ከሌሎች ዩኒቨርስቲዎች ጋር ያለው ግንኙነት እና አብሮ የመስራት ሁኔታስ እንዴት ነው?**

አቶ ሞገስ፡- በሀገር ውስጥ እና እና ከሀገር ውጪ ካሉ ዩኒቨርስቲዎች ጋር የልምድ ልውውጦችን በማድረግ እየጠቀመ እና እየተጠቀመ ነው፡፡ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጋር በተወሰነ ደረጃ በመሥራት ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች “በኢንዲቪጁዋል ሌቭል” እየረዳናቸው እንገኛለን፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቤተ መጽሐፍት እና ጆርናል ከመጠቀም አንፃር ሰብስክራይብ አድርገን እየሰራን ነው፡፡

በአሜሪካን ሀገር በ1818 የተቋቋመው “ዩታ ስቴት ዩኒቨርስቲ” ከሚባል ትልቅ የመንግስት አንጋፋ ዩኒቨርስቲ ጋር በአራት ዘርፎች ለመሥራት ተስማምተናል፡፡ በመማር ማስተማር፣ በሪሰርች፣ በልምድ ልውውጥ፣ በስታፍ ኤክስቼንጅ እንዲሁም ከተማሪዎች ጋር በተያያዘ በጋራ ለመሥራት በ2018 G.C ተፈራርመናል፡፡ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ግንኙነታችን በጣም እያደገ ከመጣ ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንደርሳለን ብለን እናምናለን፡፡

ከኦገስት 25—26 G.C የሕንድ መንግስት በ “ኒውደልሂ” አፍሪካን ኢንዲያ ሀያ ኤዲኬሽን ሰሚት፣ በሕንድ እና አፍሪካ መካከል ያሉ ዩኒቨርስቲዎችን የልምድ ልውውጥ እና በጋራ መስራት እንዲችል ያመቻቻል፡፡

**ግዮን፡- የጌጅ ኮሌጅ ዕቅድ እና ራዕይ ምንድነው?**

አቶ ሞገስ፡- በቴክኖሎጂ እና ቢዝነስ የሙያ ዘርፎች ዓለም አቀፍ ተፎካካሪ መሆን፤ ተማሪዎቻችንን በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ማድረግ፤ ብቃት ያላቸው መምህራንን እና ሠራተኞችን መፍጠር፣ ሕብረተሰቡን በቅንነት እና በታማኝነት ማገልገል እንዲሁም በራሳቸው የሚተማመኑ እና የሥራ ፈጠራን ባህላቸው ያደረጉ ብቁ ዜጎችን ማፍራት ዓላማችን ነው፡፡

**ግዮን፡- ስለ ግል ተሞክርዎ ቢያጫውቱን?**

አቶ ሞገስ፡- በ1987 ዓ.ም ዩኒቨርስቲ ገባሁ፤ በ1990 ዓ.ም ተቀጥሬ ሥራ ጀመርኩ፡፡ አስራ ሁለተኛ እና ከዚያ በታች የክፍል ደረጃ ያላቸውን ሕፃናት ቤት ለቤት አስጠና ነበር፡፡ እውቀትን ከማካፈል እና ገንዘብ ከማግኘት አንፃር ጥሩ ነበር፡፡ ረጅም ጊዜ በማስተማር ቆይቻለሁ፡፡ “አካዳሚክ ወርልድ” ላይ ጥሩ ግንዛቤ ያገኘሁ ይመስለኛል፡፡ ያም ቢሆን ብዙ እንደሚቀረኝ አስባለሁ፡፡ እኔ የተፈጠርኩት፣ እግዚአብሔርም የፈቀደልኝ የምወደው ሙያዬ ማስተማር በመሆኑ ትልቁ ፀጋዬ ነው ማለት እችላለሁ፡፡

**ግዮን፡- ኮሌጃችሁ ተማሪዎችን አስመርቆ ሥራ ከመፍጠር አኳያ ምን አድርጓል?**

አቶ ሞገስ፡- አብዛኞቹ ተማሪዎቻችን በሥራ ላይ ያሉ የመንግሥት ሠራተኞች፣ ሚሊተሪ ፖሊሶች የመከላከያ ሠራዊት አባላት እና ሌሎችም በመሆናቸው የት/ት ደረጃቸውን የሚያሻሽሉ ናቸው፡፡ የተቀሩት ተማሪዎች ከ10ኛ እና 12 ክፍል ለሚመጡ እና ለምናስመርቃቸው ደግሞ ከሌሎች የተለያዩ ተቋማት ጋር በመነጋገር የሥራ ዕድል እንዲያገኙ እያደረግን እንገኛለን፡፡

**ግዮን፡-እናመሰግናለን፡፡**

# ማገጣበር - አገር አቀፍ ችግር

በዚህ ዓመት ማለትም በ2011ዓ.ም ከመንግሥት ዩኒቨርስቲዎች ከ130 ሺ.ህ በላይ ከግል ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ከ50ሺ.ህ የማያንሱ ተማሪዎች ተመርቀዋል፤፤ በልዩ ልዩ የሥራ መስኮች ነገ የሚሰማሩት እነሱ ናቸው፤፤ እነሱን ለዚህ ቦታ የሚያዘጋጁት በታችኛው የትምህርት እርከኖች ላይ የሚገኙት ትምህርት ቤቶችና መምህራን ናቸው። የእያንዳንዱ ተማሪና መምህር እንዲሁም የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ሕይወት ቢዳሰስ ተዘርዝሮ የማያልቅ ታሪክ እና ልምድ ሊገኝበት እንደሚችል ይታመናል።

በአዲስ አበባ የሚገኙ ሃያ  የሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች መምህራንና ርዕሰ መምህራን ሐምሌ 12 ቀን 2011 ዓ.ም በሞናሞ ሆቴል ተሰብስበው የልምድ ልውውጥ አድርገዋል። በኢትዮጵያ ከሚገኘው የቼክ ሪፐብሊክ ኢምባሲ ጋር በመሆን ፕሮግራሙን ያዘጋጀው መንግሥታዊ ድርጅት ያልሆነው ኢንሼስቲብ አፍሪካ ሲሆን የኤምባሲው ተወካይ ቤዛዊት አድማሱ በቦታው ተገኝተው ሂደቱን ተከታትለዋል። የልምድ መለዋወጫው ዋና ጉዳይ ደግሞ ‹‹ማገጣበር›› ነበር።

‹‹ማገጣበር›› ምንድን ነው? ማጋጠበር ብዙ የተለመደ ቃል አይደለም፡ ፡ የእንግሊዘኛውን ‹‹bulling›› በመተካት እንዲያገለግል ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው። ቀደም ባሉት ዓመታት  ጉልቤ፤ ትንኮሳ ወይም ጥቃት የሚሉ ቃሎች ነበሩ፤፤ ጉዳዩን ስፋት በትክክል እየገለጡት ነው ለማለት የሚያስችል ሆኖ አልተገኘም። ለምሳሌ ጥቃት ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውለው ከወሲብ ጋር በተያያዘው ነው። ‹‹ማገጣበር›› ስንል ግን በአካላዊ እንቅስቃሴ አሊያም በጉልበት አንድ ተማሪ ላይ የሚፈፀምን ዘለፋ፤ ማንቋሸሽ፤ ማብሸቅ፤ የቅፅል ስም ማውጣት፣ ድብደባና አንድን ልጅ እየተጠቃቀሱ መሳለቂያ ማድረግ የመሳሰለውን ለመግለጽ ነው።

አንዳንድ ት/ቤቶች ሕግና ደንብ አዘጋጅተው በተማሪዎቻቸው ላይ የሚፈፀመውን ማገጣበር ለመከላከል ከተቻለም ለማስወገድ እየሰሩ መሆኑን፤ ማገጣበር በሁለቱም ጾታዎች ላይ የሚፈጸም ቢሆንም የሚበዛው ግን በሴት ተማሪዎች ላይ መሆኑን ከኢኒሽየቲብ አፍሪካ አቶ የኒላሽት ገብረሚካኤል ገልጸዋል። ማገጣበር እንደተራ ጉዳይ ሊታለፍ እንደማይገባ በአፅንኦት የተናገሩት አቶ የኒላሽት ችግሩ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ለዘለቄታ ሊቆይ የሚችል ችግር ሊፈጥር እንደሚችል  አስገንዝበዋል።

“በየትምህርት ቤቱ ተዘዋውረን ጉብኝት ባደረግንበት ጊዜ በግቢያችን ሲጋራ አይጤስም ብለው ያረጋገጡልን ት/ቤቶች ነበሩ። ተማሪዎችን ነጥለን ስንጠይቃቸው ግን ሲጋራ እንደማይጨስ ሆኖም ግን ‹ኦሪስ› የተባለ እንደሲጋራ እየተጠቀለለ የሚጨስ ነገር መኖሩን ነግረውናል” ያሉት አቶ የኒላሽት አስተዳደሩ የሚሸፍናቸውን አንዳንድ ጉዳዮች  ተማሪዎች ሊያጋልጧቸው እንደሚችሉ አስረድተዋል።

የልምድ ልውውጥ ተሳታፊዎቹ ‹ኦሪስ› ሱስ የሚያሲዝ መሆኑን፤ በትምህርት ቤቱም ይህንኑ በማሰራጨት ተግባር ላይ የተደራጁ ክፍሎች መኖራቸውንና፤ የግብይት መስመሩ እስከ ደብረዘይት የተዘረጋ መሆኑን ገልጸዋል። የቦሌ መሰናዶ ት/ቤት ርዕሰ መምህር አቶ ዳንኤል መኮንን ‹‹ለፅኑ ህሙማን በሐኪም ትዕዛዝ መሸጥ ያለበት ‹ትራማዶል ዶናዶል› የተባለ መድኃኒት በየፋርማሲው እንደ ተራ ነገር እየተሸጠና ተማሪዎች እየተጠቀሙበት ነው›› በማለት ራሳቸውን እስከመሳት እንደሚያደርሳቸው በማስረዳት የምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን በጉዳዩ ላይ ሊያስብበት እንደሚገባ አመልክተዋል። በአንድ ሴት ተማሪያቸው ላይ የተፈፀመውን የማገጠባር ድርጊት የገለጡት ሌላኛው ርዕሰ መምህር ደግሞ “ልጅቱ ክፍል ውስጥ የምትቀመጠው ከፊት ነው። ከኋላ ሦስት ወንዶች አሉ። በትምህርት ሰዓት ይጎነትሏታል፣ ይቆነጥጧታል፤፤ ሦስቱም ልጆች ደብተራቸውን ሰጥተዋታል እሷንም እነሱንም የምትጽፈው እሷ ናት። ሦስቱም ክብረ ንፅህናሽን የምትሰጪው ለማን ነው? እያሉ ይጠይቋታል፣ ያስጨንቋታል፤፤ እንዲያውም አንደኛው በስሙ የባንክ ሂሳብ ከፍቶ በዚያ ሂሳብ ገንዘብ እንድታስገባ ጭምር ያስገድዳት ነበር። የልጆቹን የቤተሰብ ታሪክ ስናጠና የአንደኛው እናት አረብ ሀገር ሄዳለች፤ ገንዘብ ይላክለታል። የሁለተኛው እናት ተደፍራ አርግዛ የወለደችው ነው። የሦስተኛው ደግሞ እናቱ ሁል ጊዜ ስለምትደበድበው ሴት በጣም የሚጠላ መሆኑን ነው የደረስንበት” በማለት በ ብዙ ጥረት ተመሪዎቹ ወደ መልካም ምግባር መመለሳቸውን አስረድተዋል።

በተማሪዎች ላይ የማገጣበር ድርጊት የሚፈፀመው ከቤት ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱና ሲመለሱ እንዲሁም ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ መሆኑን በተሰብሳቢዎች በተደጋጋሚ ተወስቷል። ትምህርት ሚኒስትር አገር አቀፍ ችግርነቱን በማመን እና በመቀበል ለየትምህርት ቤቱ መመሪያ ማስተላለፉ በመድረኩ ተመልክቷል። ውይይቱ የተቋጨው አንዳንድ ትምህርት ቤቶች በት/ቤት የጥቃት መጠን መመዘኛ (Index) ተግባራዊ እያደረጉ  መሆናቸውን ከግምት በማስገባት ችግሩን ለመግታት የመምህራን ሚና ከፍተኛ መሆኑ ላይ መግባባት በመፍጠር ነው።

# “ስንት አስጫርህ?”



በአያሌው አስረስ

ከኢንሼቲብ አፍሪካ ጋር ባለኝ የሥራ ግንኙነት ለሁለት ቀናት በአምቦ ከተማ ቆይታ አድርጌ ነበር። ‹‹ኢንሼቲብ አፍሪካ›› ከሚሠራቸው ተግባራት አንዱ የሴቶች ጉዳይ ነው። በተለይም ደግሞ በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ልዩ ልዩ ጥቃቶች እንዲቀንሱ ቀስ በቀስም እንዲጠፉ የበኩሉን ሚና ይጫወታል።

በቆይታዬ መጀመሪያ ላይ ያገኘሁት በአምቦ ከተማ  አስተዳደር ፖሊስ መምሪያ፤ የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ አስፈፃሚ እንስፔክተር የሺ አሰፋን ነው፡ ፡ ኢንስፔክተር የሺ 2006 ዓ.ም ጀምሮ በዚህ ኃላፊነት ላይ ሠርተዋል፤፤ በቆይታቸው የተገነዘቡት በደል የተፈጸመባቸው ወገኖች ወደ አደባባይ እየወጡ የሕግ ድጋፍ የማግኘት ፍላጎታቸው እያደገ መምጣቱንና በአንፃሩም ቀደም ሲል የነበረው የጥቃት ብዛት እየቀነሰ መምጣቱን ነው።

“በሴት መደፈር ወንጀል ተጠያቂ የሚሆኑ ሰዎች አንድም ጊዜ ጥፋተኛነታቸውን አምነው ሲጸጸቱ አጋጥሞኝ አያውቅም፤ ክደው ነው የሚከራከሩት“ የሚሉት ኢንስፔክተር የሺ፣ ክፍላቸው ከመዘገባቸው አስር አስገድዶ መድፈር ወንጀሎች፡ ሰባቱ ውሳኔ ማግኘታቸውን፤ ሁለቱ ተበዳዮች ጥቃት ከአደረሱባቸው ወንዶች ጋር ተስማምተው መጥፋታቸውን፤ አንደኛዋ ተበዳይ ግን ክሱን የመሠረተው ቤተሰቧ ስለነበረ እሷ ደግሞ ጥፋተኛው እንዳይያዝ ስለፈለገች እንዲጠፋ ማድረጓንና ግለሰቡ እየተፈለገ መሆኑን አስረድተዋል። በተጨማሪም የሚያሳድጋትን የአስራ አንድ አመት ልጅ የደፈረው አባወራ የአስራ የአንድ ልጅ አባት ሲሆን አሁን በእስር ላይ እንደሚገኝ ጠቁመው፡ የአምቦ ዩኒቨርስቲ ተማሪዋን የደፈረው የመከላከያ ሠራዊት አባል ተፈርዶበት በእስር ላይ እንደሚገኝ አሳውቀዋል። በአሳዳጊዋ የተደፈረች ሕፃንና በመከላከያ ሠራዊት አባል የተደፈረችው ተማሪ ጉዳይ ልባቸው በሐዘን እንደሰበረው የሚያስታውሱት ኢንስፔክተር የሺ ከአቃቤ ሕግና ከአምቦ ሪፈራል ሆስፒታል ጋር በቅርበት ስለሚሠሩ ጉዳዩን ወደ ሕግ ደርሶ ውሳኔ ለማሰጠት ችግር አለመኖሩን አረጋግጠዋል።

በአምቦ ዩኒቨርስቲ የሴቶች ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ዳሬክተር ሲስተር የሺ ተረፈ በበኩላቸው፤ የመከላከያ ሰራዊት አሉና ተባባሪው 24 ዓመት ተፈርዶባቸው አምቦ ማረሚያ ቤት እንደሚገኙ ገልጠዋል።

ቢሮዋቸው በዩንቨርስቲው ውስጥ በሚገኙ ሴት ተማሪዎች፣ ሴት መምህራንና ሴት የአስተዳደር ሠራተኞች ዙሪያ እንደሚሠራ ጠቁመው፡ አንድ መምህር የተማሪውን ውጤት ለመግለጽ ባለመፈለግ ውጤት የላትም (no grade) እያለ ሪፖርት በማድረጉ፤ በፈጸመው የፆታ ትንኮሳ ወንጀል የአስተዳደር እርምጃ እንደተወሰደበትና ሊያገኝ የሚገባውን እድገት እንዲሁም የትምህርት ዕድል እንዲያጣ መደረጉን አሳውቀዋል።

ክፍላቸው በሥነ ተዋልዶ በፆታዊ ጥቃት በተደጋጋሚ ሥልጠናና ትምህርት እንደሚሰጥ የጠቆሙት ሲስተር የሺ በተለይ ለ1600 የአንደኛ ዓመት ተማሪዎች ፆታዊ ጥቃትን እንዴት መከላከል እንደሚችሉ ግንዛቤ እንዲይዙ መደረጉን አሳውቀዋል። ሲስተር የሺ አንዳንድ ተማሪዎች የዩንቨርስቲ መግቢያ ነጥብ አግኝተው ቢገቡም በዩኒቨርስቲው እንቆያለን የሚል ዕምነት ስለሌላቸው የሚያስቡት ከዩኒቨርስቲው የሚወጡበትን ጊዜ መሆኑን ጠቁመው ሌሎች ደግሞ ቀድመው ዩኒቨርስቲ በገቡ የየአካባቢያቸው ተማሪዎች ለአደጋ እንደሚጋለጡ አስረድተዋል። “አዲስ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርስቲው በሚመጡበት ጊዜ በተለይ ለሴቶች ልዩ ዝግጅት አድርገን እናወያያቸዋለን። መምህራንና አስተዳደር ሠራተኞች የሕይወት ተሞክሮአቸውን እንዲነግሯቸው እናደርጋለን። ይሁን እንጂ ቀድመው የገቡ የአካባቢያቸው ልጆች ካሉ ወደ እነሱ ያዘነብላሉ። ወደድኩሽ በማለት ከትምህርታቸው እንዲዘናጉ ያደርጓቸዋል። ጊዜያቸውን ከእነሱ ጋር ያባክናሉ። ሳይዘጋጁ የፈተና ጊዜ ይደርሳል። በዩኒቨርስቲው የሚይቆያቸው ውጤት ማምጣት ያቅታቸዋል። ዩኒቨርስቲውም ያባርራቸዋል።›› በማለትም ነገሩን አስረድተዋል።

ሲስተር የሺ በሴት ተማሪዎች ላይ በልዩ ልዩ መንገድ የሚደርሱ ትንኮሳዎችን ለማስቀረት ዩኒቨርስቲው የተማሪዎችን መታወቂያ ዘመናዊ ማድረጉን፣ ከግቢ ወጥተው ሲገቡ መታወቂያቸውን የሚያነበው ሰው ሳይሆን መሣሪያ (ሴንሰር) እንዲሆን መደረጉን ገልጸዋል።

በትምህርት ተቋሙ ያነጋገርኳቸው የዩኒቨርስቲው ሴት ተማሪዎች የገለጹልኝ ግን ቢሮው ስለመኖሩ እንኳን እንደማያውቁ ሲሆን፤ ማርታ (የአባቷን ስም መናገር አልፈለገችም) የተባለች ተማሪ ከሁለት ቀን በፊት አንድ ጓደኛዋ በራፍ ላይ ጨቤ በያዙ ልጆች ተንቀሳቃሽ ስልኳን መነጠቋን ተናግራለች።  ሴት ተማሪዎች ቢሮው ስለመኖሩ አናውቅም እያሉ ነው ብዬ የጠየቅኳቸው ሲስተር የሺ፣ ወደ ቢሮ የሚመጡት ጉዳይ ያላቸው ተማሪዎች መሆናቸውን በመግለጽ፤ ቢሮው ውሱንነቶች ስላሉበት ሁሌም በተፈለገው መጠን ወደ ተማሪዎች ለመድረስ ያለመቻሉን ገልጸውልኛል። በ2011ዓ.ም አምቦ ዩኒቨርስቲ ከመጀመሪያ እስከ ሦስተኛ ድግሪ በልዩ ልዩ የትምህርት መስኮች 19,864 ሴቶችን ሲያስተምር መቆየቱን ለማወቅ ተችሏል።

# ሰሞነኛው የሱዳን አክራሞት

“በባለፈው መራራ ዘመን ላይ አዲስ ምዕራፍ ከፍተን መጪውን መመልከት የምንችልበት ቀን እንዲሆን ለእያንዳንዳችሁ ጥሪ አቀርባለሁ፡፡” ***መሐመድ ሀምዳን ዳጋሎ***

“መጪው ጊዜ ማንም የማይገለልበት ስለመሆኑ መፈተሻ ነው” ***ሳዲቅ አልማህዲ***

**ጌኖክ ገለታው**

ባሳለፍነው ቅዳሜ በሱዳን ዋና መዲና ካርቱም በወታደራዊ ም/ቤቱና በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ህብረት መካከል የተደረሰው ስምምት አፍሪካን ማዕከል አድርገው የሚጽፉ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ሚዲያዎች ትኩረት ሆኖ ሰንብቷል፡፡ ሁለቱ የሀገሪቱ ኃይሎች በእኩል ድርሻ መወሰን የሚችሉበት ጥምር የሽግግር መንግሥት በማቋቋም ያስቀመጡትን ፊርማ ተከትም በአስር ሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በዋና ከተማዋ አደባባይ በመውጣት የድጋፍ ደስታቸውን ገልፀዋል፡፡

በነጮቹ ታህሳስ 19 2018 በተለያዩ የሱዳን ከተሞች እየከፋ የመጣውን የኑሮ ውድነትና የኢኮኖሚ ቀውስን መነሻ አድርጎ የተጀመረው የሱዳናውያን የአደባባይ ተቃዋሞ በጥር 2019 ፖለቲካዊ መልክ በመያዝ የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ኦማር አልበሽርን ከሥልጣናቸው እንዲነሱ ለወራት ጠይቋል፡፡ በሚያዝያ 11 የሐገሪቱ መከላከያ ኦማር አልበሽርን ለተከታታይ ሠላሳ ዓመታት ከተቆናጠጡት ዙፋን በማንሳት ካቢኒያቸውንና ብሔራዊ ሕግ አውጪውን አካል ከሥራ በማገድ የሶስት ወራት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጆ ነበር፡፡ የመከላከያ ሚኒስትርና የሀገሪቱ ምክትል ፕሬዚዳንት የነበሩት ሌ/ጀነራል አህመድ አዋድ እብን ኡፍ የሀገሪቱ ሕገ መንግሥት መታገዱንና ርዕሰ ብሔር መሆናቸውን ይፋ ባደረጉ ሰዓታት ውስጥ ግን ሱዳናዊያን ተቃውሟቸውን በአደባባይ መግለጻቸውን ቀጠሉ፡፡ ይህን ተከትሎም ሌ/ጀነራል አብዱልፈታህ አብደልረህማን ቡርሃን የወታደራዊ ም/ቤቱ ተጠሪ በመሆኑ ከሲቪል አስተዳደር ጋር መንግሥቱን ለመምራት መስማማታቸውን ገለፁ፡፡

የአፍሪካ ሕብረትና የኢትዮጵያ ሚና ትልቅ ነበር ተብሎ በተነገረለት ያለፉት ወራት የሱዳን ወታደራዊ ም/ቤትና ተቃዋሚ ሲቪል የፖለቲካ ኃይሎችን የማሸማገል ሂደት ፍሬ አፍርቶ ያለፈው ቅዳሜ የስምምነት ፊርማ ሊያስቀምጡ በቅተዋል፡፡ ለሱዳናውያን ትልቅ ታሪክ ተደርጎ በተወሰደው በዚህ የፊርማ ሥነ ሥርዓት ላይ የኢትዮጵያው ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ፣ የኬኒያው ኡምሩ ኬንያታ፣ የደቡብ ሱዳኑ ሳልቫኪር፣ የቻዱ ኢድሪስ ዴቤ ኢንቶ፣ የአፍሪካ ሕብረት ሊቀ መንበር ሙሳፋቂ ማህማት የታደሙ ሲሆን ስለ ሱዳን ሰላማዊ ሽግግር ሌ/ጄ አብዱራህማን ቡርሃን አስመራ ድረስ ማቅናታቸውን ተከትሎ የኤርትራ ተወካይ ግን በመድረኩ አለመገኘቱ መነጋገሪያ ሆኖ ነበር፡፡

በስምምነቱ ሁነት ላይ ፊርማቸውን ያኖሩት ከሱዳን ከፍተኛ የጦር ጄነራሎች አንዱ የሆኑትና የወታደራዊ ም/ቤቱ ምክትል ተጠሪ የሆኑት መሐመድ ሐምዳን ደጋሎ እና የተቃዋሚዎች ህብረቱ ተወካይ አህመድ አል ራቢ በለስላሳ የኦርኬስትራ ሙዚቃ እዜተወዛወዙ ጽዋቸውን ለደስታ ከማንሳታቸው በፊት ንግግር አድርዋል፡፡ መሐመድ ሐምዳም ፊርማውን ተከትሎ ባደረጉት ንግግር ‹‹ በባለፈው መራራ ዘመን ላይ አዲስ ምዕራፍ ከፍተን መጪውን መመልከት የምንችልበት ቀን እንደሆነ ለእያዳንዳችሁ ጥሪ አቀርባለሁ ›› በማለት ሀገሪቷን ወደተሻለ የዴሞክራሲ እርከን ለማሻገር ቁርጠኛ መሆናቸው ሲናገሩ በአንፃሩ ግን በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለመጨረሻ ጊዜ የተመረጡ ሰው ስለመሆናቸው የሚነገርላቸው ከተቃዋሚ ህብረቱ ተወካዮች አንዱ የሆኑት ሳዲቅ አልማህዲ ‹‹ መጪው ጊዜ ማንም የማይገለልበት ስለመሆኑ መፈተሻ ነው ›› በማለት ነገሮችን በኃላፊነት ስሜት መምራጽ ከሁሉም እንደሚጠበቅ አሳስበዋል፡፡

በመድረኩ ላይ አሁን በሥልጣን ላይ ባለው የወታደራዊ ም/ቤት የሥልጣን ዘመን በተለይም ደግሞ ከሁለት ወራት በፊት በሰኔ ሦስት ‹‹ ወታደራዊ ኃይሉ ሥልጣኑን ለሲቪል አስተዳደር ያስረክብ ›› በማለት በዋና ከተማዋ ካርቱም ለተቃውሞ በወጡ ሱዳናውያን ላይ ለደረሰው ግድያ በአስቸኳይ ማጣራትና ምርመራ ተካሂዶ ግድያውን የፈፀሙ አካላት ተጠያቂ እንዲሆኑ የነፃነትና የለውጥ ኃይሎች ህብረት (FFC) መሪ የሆኑት መሐመድ ናጊ አልሳም በምሬት ጠይቀዋል፡፡

በዚህ የቅዳሜው ሁነት ላይ ከሁለቱም ወገን የተውጣጣ አምስት አባላት ያሉት ዋና ም/ቤት የተቋቋመ ሲሆን ሦስት መቶ አባላት ያሉት የሕግ አውጪ ጉባዔ ምሁራንና ሙያተኞችን ባካተተ መልኩ በሽግግር ዘመኑ እንደሚዋቀርም ተገልጿል፡፡ የአዲሱ የሽግግር መንግሥት ትልቅ ተግዳሮት ይሆናል ተብሎ የሚጠበቀውን የሐገሪቱ የኢኮኖሚ ቀውስ፤ የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ከመቅረፍ አንስቶ በርካታ ተግባራት በማከናወን ሱዳንን የተረጋጋች ሀገር ከማድረግ ያልተናነሰ ሥራ መስራት እንደሚጠበቅበት ተጠቅሷል፡፡

በመድረኩ የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ መልዕክት ያስተላለፉ ሲሆን ሱዳናውያን ሰላማቸውን ከመቼውም ጊዜ በላይ በመጠበቅ ዴሞክራሲን እንደገነቡ ጥሪ አቅርበዋል፡፡ ሁለቱን ወገኖች በማሸማገል ሂደት መሪ የነበሩት በሱዳን የኢትዮጵያ አምባሳደር ሙሀመድ ድሪር በበኩላቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በሂደቱ ትልቅ ሚና እንደተጫወቱ በመግለጽ ሱዳናውያን የተሳካ የሽግግር ዘመን እንደሆነላቸው ጥሪቱ እንደሚቀጥል ተናግረዋል፡፡ በመድረኩ ላይ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ሥም ተጠቅሶ ሲመሰገኑና የአዳራሹ ታዳሚም ከመቀመጫው ተነስቶ ድጋፉን ሲገልጽ በሹዳን ቴሌቭዥን ጣቢያዎች ታይቷል፡፡

ከፊርማው ሥነ ሥርዓት ጎንለጎን የቀድሞው የተባበሩት መንግሥታት የምጣኔ ሀብት ባለሙያ አብደላ ሀምዶክ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር፤ የተቃዋሚ ድርጅት መሪው መሐመድ አልሃፍዚ መሐመድ ዋና ዓቃቤ ሕግ(public prosecutor) እንዲሁም አብዱልቃድር ሙሐመድ የፍትህ ዘርፍ ዋና ተጠሪ ሊሆኑ እንደሚችሉ የተለያዩ መገናኛ ብዙኀን በመዘገብ ላይ ናቸው፡፤ የፊርማውን ሂደት ተከትሎ በአስር ሺህዎች የሚቆጠሩ ሱዳናውያን በካርቱም አደባባዮች በመውጣት ከአልበሽር መንግሥት መውደቅ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ የድጋፍ ሰልፍ አድርገዋል፡፡



ጠ/ሚኒስትር አብይ ካርቱም ሲደርሱ የተደረገላቸው አቀባበል

# "ኢትዮጵያን" ከአዲስ አበባ ውጭ ፈልጌ አጣኋት!



መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

አሁን በሥራ ላይ ያለው ሕገ መንግሥት ነሐሴ 15 ቀን 1987 ዓ.ም ከፀደቀ እና ተግባር ላይ ከዋለ ጀምሮ፤ ማንም በፍጥነት ሊገነዘበው በማይችል ሁኔታ፣ ቀስ በቀስ ብሔርተኝነት ክንዱን እየፈረጠመ፣ ኢትዮጵያዊነት እየደበዘዘ ሄዶ አሁን ያለንበት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሰናል።

ከአዲስ አበባ ውጭ ያሉ ክልሎች፤ ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ መዋቅር ተዘርግቶላቸው። "ይህ ቦታ የእኛ ነው" በሚሉ ኃይሎች እጅ በመግባቱ፤ ለልማት፣ ለኢንቨስትመንት እና ለቱሪዝም ወዘተ እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ በመፈጠሩ፤ ኢትዮጵያዊነትን ፈልጎ ማግኘት የሚቻለው አዲስ አበባ ውስጥ ብቻ እየሆነ ነው።

ይባስ ብሎ እነዚህ ክልሎች ከበጀታቸው ትልቁን ድርሻ ለልማት ማዋል ሲገባቸው፤ ጦር መሳሪያ ሸምተው ልዩ ኃይል በማደራጀት፣ ወደ ክልል የሚደረግ ኢንቨስትመንት ቀርቶ እንዲሁ ለመጓዝ እንኳን የሚደረገው ጥረት ከብዙ ችግሮች ጋር እንዲያያዝ እያደረጉት ነው። በተቃራኒው አሁንም ከፍተኛ በሚባል ደረጃ የኢንቨስትመንት ፍሰቱ በአዲስ አበባ በስፋት መካሄዱ ቀጥሏል። ይህ ደግሞ እጅግ አስፈሪ የኑሮ ውድነትን እያስከተለ እንደሆነ የከተማዋ ነዋሪ የሆነ ሰው የሚመሰክረው ሀቅ ነው።

የከተማውን የኑሮ ውድነት እንደፈለጉ የሚያንሩት ደላሎች ናቸው። በተለይ የቤት ሽያጭን በተመለከተ፤ "የእናንተ ቤት ይህን ያህል ሚሊዮን ያወጣል" እያሉ ባልና ሚስት ተረጋግተው ልጆቻቸውን እንዳያሳድጉ፣ ከዚያም አለፍ ሲል ባል ወይ ሚስት ቤቱ አይሸጥም በማለታቸው ትዳር እየፈረሰ፣ በግልባጩ ግን ደላሎች ኪሳቸው እየፈረጠመ ነው።

**...ኢትዮጵያ ውስጥ እንኳን ስለ ትምህርት ጥራት ልናስብ ይቅርና ፤ የአንድ አገር ዜጎች ነን ብለን ለመናገር እንኳን እስኪያቅተን ችግር ውስጥ የከተተን ሥርዓት አሜን ብለን የተቀበልን ሕዝቦች ነን...**

እንዲህ ያሉ ሁኔታዎች ጤነኛ የኢኮኖሚ ሥርዓት እንደሌለን አመላካች ናቸው። አንድ ቤት የዛሬ አስር ዓመት አምስት ሚሊዮን ተሸጦ፣ አሁን ሰማንያ ሚሊዮን ካወጣ በአገሪቱ ውስጥ ጤነኛ ያልሆነ ሥርዓት እንዳለ ማረጋገጥ ይቻላል።

ማንኛውም ዜጋ በመላ ኢትዮጵያ ተዘዋውሮ እንደ ልቡ መስራት እንዳይችል ሕገ መንግስቱ ማነቆ በመሆኑ፣ በተጨማሪም የጠ/ሚ/ር ዐቢይ መንግሥት ሕገ መንግሥቱን ለማረም አንዲት ጋት እንኳን ሥልጣን ላይ ከወጣ በኋላ ሙከራ አለማድረጉ፣ ሁኔታው ወደ ፊት ሊቀጥል እንደሚችል ቅድመ ግምታችንን እንድናስቀምጥ ያስገድደናል።

ምናልባትም በዓለም ላይ በገዛ ሀገሩ ግዛት ላይ እንደልቡ ማዘዝ የማይችል መንግሥት፣ አሁን ሥልጣን ላይ ያለው ኢትዮጵያ መንግሥት ብቻ ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ ሊቀየር የሚችልበት ጅማሮም እየታየ አይደለም።

አቶ አሥመላሽ ገ/ሥላሴ የተባሉ የፓርላማ አባል በአንድ ወቅት ስለ ፌዴራላዊ ሥርዓቱ ሲያስረዱ "የፌደራል መንግሥት ስልጣን እንጂ፣ የፌደራል መንግሥት በብቸኝነት ወይም የበላይ ሆኖ የሚያዝበት ሥልጣን የለም" ብለው ነበር። ይህን አባባል በጥልቀት ለመረመረው፣ ኢትዮጵያ የምትባል "የዕድርተኞች ማኅበር" እንጂ ሀገር እንደሌለችው ይረዳል። ነገሩ ባለበት የሚረግጥ ከሆነ በእርግጠኝነት በክልሎች ውስጥ አስከፊ ድህነትና ኋላቀርነት፣ አዲስ አበባ ውስጥ ደግሞ አስፈሪ የኑሮ ውድነትና ዕድገት በተነጻጻሪነት መመዝገቡ አይቀሬ ይመስላል።

በእኔ እይታ ይህንን "ጋጥ ወጥ" አካሄድ ለመለወጥ አቅሙ የፈጠረ አንድም ኃይል አይታየኝም። በመሆኑም መጪው ዘመን ካለፈው የከፋ ሊሆን እንደሚችል ያለ ጥርጥር መናገር እችላለሁ። ከሁሉም በላይ እጅግ አሳፋሪው ነገር፤ ሌሎች አገሮች አይደለም የገዛ ሀገራቸውን ሐብት፣ የሌሎችን ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችላቸውን ሥርዓት አሻግረው ሲዘረጉ፣ እኛ ሀገራችን ያላትን የተፈጥሮ ጸጋ ወደ ጥቅም ለውጠን፣ ሕይወታችንን የተሻለ ለማድረግ አቅቶን (በሕገ መንግሥቱ ምክንያት) በድህነት ለመኖር መገደዳችን ነው።

ዛሬ በርካታ ሀገሮች ሀገራቸውን ገንብተው አጠናቀዋል፤ አብዛኞቹም ገንዘባቸውን እና ጊዜያቸውን የሚያጠፉት በውጭ ፖሊሲ ላይ ሆኗል። በአንጻሩ ግን እኛ እንኳን ሀገራችንን ገንብተን ልንጨርስ፣ ደረጃውን የጠበቀ ሕገ መንግሥት እንኳን ለመፃፍ እጃችን ቆፈን እንደያዘው አለ።

እኛ ልጆች እያለን ዕውቀትን የቀሰምነው ከመንግሥት ት/ቤት ነው፤ ያኔ በተገቢው የትምህርት ጥራት የተማሩ ዜጎች አሁን በበርካታ ሀገራት ዩኒቨርስቲዎች እና ሌሎች ከፍተኛ ተቋማት ውስጥ በመሥራት ላይ ናቸው። ዛሬ ላይ መንግሥት ት/ቤት የሚማሩ ልጆች ሲያድጉ የሚጠብቃቸውን ሕይወት ሳስበው በእጅጉ ይጨንቀኛል።

ኢትዮጵያ ውስጥ እንኳን ስለ ትምህርት ጥራት ልናስብ ይቅርና ፤ የአንድ አገር ዜጎች ነን ብለን ለመናገር እንኳን እስኪያቅተን ችግር ውስጥ የከተተን ሥርዓት አሜን ብለን የተቀበልን ሕዝቦች ነን። እኛ ኢትዮጵያውያን ቤተ ሙከራ ውስጥ ያሉ "አይጦች" ይመሥል ላለፉት 28 ዓመታት ሲቀለድብን፣ ሲሞከርብን የኖርን ሰዎች ነን።


የሰው ልጆች ለዘመናት በርካታ ጦርነቶችን አድርገው "ያንተ ሥርዓት ከኔ ይሻላል" እያሉ ሲፋጁ ከርመዋል። አሁን ግን ምን ዓይነት የፌደራል ሥርዓትና የመንግሥት አስተዳደር ለሀገር እድገት እንደሚጠቅም ብዙዎች መግባባት ላይ ቢደርስም ኢትዮጵያዊያን ግን አ ሁንም የሚጠቅመንን ፍኖት አምጠን መውለድ እየቻልን አይመስልም።

ዛሬም በመሀይማን ፖለቲከኞች እየተመራን አሁንም ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ እየዳከርን ነው። ህወሓት ከቤተ መንግሥት ተባረረ እንጂ የጻፈው ሕገ መንግስት፣ አስተሳሰቡና ርዕዮቱ እንዳለ ነው። ሌላው ቢቀር ላለፉት 28 ዓመታት ያደረግነው ጉዞ ትክክል ነው ወይ? ማን ተጠቃሚ ፣ ማንስ ተጎጂ ሆነ? ብለው እንኳን ወደ ኋላ ነገሮችን ማጤን የተሳናቸው መሪዎች ይዘን ነው እየተጓዝን ያለነው። ሰሞኑን በተከታታይ እየተነገረ ስላለው የክልሎች በጀት ጉዳይን ብንመለከት እንኳ የትኛው ክልል እየለማ፣ የትኛው ጠኔ ይዞት እንደተቆራመደ መገንዘብ ቀላል ነው።

አዲስ አበባ አምስት መቶ አርባ ስኩዌር ኪ.ሜ የቆዳ ስፋት ይዛ በ2009 ዓ.ም 31 ቢሊዮን ብር፣ 2010 ዓ.ም 40 ቢሊዮን ብር፣ 2011 ዓ.ም 45 ቢሊዮን ብር፣ በ2012 ዓ.ም ደግሞ 48 ቢሊዮን ብር በጀት ስትይዝ ፤ በአንጻሩ አማራ ክልል ግን 160 000 ሺ ስኩዌር ኪ.ሜ ስፋት ይዞ ለ2012 በጀት ዓመት የያዘው በጀት ከአዲስ አበባ ከተማ እኩል አርባ ሰባት ቢሊዮን ብር ነው።

ክልሎች በየዓመቱ የሚይዙትን በጀት ብቻ አስተውሎ በሥራ ላይ ያለው ሕገ መንግሥት ምንያህል "ተራ" ስለመሆኑ ማስረጃ አድርጎ ማመሳከር ይችላል። ይህንን ችግር እያዩ "ቆይ ዛሬ፣ ቆይ ነገ" ማለት ታዲያ ጊዜ ለማቃጠል እና ሀገርን ለማጥፋት ካልሆነ በስተቀር እንዴት ጤነኛ አመለካከት ሆኖ ሊደመጥ ይችላል?

# አንደበት



“የእኛ መለኪያ፣ የምርጫ ምህዳሩ አለ ወይ? የሚለው ነው፡፡ ከማዕከል እስከ ታችኛው ድምፅ መስጫ ጣቢያ ድረስ ያለውን አደረጃጀት ከኢሕአዴግ ካድሬዎች ነፃ አድርጎ፣ ወገንተኛ ባልሆኑ አካላት የሚመራ መሆኑን ማረጋገጥ እንፈልጋለን፡፡ ይህ ሳይረጋገጥ ምርጫ ማካሄድ ማለት ቀልድ ነው፡፡ እኛ እስከ ሰለቸን ምርጫ እየገባን፣ ህዝባችንን ለትልቅ ጣጣ ዳርገነዋል፡፡ እስካሁን የህዝብን መብት ማስከበር አቅቶን፣ በሕይወቱና በነፍሱ እየከፈለ፣ ጥቂቶቻችን፣ “ፓርላማ ነበርን” እንድንል አስችሎናል፡፡ አንድ ሰው የሚመረጠው ብዙ ሰው ተሰውቶ እንደሆነ በትግሉ ሜዳ ላይ ያለፍን እናውቀዋለን”

*ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ /የኢትዮጵያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ ፕሬዘዳንት*
*/ኦትዮጲስ ጋዜጣ ነሐሴ 12 ቀን 2011 ዓ.ም*

..................................................



“በነገራችን ላይ ህዝቡ የሚወደው ኢሕአዴግን ሳይሆን ዶክተር ዐቢይን ነው፡፡ ስለዚህ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ኢሕአዴግን መርታት የሚችሉበት ዕድል አለ ማለት ነው፡፡ ህዝቡ ጥንቁቅ ስለሆነ ነው እኮ የተሰራው በጎ ነገር ሁሉ በኢሕአዴግ ሳይሆን በዶክተር ዐቢይ መሆኑን ደጋግሞ ሲገልፅ የነበረው፡፡ ይህች ጉዳይ አስፈላጊ ትመስለኛለች፡፡ አሕአዴግም እንበለው ሌላው በዚያ ባህል ከሚኖሩ ሰዎች ጋር መግባባት መቻል አለበት፡፡ ያንን ለማድረግ ደግሞ መንገዱን ጠንቅቆ ማወቅ ይገባዋል፡፡ ዶክተር ዐቢይም ቢሆኑ ፓርቲያቸው እንዲመረጥ ብዙ ፈተና አለባቸው”

*ዶክተር ኢንጅነር አድማሱ ገበየሁ*
*/አዲስ ዘመን ጋዜጣ ነሐሴ 11 ቀን 2011 ዓ.ም/*

..................................................



“የቴክኖሎጂ ፖሊሲያችን፤ ከሁሉም የተለየ ያደርገናል የሚል ዕምነት አለኝ፡፡ ምርትን ለማሳደግና ምርታማ ለመሆን ቴክኖሎጂን አሟጠን መጠቀም አለብን ከሚል መነሻ የተዘጋጀ ፖሊሲ ነው፡፡ ኋላ ቀር የሆነውን ቴክኖሎጂ በሙሉ የማዘመንና አዲስ ጠቃሚ ቴክኖሎጂን ያለ ገደብ የመጠቀም ፖሊሲ አዘጋጅተናል፡፡ ለግብርና፣ ለትምህርት፣ ለጤና፣ ለባንክና ለሌሎችም የአገልግሎት ዘርፎች የሚል ቴክኖሎጂ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ አልተተገበረም፡፡ ፖሊሲው ዋነኛ ትኩረቱ እዚህ ላይ ነው”

*ዶ/ር ጫኔ ከበደ /የኢዜማ ምክትል ሊ/መንበር/*
*/አዲስ አድማስ ጋዜጣ ነሐሴ 11 ቀን 2011 ዓ.ም/*

..................................................



“ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ወደ 50 የሚጠጉ የመንግሥት ዩኒቨርስቲዎች እያስተናገደች ያለችበት ወቅት ነው፡፡ ከዚሁ አኳያ የመንግሥት ዩኒቨርስቲዎችን በማስፋፋት ብቻ የአገሪቱን የከፍተኛ ትምህርት ፍላጎት ማሟላት የሚቻልበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ ለዚህ ነው የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአሁኑ ጊዜ ቁጥራቸው እየጨመረ የመጣው፡፡ ይህም የቁጥር ዕድገት ብቻ እንዳይሆን ተቋማቱን የመደገፍ፣ አመቺ የሆኑ ፖሊሲዎችን የማዘጋጃ ሥራ ከመንግሥት በኩል ይጠበቃል፡፡ ከግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጀምሮ ዘርፉን አስፈላጊ ወደሆነና የንግድ ስሜት ወዳለው አቅጣጫ እንዳይሄድ፣ መንግሥትና ሕዝቡ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በመወጣት ወደ ተሻለ የጥራት ደረጃ መድረስ ይጠበቅባቸዋል የሚል ዕምነት አለኝ”

*ወንደሰን ታምራት (ተባባሪ ፕሮፌሰር)*
*የቅድስት ማሪያም ዩኒቨርስቲ መሥራችና ፕሬዚዳንት*
*ሪፖርተር ነሐሴ 15 ቀን 2011 ዓ.ም*

..................................................



““በኢንተርናሽናል ውድድር ሜዳዎቻችን ተቀባይነት አጥተዋል፤ ሊያመልጠን የማይገባን የቻን ውድድር ተሰርዞብናል፡፡ እንደ አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ዓይነት ከአገር አልፈው አፍሪካን የሚመሩ መሪዎች ማፍራት አለብን፡፡ ባለፉት 28 ዓመታት ግን ይህን ማድረግ አልቻልንም፤ በተጫዋች ደረጃ አውሮፓ አንድ፣ አፍሪካ ደግሞ ሁለት ነው ያሉን፤ ጋቶች ከግብፅ ክለቦች ተሰናብቷል፡፡ ከ100 ሚሊዮን ህዝብ ያሉን 3 ፕሮፌሽናል ተጫዋቾች ናቸው፡፡ በየጊዜው ተተኪ እያፈራን አይደለም፤ በአፍሪካ ደረጃ የዓለምና የአፍሪካ ዋንጫ ላይ ያጫወተ የምናውቀው ዳኛ አንድ ነው ብቻ ነው”

*አሰልጣኝ ዮሐንስ ሳህሌ /ወልዋሎ አዲግራት/*
*ሀትሪክ ነሐሴ 15 ቀን 2011 ዓ.ም*

# አባባል

- አውቃለሁ ማለት ያፈርሳል፣ ፍቅር ግን ያንፃል ፤አውቃለሁ የሚል ቢኖር ገና አላወቀምና ሊያውቀው የሚገባውን ይወቅ፡፡
- አልጋ የተፈለሰፈው ከመሬት ለመሸሽ ነበር፤ ግን ሸሽቶ ማምለጥን የቻለ እስከ አሁን ድረስ አልተገኘም፡፡
- የተመኘውን የሚፈፅም ታላቅ ሰው ነው፣ ሊያገኝ የሚችለውን ብቻ የሚመኝ ደግሞ ብልህ ነው፡፡
- አብልተው፣ አጠጥተው ይህን ፈጽሙልን የሚሉ ሰዎች ከነፍሰ ገዳዮች ወገን ናቸው፡፡
- አለመናገር ኩራት የሚመስላቸው ሞልተዋል፤ ግን ጨዋነትም ነው፡፡

# ለጠቅላላ እውቀት

በኢትዮጵያ የንጉሰ ነገስት ሥርዓት ውስጥ የነበሩ መዓረጋትና የመዓረጋቱ ተዋረድ ለሠላማዊ ክፍል የሚሰጥ መዓረግ ስማና የደረጃው ተዋረድ፡

**ቢትወድድ፡-** እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ያለ ባለሙሉ ስልጣን

**አፈ ንጉስ፡-** የፍርድ ሚኒስትር

**ጸሐፌ ትዕዛዝ፡-** የጽሕፈት ሚኒስትር

**አዛዥ፡-** የግቢ ሚኒስትር

**በጅሮንድ፡-** የገንዘብ ሚኒስትር

**ነጋድራስ፡-** የንግድ ሚኒስትር

**ከንቲባ፡-** የአ.አ ከተማ የማዘጋጃ ቤት ሹም

**ብላቴን ጌታ፡-** በልዩ ልዩ ክፍል የሚኒስቴርነት ሥልጣን ላገኙ የሚሰጥ

**ሊቀ መኳስ፡-** ንጉሠ ነገስት በነገሰና ጉባኤ ባደረገ ጊዜ በግራና በቀኝ የሚቆም

**ወህኒ አዛዥ፡-** ከአዛዥ በታች ይሾማል፡፡

**ብላታ፡-** በየሥራው ክፍል ላሉ ጠቅላይ ዲሬክተሮችና የመንግሥት ወንበሮች ለሆኑ የሚሰጥ

**ልጅ፡-** የመኳንንት ልጆች የሚጠሩበት

**አቶ፡-** የማናቸውም የጨዋ ሰው ስም

## ግጥም

# እናባልፋቸው

አምቡላንሱ ሲጮኽ
ፊሽካ እየተነፋ
እግረኛው ሲዋከብ
ወደዳር ሲገፋ
ጎዳና የገባው
ተሽከርካሪ ሁሉ
ቃፊር ተገትሮ
አትንዝ መባሉ፡፡
በዚያች አንዲት አፍታ
ጭርታ ጭጭታ
ግርምታ - ሹክሹክታ
አይኖች - ተቅበዝብዘው
ጓጉተው - ተጎልጉለው
ልቦችም - ተሰቅለው
ሽው - እልም
ሽው - እልም
ቱር - ቱር …
ብር - ብር ….
መኪና እንደ - ጀት
አስፋልትም እንደ - አየር
እንዲህ ነው “የኛ” ዓለም
የገዢነት ኑሮ
መባተት ጭልፊት
እንደምትሸሽ ዶሮ፡፡
ለነፃነት ታግሎ
ጨቋኙን ጨፍልቆ
በደስታ መፍነክነክ
መግዛት ተደብቆ
ይሄም ይባል እንዴ
ታላቅ አርአያነት?
ለሌላው ማንበሽበሽ
ያጡትን አርነት፡፡

***የአንድ ቀን እስረኛ በእንድርያስ ተረፈ ወ/አማኑኤል***

# “የፀረ ሽብር ሕጉ የክስ መሠረት መሆኑ ፈፅሞ አግባብ አይደለም”

## “እንግልትና ድብደባ ቢደርስብኝም ከሀገሬ ተገልዬ አልኖርኩም”

### *ዶ/ር ዳንኤል በቀለ (የኢትዮጵያ ሰብኣዊ መብት ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር)*

በቅርቡ የኢትዮጵያ ሰብኣዊ መብት ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ሆነው የተሾሙት ዶ/ር ዳንኤል በቀለ፤ዓለም አቀፉ የሰብኣዊ መብት ተሚጋች ሂዩማን ራይትስ ዎች ከየትኛውም አገር የገንዘብ ድጋፍ እንደማይቀበል፣ ድጎማ የሚያደርጉለት ፋውንዴሽኖች እና ባለፀጎችም በሥራው ላይ ፈፅሞ ተፅዕኖ ሊያሳድሩበት እንደማይችሉ ያመላከቱት የሰብኣዊ መብት ኮሚሽነር፣ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ “ሂዩማን ራይትስ ዎች እኛ ወንጀለኛ ያደረግናቸውን የሚሾም ነፃ ያልሆነ ድርጅት ነው” በማለት የእሳቸውን ሹመት በፓርላማ ያጣጣሉበትን አስመልክቶ በወቅቱ የተሰማቸውን ስሜት አካፍለውናል፡፡

በቀጣይ የኢትዮጵያ የሰብኣዊ መብት ኮሚሽን ምን ሊሠራ እንዳሰበ፣ በዜጎች ላይ ከባድ የሰብኣዊ መብት ጥሰት አድርሰው የተደበቁ ግለሰቦች በሕግ በሚጠየቁበት ጉዳይ ዙሪያ የተቋሙ ድርሻ ምን ድረስ እንደሆነ፤ እንዲሁም የወደፊት ህልም እና ራዕያቸውን ጭምር በቆይታችን ነግረውናል፡፡

ከዚህ በኋላ ማንኛውም የሕግ አካልም ሆነ ሹመኛ የሰብኣዊ መብት ጥሰት ከፈፀመ ጉዳዩ አደባባይ የሚወጣበት፣ አጥፊውም በሕግ የሚቀጣበት እና ሌሎችም የሚማሩበት አሠራር እንደሚከተሉ ያሳወቁት የኢትዮጵያ የሰብኣዊ መብት ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ዶ/ር ዳንኤል በቀለ ከግዮን ጋዜጠኞች ሮቤል ምትኩ እና ፍቃዱ ማ/ወርቅ ጋር ያደረጉትን ቆይታ ሁለተኛ ክፍል እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡

***ግዮን፡-ጆርጅ ሶሮስ ለሂዩማን ራይትስ ዎች ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርገው፣ ከሰብኣዊ መብት ጋር በተያያዘ በተለያዩ ሀገራት ላይ ተጽዕኖ ለመፍጠር እና የተመሳሳይ ፆታ ጋብቻ እውን እንዲሆን ግፊት ያደርጋል የሚል ነገር አለ፡፡ እርስዎ በተቋሙ የሠሩ እንደመሆንዎ ይሄ አስተያየት ትክክል ነው ብለው ያምናሉ?***

ዶ/ር ዳንኤል፡- ጆርጅ ሶሮስ ፋውንዴሽን፤ “ኦፕን ሶሳይቲ ፋውንዴሽን እና ኦፕን ሶሳይቲ ኢንስቲትዩት” የሚባል፣ በዓለም የሚታወቅ ትልቅ ተቋም ነው፡፡ ለሂዩማን ራይትስ ዎች ትልቅ የገንዘብ ድጋፍ ከሚያደርጉ ድርጅቶች ውስጥ አንዱ ጆርጅ ሶርስ መሆኑን እዛ በምሰራበት ወቅት ተመልክቻለሁ፤ ይሄ ምስጢር አይደለም፤ በአደባባይ የሚታወቅ ነገር ነው፡፡

ነገር ግን ሂዩማን ራይትስ ዎች ከጆርጅ ሶሮስም ይሁን ከሌሎች ከማናቸውም የገንዘብ ድጋፍ ከሚሰጡት ድርጅቶች የሚመጣ መመሪያ እና ቅድመ ሁኔታን አይቀበልም፡፡ ተፅዕኖ ሊያደርጉበትም አይችሉም፡ ፡ ሂዩማን ራይትስ ዎች ዋናው የሚታወቅበት ከየትኛውም ሀገር መንግሥት ገንዘብ አለመቀበሉ ነው ፡፡ አንዳንድ ሰዎች በአሜሪካ መንግሥት የሚደገፍ ይመስላቸዋል፣ ይሄ ግን የተሳሳተ ዕሣቤ ነው፡፡

የገንዘብ ምንጫችን ግለሰቦች፣ ፋውንዴሽኖች፣ ዓላማውን የሚደግፉ ሐብት ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ ገንዘብ ከመቀበላችን በፊት የጥቅም ግጭት አለመኖሩን እናረጋግጣለን፡፡ በገንዘብ የሚደግፉን ሰዎች እኛ ከምንሠራው ሥራና ተልዕኮ ጋር የሚጋጭ ዓላማ ያላቸውና የሌላቸው መሆኑን ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ እናጣራለን፡፡ አጭር ምሳሌ ለመስጠት ያህል፣ ነዳጅና ማዕድን የማውጣት ሥራ ከሚሠሩ ኩባንያዎች እና እነሱ ከመሠረቷቸው ፋውንዴሽኖች ገንዘብ አንቀበልም፡፡

***ግዮን፡- ምክንያታችሁ ምንድን ነው?***

ዶ/ር ዳንኤል፡- አንዱ የምንሰራው የሰብኣዊ መብት ጥናት፣ ምርምር እና አድቮኬሲ ሥራ በነዳጅና ማዕድን ማውጣት ሥራ የሚፈፀሙ የሰብኣዊ መብት ጥሰቶችን የሚመለከት ስለሆነ፣ ይሄ ደግሞ የጥቅም ግጭት ስላለው ገንዘብ አንቀበልም፡፡

እነዚህ ዓለም አቀፍ የሰብኣዊ መብት ተቋሞች ሥራቸውን ለማካሄድ የሚያስችል ገንዘብ የግድ ያስፈልጋቸዋል፤ ነገር ግን ያንን ገንዘብ የሰጣቸው አካል ገና ለገና ድጋፍ ስላደረገላቸው ዓላማቸው ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል ማለት አይደለም፡፡ ብዙ ጊዜ እንዲህ ዓይነት ግምት እንዳለ ይገባኛል፡፡ ነገር ግን ግምቱ የመጣው ድርጅቶቹ የሚሰሩበትን ሁኔታ በቅርብ ካለመረዳት፣ እንዲሁም በተቋማቱ ውስጥ የሚያገለግሉት ባለሙያዎች ያላቸውን የሙያ ብቃት እና የነፃ ባለሙያነት ስሜት ካለማወቅ ይመነጫል፡፡ እኔ እዛ በነበርኩበት ወቅት ከጆርጅ ሶሮስም ሆነ ከየትኛውም ዓይነት ዕርዳታ ሰጪ ድርጅት፣ ምንም ዓይነት የፕሮግራም ተጽዕኖ ገጥሞን አያውቅም፡፡

***ግዮን፡- በሂዩማን ራይትስ ዎች የአፍሪካ ዋና ዳይሬክተር ሆነው ኬንያ በሚሰሩበት ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ “እኛ ወንጀለኛ ያደረግ ነቸውን የሚሾም፣ ነፃ ያልሆነ ድርጅት መሆኑን ይኸው እያሳየን ነው” በማለት በፓርላማ ላይ የእርስዎን ዓለም አቀፍ ሹመት*** ►



**ያጣጣሉበትን ንግግር ሲያስደምጡ ምን ተሰማዎት?**

ዶ/ር ዳንኤል፡- ያኔ ጠ/ሚ/ር የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ ፓርላማ ላይ ንግግር ሲያደርጉ ይሄንን ሀሳብ ጠቅሰው እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ በወቅቱ ንግግራቸውን ስሰማ አሳዝነኖኛል፤ በሌላ በኩል ምናልባት እንድፈራ ተብሎ የተላለፈ መልዕክት ከሆነ ደግሞ ፈጽሞ የእሳቸው አባባል እንደማያስጨንቀኝም፣ እንደማያስፈራኝም በወቅቱ ገልጫለሁ፡፡ ያንን አቋሜን ወደ ሀገር ውስጥ መጥቼም አሳይቻለሁ፡፡ በእሳቸው አንደበት እንደዛ ዓይነቱ የማይረባ ነገር ስለተወራ ፍርሃት ይፈጥርበታል ወይንም ሀገር ውስጥ እንዳይመጣ ያደርገዋል ተብሎ ታስቦ ከሆነ ስህተት መሆኑን ለማሳየት በተደጋጋሚ ወደ ሀገር ቤት መጥቻለሁ፡፡

**ግዮን፡- አቶ መለስ እንደዛ ካሉ ከስንት ጊዜ በኋላ ነበር የመጡት?**

ዶ/ር ዳንኤል፡- ጠ/ሚ/ሩ በምክር ቤቱ አባላት ፊት ይሄንን ንግግር ባደረጉ፣ በኹለት ወር ጊዜ ውስጥ ወደ አዲስ አበባ መጥቻለሁ፡፡ በፊት ያኔ በነበረው አስተዳደር የረዥምም ጊዜ እስር፣ እንግልትና ድብደባን የመሰሉ ብዙ ጥቃቶች ያደረሰብኝ ቢሆንም፤ ስፈታ ለትምህርት እና ለሥራ ውጭ ሀገር ብሄድም፣ ይሄንን ሁሉ ዘመናት ከሀገሬ ራሴን አግልዬ አልኖርኩም፡፡

ሁልጊዜም እመጣ ነበር፡፡ ሂዩማን ራይትስዎች በምሰራበት ጊዜም በተደጋጋሚ ወደ እዚህ መጥቻለሁ፤ ግን ስመጣ ችግር አይገጥመኝም ማለት አልነበረም፤ አልፎ አልፎ ችግሮች ቢያጋጥሙኝም መምጣቴን አላቆምኩም ነበር፡፡

**ግዮን፡- ችግሮቹ ምን ዓይነት ነበሩ?**

ዶ/ር ዳንኤል፡- የሚከታተሉኝ ሰዎች ነበሩ፣ የሚያስፈራሩኝም ሰዎች ነበሩ፡፡ ኤርፖርት ከምደርስበት ጊዜ አንስቶ ዕቃዬን የሚነጥቁኝ ሰዎችም አሉ፡፡ በአንድ ወቅት ፓስፖርቴን እስከመንጠቅ ደርሰው ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ፓስፖርት ነው ያለኝ፣ ውጭ ሀገርም ሄጄ የፖለቲካ ጥገኝነት ጠይቄ ሳይሆን፣ በኢትዮጵያዊ ፓስፖርቴ ነው የኖርኩት፡፡

ስለዚህ ፓስፖርቴንም ለማደስ፣ በሁለተኛ ደረጃ ሀገሬን ጥዬ የማልሄድ መሆኔን ጭምር ለማሳወቅ ወደ ኢትዮጵያ እመላለስ ነበር፡፡ እስር ቤት ውስጥ እስረኞችን ለመጎብኘት በምሄድበት ጊዜ እንዳልገባ እከለከላለሁ፣ ለአንዳንድ ጉዳዮች መንግሥት መ/ቤት በምሄድ ጊዜ የምፈልገውን ነገር እንዳላገኝ እከለከላለሁ፡፡ በጥቅሉ ‹‹ሀራስመንት›› የምንለው ዓይነት ነገር ገጥሞኛል፡፡

ትንሽ ከበድ የሚለው በአንድ ወቅት ፓስፖርቴን መነጠቄ ብቻ ነው፡፡ በኋላ ግን ጥቂት ባለሥልጣኖች ጣልቃ ገብተው ፓስፖርቴ እንዲመለስልኝ አድርገውልኛል፡፡ ያኔ ጠ/ሚ/ሩ ስለ እኔ የሰጡት አስተያየት ኢትዮጵያ ውስጥ በነበረው አሰራር እንድትፈራ ማድረግ፣ ሌሎችም ላይ ተመሳሳይ ስሜትን መፍጠር እና ከምትሰራው ሥራ እንድትታቀብ ለማስቻል የታለመ ነበር፡፡ ግን ያ ሁሉ ጨቋኝ የሆነ የፖለቲካ አስተሳሰብና አሰራር የማይሰራ መሆኑ የታወቀ ይመስለኛል፡፡

**ግዮን፡- በቅርቡ መነጋገሪያ የሆነው እና ብዙዎች ለሞት፣ ለእስር፣ ለመከራና ለአካል ጉዳት የተዳረጉበት የጸረ ሽብር ህጉ ምንም መሻሻል ሳይደረግበት ተግባር ላይ እየዋለ ነው፡፡ አሁንም ጋዜጠኞች እና ፖለቲከኞች የዚህ ሠለባ ሆነዋል፤ ይሄ ሕግ አለመሻሻሉ እናንተ ለምትሰሩት የሰብኣዊ መብት ክትትል ተጽዕኖ አይፈጥርም?**

ዶ/ር ዳንኤል፡- ኢትዮጵያ ውስጥ ከዚህ በፊት በነበረው የፖለቲካ አስተዳደር ተፈ ጥረው ከነበሩ፣ ጨቋኝ ናቸው ተብለው ከሚታሙ ሕጎች ውስጥ አንዱ የጸረ ሽብር ሕግ በመባል የሚታወቀው ነው፡፡ አዲሱ የለውጥ አስተዳደር ወደ ሥልጣን ከመጣ በኋላ በአስቸኳይ የማሻሻያ ዕርምጃ እወስድባቸዋለሁ ብሎ ከለያቸው ሕጎች ውስጥ አንዱ እሱ ነው፤ የሲቪክ ማኅበራትና ሚዲያን የሚመለከተው ሕግም በተከታይነት ይቀመጣሉ፡፡

ከእነዚህ ውስጥ ጨቋኝ የነበረው የሲቪክ ማህበራት ሕግ አሁን የተሻለ ሆኖ ተተክቷል፤ የፀረ ሽብር ሕጉንም እንዲሁ ለማሻሻል ተጠናቆ ረቂቅ ህግ ሁሉ ተዘጋጅቶ፣ የመጨረሻው ደረጃ ላይ የደረሰ ይመስለኛል፡፡ ለሚኒስትሮች ም/ቤት እና በቀጣይ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ቀርቦ ይፀድቃል፡፡

በዚህ ሁኔታ ላይ እያለን፣ ኢትዮጵያ ውስጥ አዲስ ከተጀመረው ራዕይም አንጻር ይሄ የተነቀፈ እና ሊሻሻል ይገባዋል የተባለ የጸረ ሽብር ሕግ አሁን ባለንበት ጊዜ ለክስ መሰረት መሆኑ ፈፅሞ አግባብ አይደለም፡፡ በእኔ አስተሳሰብ የተደረገው ነገር ትልቅ ስህተት ይመስለኛል፡፡

መንግስት በወንጀል ሊጠይቃቸው የሚፈልጋቸው ሰዎች ካሉ፣ በእርግጥም የፈፀሙት ወንጀል ከተገኘ፣ በመደበኛው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ላይሸፈን የሚችል ጥፋት የለም፡፡ መደበኛው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በጣም ሰፊ ነው፤ ሁሉንም ዓይነት ጉዳዮችን ይመለከታል፣ ያካትታል፡፡ ስለዚህ ተፈ ፀመ የተባለ ጥፋት ካለም በመደበኛ ወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ መክሰስ ነው እንጂ በዚህ በተወገዘና በጣም በተነቀፈ፣ እንዲሁም ሊሻሻል እንደሚገባው ተረጋግጦለት በሂደት ላይ ባለ ሕግ ላይ ተመስርቶ መክሰስ ስህተት ነው፡፡ በተለይ ደግሞ አሁን ባለንበት ወቅት፡፡

ሕጉ ስላልተሻሻለ፣ ቴክኒካሊ ሥራ ላይ ያለ በመሆኑ ክስ ልታቀርብበት ትችል ይሆናል፤ ነገር ግን ከሁኔታው አንፃር አላስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤትም ሆነ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሙሉ፤ ይሄንን ሕግ መጠቀም አላስፈላጊ መሆኑን ሊያውቁት እንደሚገባ መልዕክቴን አስተላልፋለሁ፡፡ አፋኙን ሕግ መሰረት ተደርጎ የጊዜ ቀጠሮ የተጠየቀባቸው እንዳሉ ሠምቻለሁ፤ በርግጥ ሕጉ ስላለ ሕገወጥ ነው ማለት ባያስችልም፣ ተገቢ ያልሆነ አሠራር ነውና መታረም አለበት፡፡

በሀገር ውስጥም በዓለም አቀፍ ደረጃም ከተወቀሱ ሕጎች ቀዳሚው የሆነ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ ይሄንን መሠረት በማድረግ የቀድሞው የኢሕአዴግ አስተዳደር ምን ያህል የግፍ መፈፀሚያ መሳሪያው አድርጎት እንደነበር የቅርብ ጊዜ ታሪካችን ነው፡፡ ከውስጣችን ያልወጣ፣ የማይረሳም ጭምር፡፡ አሁን ላይ ያለው የለውጡ አስተዳደር አማራጭ እያለው ያንኑ መንገድ መጠቀሙ ስህተት ነው፤ ይሄ አካሄድ በፍጥነት ይቆማል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ግዮን፡- በዚህ የጸረ ሽብር ህግ የታሰሩ ጋዜጠኞች የሰብኣዊ መብት ጥሰት እንደተፈ ፀመባቸው ተናግረዋል፤ በየቦታው ዜጎች “ውጡልን” እየተባሉ መፈናቀል እና ስደቱም ተጠናክሯል፡፡ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ መረጃዎችን ማሰባሰብ ጀምራችኋል? ክትትልስ እያደረጋችሁ ነው?

ዶ/ር ዳንኤል፡- ሥራ ከጀመርኩ ገና ሦስተኛ ሳምንቴ ነው፤ (ይህን ቃለምልልስ ያደረግነው ማክሰኞ ሐምሌ 30/2011 ነው) ስለዚህ እዛ ደረጃ ላይ ገና አልደረስንም፡፡ በእነዚህ ባለፉት የተወሰኑ ቀናት ለማድረግ እየሞከርኩ ያለኹት፣ ይሄ የምመራው የሰብኣዊ መብት ኮሚሽን እስከዛሬ እንዴት ይሰራ ነበር? ያጋጠሙት ችግሮች ምንድን ናቸው፣ ሠራተኞቹ ምን አስተያየት አላቸው? ሌሎች ባለድርሻ አካላትስ ምን ይላሉ? የኢትዮጵያ የሰብኣዊ መብት ኮሚሽን ከእንግዲህ ወዲያ እንዴት ነው ሊሰራ የሚገባው? የሚሉትን ነገሮች ገና በማዳመጥ ሂደት ላይ ነው ያለኹት፡፡

ወደ ዋናው ሥራችን በማስበውና በምሻው መጠን ገና አልገባንም፡፡ እንዳላችሁት ግን የሀገራችን የሰብኣዊ መብት አያያዝ ሁኔታ በተለይ ከግጭት ጋር በተያያዘና በርካታ ዜጎች እየተፈናቀሉ በመሆኑ በጣም አሳሳቢ የሆነ የሰብኣዊ መብት ጥሰት እንዳለ እገነዘባለሁ፡፡ በዛው ልክ ፈጣን ምላሽ እንደሚያስፈልገውም

**ቀደም ሲል ሥልጣን ላይ የነበረው አስተዳደር በጣም ዘግናኝ፣ አሳዛኝ እና ከባድ የሰብኣዊ መብት ጥሰቶችን ይፈፅም እንደነበር ይታወቃል፡፡ ራሴም በተወሰነ መጠን ጉዳተኛ ሆኜ ችግሩን ተመልክቼዋለሁ፡፡ ምን ያህል ተገቢ ያልሆነ ሥራ ሲሠራ እንደነበር በፊትም ስለማውቅ ነው ከንደኞቼ ጋር እታገል የነበረው**

እረዳለሁ፡፡

ተቋሙን የመረዳት እና ለዘላቂ ሥራ ጠንካራ ተቋም ለመፍጠር የሚያስፈልገውን ሪፎርም የማካሄድ ሥራ በአንድ በኩል፤ በሌላ አቀጣጫ ዕለት ተዕለት የሚያጋጥሙንን የሰብኣዊ መብት ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት የሚያስፈልግ በመሆኑ ኹለቱን አጣምሮ ለማስኬድ በዝግጅት ላይ ነው ያለሁት፤ በዚህ አጋጣሚ ሕዝብ ትንሽ እንዲታገሰኝ አደራ እላለሁ፡፡ ይህ ማለት ግን የሰብኣዊ መብት ጉዳይ ላይ ሀሳብ፣ አስተያየት ጥያቄ ያላቸው ሰዎች ያንን ማቅረባቸውን ማቆም አለባቸው እያልኩ አይደለም፡፡ እነሱንም ተቀብለን ለማስተናገድ እየሞከርን ነው፡፡

**ግዮን፡- ከምርጫ 97 በኋላ ጠንካራ ሲቪክ ማኅበራት እንዲጠፉ ተደርገዋል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ተቋማት መኖራቸው ለእናንተ ሥራ ጠቀሜታው የጎላ ከመሆኑ አኳያ፣ ሲቪክ ማኅበራቱ እንዲበራከቱ መንግሥት ምን ማድረግ አለበት ይላሉ?**

ዶ/ር ዳንኤል፡- ከምርጫ 97 በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠረው የፖለቲካ ቀውስ አንዱ አሳዛኝ እና መጥፎ ገጽታው፤ በሀገሪቱ ውስጥ ትንሽ ማበብ ጀምሮ የነበረው የሲቪክ ማህበራት እንቅስቃሴን ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ ማጥፋቱ ነው፡፡ በጣም አዳክሞታል፤ አደብዝዞታል፡፡

ግን በተፈጠረው አዲስ የፖለቲካ ምዕራፍ ይሄ መልሶ ሊያገግም፣ ሊያቆጠቁጥ፣ ሊያብብ እና ሊጠናከር የሚችልበት ዕድል ተፈጥሯል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱና ወሳኙ፤ አሁን ያነሳነው የሕግ ማዕቀፉ የመሻሻል ጉዳይ ነበር፡፡ ትልቁ እንቅፋት የሕግ እና የፖሊሲ ገደቡ ነበር ፤ እሱ ሙሉ በሙሉ ተሻሽሎ፣ እጅግ በጣም ደጋፊ በሆነ ሕግ ተተክቷል፡፡ ከዚህ የተነሳ ድርጅቶች ሥራቸውን በአዲስ መልክ ማሰብ ጀምረዋል፤ አዳዲስ ድርጅቶችም እየተመዘገቡ ነው፡፡

የተሻለ ዕድል አለ፤ ባለፉት ዓመታት በተወ ሰዱት እርምጃዎች ይህ ዘርፍ በጣም ተዳ ክሞ ስለነበረ፣ በደንብ እንዲያገግም ልዩ እገዛ ያስፈልገዋል፡፡ በመንግሥት በኩል ሕግ ማውጣቱ አንድ ትልቅ ዕርምጃ ነው፤ ግን በዛ ብቻ ማቆም የለበትም፡፡ ሴክተሩ እንዲጠነክር ልዩ ልዩ ዓይነት እገዛዎችና ድጋፎች ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ እኔ ራሴ በዚህ በምሰራበት የኢትዮጵያ ሰብኣዊ መብት ኮሚሽን አማካይነት በተለይ በሰብኣዊ ጉዳይ ላይ አተኩረው የሚሰሩ ሲቪክ ማኅበራትን ለማገዝ ራሱን የቻለ ፕሮግራም እንነድፋለን ብለን እናስባለን፡፡

አቅምን የመገንባት፣ ክህሎታቸውን የመመ ርመር፣ አባላቶቻቸውን የማስፋት ሥራ እንዲሰሩ አቅማችን የፈቀደውን ሁሉ ከማድ ረግ ወደ ኋላ አንልም፡፡ የኢትዮጵያ ሰብኣዊ መብት ኮሚሽን ከሲቪክ ማኅበራት ጋር በጣም የቅርብ አጋር ሆኖ የሚሰራበትን ሂደት ነው የማልመው፡፡ ሲቪክ ማኅበረሰብ የሚለው ጽንሰ ሃሳብ በተለምዶ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ሚዲያን፣ የትምህርት ተቋማት፣ በኃይማኖት ሥር የሚቋቋሙ ልዩ ልዩ ማህበረሰቦችን እና ስብስቦችን ጨምሮ ሁሉን ያቀፈ ሕብረት ተፈጥሮ እንዲጠናከር ነው የምንፈልገው፡፡

እኔ እንደሚመስለኝ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ካለው ውስብስብ ነገር እና የፖለቲካ ክረት አኳያ ምናልባትም በጣም የሚጠቅመው እንደዚህ ዓይነት የሲቪል ማኅበራት የበለጠ ማደግና መጎልበት ነው፡፡ በተለይ ከብሔር



ዶ/ር ዳንኤል በቀለ

ፖለቲካ ውጥረት ነፃ የሆኑ የሲቪክ ማኅበራት መስፋፋት፣ መጠንከር እና መጎልበት አለባቸው፡፡ እዚህ ላይ ትኩረት ሰጥተን እንሰራለን፡፡ ለዴሞክራሲም ሆነ ለሰላም፣ ለእድገትም ሆነ ለብልጽግና የሚበጀው ይሄኛው አካሄድ ነው፡፡

**ግዮን፡- ከለውጡ በኋላ ኢትዮጵያውያንን ያላቀሰ፣ የነበረውን ሥርዓት ግፈኛነትም በተግባር ያጋለጠ፣ የሰብኣዊ መብት ጥሠት የተፈፀመባቸውን ሰዎች ቃለ ምልልስ ያካተተ፤ ዘጋቢ ፊልም ተላልፈው ነበር፡፡ ፕሮግራሞቹን ተመልክተው ከነበረ፣ እርስዎ ብዙ ዓመት የደከሙበት ጉዳይ ነውና ምን ተሰማዎት?**

ዶ/ር ዳንኤል፡- የተለያዩ ዶክመንተሪ ፊልሞች ስናይ ስለነበረ፣ በትክክል የትኛውን እንደሆነ ርግጠኛ ባልሆንም፤ ብዙዎቹ ዶክመንተሪዎች የንፁሃን ዜጎችን በደል፣ የሥርዓቱን ግፈኛና አምባገነንነት ያሳዩ ናቸው፡፡ ቀደም ሲል ሥልጣን ላይ የነበረው አስተዳደር በጣም ዘግናኝ፣ አሳዛኝ እና ከባድ የሰብኣዊ መብት ጥሰቶችን ይፈፅም እንደነበር ይታወቃል፡፡ ራሴም በተወሰነ መጠን ጉዳተኛ ሆኜ ችግሩን ተመልክቼዋለሁ፡፡ ምን ያህል ተገቢ ያልሆነ ሥራ ሲሠራ እንደነበር በፊትም ስለማውቅ ነው ከጓደኞቼ ጋር እታገል የነበረው፡፡

በዶክመንተሪዎቹ የተላለፈው በሙሉ የሚያሳዝን ታሪካችን ነው፡፡ ዋናው ነገር ከዚህ ወዴት እንሄዳለን? ነው፡፡ ተስፋ የማደርገው አሁን የተፈጠረውን ዕድል በጥበብ፣ በማስተዋል እና በትዕግሥት መጠቀም ከቻልን፣ መጻኢው ጊዜ ብሩህ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ለማየት የምንፈልጋቸው ለውጦች በአንድ ጀንበር ወይም በአጭር ጊዜ ሊመጡ የሚችሉ አይደሉም፡፡ የምናወራው ስለ ተቋም ግንባታ ነው፤ ተቋም መገንባት ማለት ደግሞ ለረዥምም ጊዜ ሥራ የሚያገለግሉ መሰረቶችን መጣል ነው፡፡

ይህን ስል ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያ የሰብኣዊ መብት አያያዝ ከዚህ በፊት ስናውቀው ከነበረው ሙሉ ለሙሉ ተለውጦ እናየዋለን ማለት አይደለም፡፡ ልዩ፣ ልዩ ዓይነት የሰብኣዊ መብት ጥሰቶችን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ማየታችን እንቀጥላለን፡፡

**ግዮን፡- እንዲህ ዓይነት የሰብኣዊ መብት ጥሰቶች ሲከሰቱ እርስዎ ምን ዓይነት ዕርምጃዎችን ለመውሰድ አስበዋል?**

ዶ/ር ዳንኤል፡- የአሁኑ የኢትዮጵያ ሰብኣዊ መብት ኮሚሽን ይለያል፤ እንደከዚህ በፊቱ የሰብኣዊ መብት ጥሰት ተፈፅሞ ሊደበቅ አይችልም፡፡ ያጣራል፣ ያረጋግጣል፤ አደባባይ ላይ እንዲወጣ ያደረጋል፡፡ ያጠፉ ሰዎችም በሕግ እንዲጠየቁ ይሠራል፤ ያጠፉ ሰዎች በሠሩት ሥራ እንዲያፍሩበት ይደረጋሉ፤ ሌሎችም ትምህርት እንዲወስዱበት ትኩረት ሰጥተን እንሰራለን፡፡

በዚህ ዓይነት አካሄድ ቀስ በቀስ የሰብኣዊ መብት ጥሰትን እየቀነስን እንሄዳለን ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ግን አሁን ላይ በአጭር ጊዜ ወይም በአንዴ የሰብኣዊ መብት አያያዝ ይቀየራል ብዬ አልጠብቅም፡፡ የምመኘውና እና የምንፈልገው ነገር ምንም ዓይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰት የሌለባት ሀገር እንድትኖረን ነው፡፡ ግን እውነታው ያ አይመስለኝም፤ ስለዚህ ተስፋ የምናደርገው እየቀነስን መምጣቱ ላይ ነው፡፡ ያን ለማሳካት ደግሞ በአንድ በኩል ግንዛቤ ማስፋት፣ ማስተማር እና አቅም የመገንባት ሥራ መሠራት አለበት፡፡ ጎን ለጎን የምርመራ፣ የማጋለጥ እና ተጠያቂነትን የማረጋገጥ ሥራ ማካሄድም ግድ ይላል፡፡

እነዚህ ላይ በቀዳሚነት እንሰራለን፤ አሁን ከሌላው ጊዜ የሚለየው ይሄንን ለመስራት የሚያስችል ዕድል አለ፡፡ ይህ ማለት ሙሉ ለሙሉ ከእንቅፋት ነፃ ነን ማለት አይደለም፡፡ በሰብኣዊ ጥሰት የምትከሳቸው እና የምትጠይቃቸው ሰዎች ብዙ ጊዜ ድርጊቱን ፈፅመናል ብለው አያምኑም፡፡ ይክዳሉ፣ ይከራከራለሉ፣ አልያም ለማፈን ይሞክራሉ፡፡ ስለዚህ ይሄንን ሁሉ እየተቋቋምን፣ ማሳወቅ፣ ማስተማር፣ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ መቻል ይኖርብናል ማለት ነው፡፡

**ግዮን፡- ባለፈው ሥርዓት የሰብኣዊ መብት ጥሠት ፈጽመው የተደበቁ ባለሥልጣናትና የጸጥታ ሃይሎች ለሕግ የሚቀርቡበትን ጉዳይ በተመለከተስ የእናንተ ተቋም ድርሻው ምንድን ነው?**

ዶ/ር ዳንኤል፡- ያለነው የሽግግር ወቅት ላይ ስለሆነ ባለፈው የፖለቲካ አስተዳደር የተፈፀሙ የሰብኣዊ መብት ጥሰቶችስ ምን ይደረጋሉ? የሚለው ራሱን የቻለ ትልቅ ጥያቄ ነው፡፡ እንደምታውቁት መንግሥት ያንን በሚመለከት የሰላም እና የእርቅ ኮሚሽን አቋቁሟል፤ በዛ አማካይነት ቢያንስ እውነቱ እንዲወጣ ይደረጋል የሚል ተስፋ አለ፡፡ ጉዳተኞችም ይካሳሉ፣ ይጠገናሉ ተብሎም ተስፋ ይደረጋል፡፡

ከዚህ በፊት የነበረውን የሰብኣዊ መብት ጥሰት እንዲፈፀም ምቹ ሁኔታ ፈጥረዋል ተብለው የታመነባቸው ሕጎች እና ተቋሞችም መሻሻል አለባቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ ሥራዎች ውስጥ የእኛም ኮሚሽን ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር አብሮ በመሥራት የራሱን አስተዋፅኦ ያደርጋል ብዬ አምናለሁ፡፡

አንደኛ እውነትን በማውጣት እና በማረጋገጥ፣ ሁለተኛ ተጠያቂነትን እና ፍትህን በማረጋገጥ፣ ሦስተኛ የተጎዱ ወገኖች እንዲታገዙ በማድረግ፤ ከዚህ በፊት የነበሩና ተገቢ ያልሆኑ ሕጎች፣ ፖሊሲዎች፣ አሠራሮች እና ተቋሞች እንዲሻሻሉ እንሰራለን፡፡ እነዚህ አራት ግቦች ወሳኝ ስለሆኑ፣ ተሳትፏችን በዚህ ዙሪያ ይሆናል፡፡

**ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡**

## “የተደበቀው ማስታወሻ”

# የአገር አንድነት አደጋ ላይ በወደቀበት ወቅት




ጌታቸው ስሜ (ኢንግላንድ)

ለአገራችን አንድነት መሰረት የሆኑ ምሰሶዎች ከመቼውም ጊዜ በላይ እንዲናዱ እጅግ በሚደከምበት ወቅት፤ የመከፋፈልና የጥላቻ አየር በሚነዛበትና ጎሰኝነት እንደእንዝርት በሾረበት በአሁኑ ወቅት እንደ አገር ያቆሙንን ጥልቅ እሴቶች ማንሳትና ማነቃቃት ወሳኝና ቁልፍ ተግባር ነው፡ ፡ ለዚህ ደግሞ እንደ ማነቃቂያ ይሆናል ያልኩት ‹‹The Memoir of the Italian - Ethiopian war of 1935- 36›› በሚል የሚታወቀውን መጽሐፍ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ‹‹የተደበቀው ማስታወሻ›› በሚል ወደ አማርኛ የተተረጎመ ሲሆን፤ በተደጋጋሚ ከሚነበቡና ተወዳጅ ከሆኑ የታሪክ ዘገባ መጽሐፍት አንዱ ነው ማለት ይቻላል፡ ፡ እነዚህ ለሀገር የተደረጉ ተጋድሎዎችን የሚያወሱ መጽሐፍት ፋሺስት ድል የሆነበት ቀን ሲቃረብ ብቻ መዘከር የለባቸውም፡ ፡ ለዛሬው እኛነታችን እዚህ መድረስ የተከፈለውን በደምና አጥንት የዋጀ መስ ዕዋትነት የሚያወሱ ድርሳናት ናቸው፡፡




የተጠቀሰው መጽሐፍ ደራሲ ዶ/ር ሃራልድ ናይስተሮም፣ በቀድሞዋ ኢትዮጵያ ግዛት ‹‹በለሳ›› በሚባል ቦታ (በአሁኗ ኤርትራ) ከሚሲዮናውያን ሲዊዲን ዜጎች የተወለደ ነው፡፡ ሃራልድ እንደ ኢትዮጵያዊ አድጎ እንደ ኢትዮጵያዊ ኖሮ ያለፈ ታላቅ ሰው ነው፡፡ ሃራልድ በፋሺስት ወረራ ወቅት አርበኞችን ሲያክም የነበረ ባለውለታም ነው፡፡

አንዳርጋቸው ፅጌ ‹‹ትውልድ አይደናገር፤ እኛም እንናገር›› በሚል ርዕስ ያሳተመውን መፅሀፍ አስመልክቶ ሲናገር ‹‹በአገራችን የወረራና የጦርነት ታሪኮች የተራው ዜጋና የሴቶች ታሪክ አልተተረከም›› ሲል ይከራከራል፡፡ በተወሰነ መልኩ እውነትነት ቢኖረውም ፤ በዚህ መፅሀፍ ግን ምንም እንኳ የዋናው ታሪክ ማጠንጠኛ ባይሆንም የሴቶችና የወጣቶች ተሳትፎ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል ማለት ይቻላል፡፡



የተደበቀው ማስታወሻ መፅሐፍ (ከላይ የመፅሩ ሽፋን) ከታች ደራሲው

ዶ/ር ሃራልድ ናይስተሮም

በዓለም ላይ ጥሩ ተዋጊዎችና የማይሸነፉ አድርገው ራሳቸውን እንዲቆጥሩ አድርጓቸዋል ይለናል፡፡ ከመጽሐፉ እንደ ማሳያ የ80 ዓመቱ አዛውንት ፊታውራሪ አሉላ ከደጃች አያሌው ጦር ጋር የዘመቱበትን ታሪክ ያስቀምጣል፡፡ እኚህ አርበኛ ከ40 ዓመት በፊት በተመሳሳይ መልኩ ፋሽስትን ለመዋጋት አድዋ የዘመቱ ናቸው፡፡ የእኚህ አርበኛ ፍላጎታቸው በዚህ የተቀደሰ ጦርነት ተካፍለው በመሰዋት ገነት መግባት ነው፡፡ በዚህም ‹‹አፍጋጋ›› በተባለው ጦርነት ከፊት መስመር ሆነው ተዋግተዋል፡፡ አስገራሚው ነገር ግን በጦርነቱ ተሳትፈው ሳይሞቱ በመትረፋቸው ከጦሩ ጋር ሲመለሱ በውጊያው አለመሰዋታቸው ያንገበግባቸውና ይከፋቸው የነበረ መሆኑ ነው፡፡

በርካታ የውጪ ሰዎች በሁለተኛው የፋሺስት ወረራ ላይ የየራሳቸውን ምልከታና ዘገባ ቢጽፉም፤ የዶ/ር ሃራልድ ግን ይለያል ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ሃራልድ ኢትዮጵያ ተወልዶ አማርኛውን እንደ እናት ቋንቋው ይናገራል፤ ይፅፋል፡፡ እስከ 22 ዓመቱ ኢትዮጵያ አድጎ ከዚያም ሲዊዲን ሄዶ ህክምና ተምሮ አገሩን ለማገልገል ተመልሶ የመጣ ሰው ነው፡፡ ስለዚህም የኢትዮጵያውያንን ሥነ ልቦና በሚገባ ያውቃል፡፡ ስለ ኢትዮጵያውያን አስተሳሰብ፣ አቋምና ፅናት ሲናገር እቅጩን ነው፡፡ ምክንያቱም እሱ ራሱ ኢትዮጵያዊ ሥነ ልቦና ነበረውና፡፡

እንደማሳያ ከሚያነሳልን የኢትየጵያውያን አስገራሚ ሥነልቦናዊ ጥንካሬ መካከል ‹‹አቢሲኒያውያን›› በጦርነት ከቆሰሉ በኋላ ስቃይ የመቋቋም ችሎታቸውን ነው፡፡ ሲተርክም ‹‹በአንድ ውጊያ ለማደንዘዥ የሚሰጥ መድኃኒት አንድ ኪሎ ብቻ ነው ያለኝ፡፡ አቢሲኒያውያን ደግሞ ለቀላል የቀዶ ህክምና ስራ ማደንዘዣ አይፈልጉም ነበር፡፡ በቀኝ ጆሮው በኩል የቆሰለ ወታደር ጥይቱ ከሳይኛው አገጭ ስር አልፎ ከጆሮ መግቢያ በኩል ባለ ማስቶይድ በሚባል አጥንት ውስጥ ተቀርቅሯል፡፡ ጥይቱን ለማውጣት ማደንዘዣ መስጠት ነበረብኝ ፡፡ ወታደሩ ማደንዘዣውን አልፈለገውም፡፡ ጥይቱን ለማውጣት በቢላዋ በጆሮው ቀዳዳ በኩል መቁረጥ እንዳለብኝ ስነግረው አልፈለገም፡፡ ቢላዋ አደገኛ ነው አለኝ፡፡ ስለዚህ በጥርስ መንቀያ ጉጠት ለመንቀል ህመሙን መቋቋም አትችልም ስለው እንደሚችል ነገረኝ፡፡ በጥርስ መንቀያ ጥይቱን ለማውጣት ቆዳው ተሰንጥቆ ሲለጠጥ፣ እንዲሁም የተቆረጠው ሰውነቱ ሲሰፋ ወታደሩ ምንም ዓይነት የህመም ስሜት አላሳየም፡፡ ልክ ቀዶ ጥገናው እንዳለቀ ‹በጣም ጥሩ ነው› የሚል ቃል ብቻ ነው የወጣው››

አፀደ የተባለች የስምንት ዓመት ህፃን ከአዲስ አበባ እስከ ጎንደር ያለውን ሰባት መቶ ኪሎ ሜትር ከወላጆቿ ጋር በእግሯ ተጉዛለች፡ ፡ ይህችን ህፃን ይዘው የሄዱት አቶ ማሞ ደግሞ ከአዲስአበባ ወደ ደጃዝማች አያሌው ብሩ ጥይት እንዲያደርሱ የተላኩ ናቸው፡፡ ባለቤታቸውም አብረው ዘምተዋል፡፡ የአቶ ማሞ ባለቤት ከባሏ ጋር በጦርነት ቢቆስል ልታስታምመው፤ ቢሞት ልትቀብረው አብራው የዘመተች ናት፡፡ በጊዜው ከአርበኞች ጋር ለስንቅ ዝግጅት ብቻ ሳይሆን በዓውደ ውጊያ ወቅት አርበኞች ሲቆስሉ ለማንሳትና ሲሞቱ ለመቅበር ከሚወዱት ጋር አብረው የዘመቱ ሴቶች ቁጥር ቀላል አልነበረም፡፡ ትንሽዋ አፀደም ከዚያ ሁሉ የፋሺስቶች የመርዝ ጋዝ ጥቃትና የከባድ መሳሪያ ውርጅብኝ በተዓምር ተርፋ፣ ጦርነቱ ሲያከትም ከእነ ዶ/ር ሃራልድና ከደጃች አያሌው ጦር ጋር ልትመለስ ችላለች፡፡

ዶ/ር ሃራልድ ናይስተሮም በመጽሐፉ ሲተርክ ኢትዮጵያውያን በራሳቸው የሚተማመኑና ላመኑበት ነገር ወደ ኋላ እንደማይሉ፤ በሥነ ልቦናቸውም የተቀረፀው ነፃ አገር ሆኖ የመኖር እምነት የሚበጠስ እንዳልሆነ ይገልጻል፡፡ እንግሊዝና ፈረንሳይ መሬታቸውን እንደሚመኙ ነገር ግን ደፍረው እንዳላጠቋቸው ያነሳል፡፡ ይህ ደግሞ ኢትዮጵያውያንን

## ስፓሂዎች

ከሰሜን አፍሪካ ሊቢያ የመጡት ስፓሂ የሚባሉት በፋሺስቶች የሚመሩ ፈረሰኞች በአርበኞች ላይ ቀላል የማይባል ጉዳት አድርሰዋል፡ ፡ ‹‹ስፓሂ ደ ሊቢያ›› ተብለው ይጠራሉ፡፡ በወቅቱ ሊቢያ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ስለነበረች ፋሺስቶች እነዚህን ፈረሰኞች መልምለው በማዝመት በተለያየ ግንባር ከአርበኞች ጋር ተዋግተዋል፡፡ ፋሺቶች ከኤርትራ የመለመሏቸውን የባንዳ ጦር ጨምረው ነበር የሚያዘምቱት፤የሚዋጉት፡ ፡ ለምሳሌ ‹‹አሜዲዮ›› የተባለ የፋሺስት መኮንን እስከ አንድ ሺ የሚሆኑ ስፓሂ ፈረሰኞችን ወደ ኢትዮጵያ ይዞ መጥቶአል፡፡ በአፍጋጋ ጦርነት ላይ አርበኞች ከእነዚህ ስፓሂዎች ጋር ባደረጉት ጦርነት አዳክመዋቸው አዛዣቸውን አሜዲዮን አበሾቹ ከፈረስ ላይ አውርደው ለመግደል ያደረጉት የሚያስገርም ሙከራ አልተሳካም፡፡ አሜዲዮ ግን ለኢትዮጵያውያን ጀግኖች የነበረውን አክብሮት ‹‹A true story of Love and War in Abyssinia›› ለተባለው መጽሐፍ ደራሲ ለሰባስትያን ኦኬሊ ገልፆለታል፡፡

ስፓሂ ተዋጊዎች በፈረስ ውጊያ ወደር የላቸውም ተብሎ ይነገራል፡፡ ዶ/ር ሃራልድ በመጽሐፉ ሲተርክ ‹‹ስፓሂዎች ፈረሶቻቸው አንገት ላይ ▶

ተለጥፈው ሽምጥ ሲጋልቡ ልክ እንደ ራሺያ ኮዛኮች አስደናቂ ናቸው። ከኢትዮጵያውኑ ፈረሰኞች ጋር ያረጉት ፍልሚያ አስደናቂ ነው፡ ፡ ምክንያቱም የአቢሲኒያ ፈረሰኞች ራሳቸው ድንቅ የውጊያ ችሎታ አላቸው። የውጊያውን የተለያየ ደረጃ ስከታተል ተመስጬ ስለነበር ስለራሴ ምንም ሳላስብ ብቻዬን መቅረቴን አሳስተዋልኩም›› ይለናል። በሌላ በኩልም ከአካባቢው ተወላጆች የሚመለመሉና የሰለጠኑ የአስካሪስ ወታደሮች ‹‹የኢጣሊያ የቅኝ ግዛት የንጉሳዊ ጦር አባል›› ተብለው ይጠሩ እንደነበርም ይናገራል። በኤርትራ ብቻ ሳይሆን በሶማሊያም እንዲህ ዓይነት ተመሳሳይ ወታደሮች ነበሩ።

እዚህ ላይ ከዶ/ር ሃራልድ መጽሐፍ በተጨማሪ አንድ ተመሳሳይ ክስተት አለ፡ ፡ ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም ‹‹ትግላችን›› በሚለው መጽሐፋቸው ሶማሊያ ኢትዮጵያን ስለወረረችበት በሚተርከው የመጽሐፋቸው ክፍል በወቅቱ የሶማሊያ ፕሬዚዳንት ስለነበረው ሙሀመድ ሲአድ ባሬ አንድ ነገር ብለዋል። ሲአድ ባሬ ፋሺስት ኢጣሊያ በሶማሊያ ከመለመላቸው ወጣት ወታደሮች አንዱ ነው። በፋሺስት አዛገሮች በሚመራ ምልምል አገልጋይ ሰራዊት አባል ሆኖ በጂቡቲ በኩል በመግባት ከኢትዮጵያ ሰራዊት ጋር ተዋግቷል። ሲአድ ባሬ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ከደርግ አመራሮች ጋር በሚደራደርበት ወቅት የኢትዮጵያን የተወሰኑ ክፍሎች በደንብ እንደሚያውቃና ይህንንም ለማወቅ የቻለው የፋሺስት አሽከር ሆኖ ወደ ኢትዮጵያ በዘመተበት ወቅት መሆኑን ተረድቻለሁ ይሉናል ኮሎኔል መንግስቱ።

## ‹‹ሙጄሌ›› እና አርበኛ

‹‹ሙጄሌ›› የተባለው እግር የሚበላና የሚያጣምም ተባይ ወደ ኢትዮጵያ የገባው በፋሽስቶች ነው። ይህንንም ያደረጉት አርበኞችን ለመጉዳት በሚል ሲሆን፤ በሞያሌ በኩል ይዘው በመምጣታቸው ምክንያትም ስሚን ከሞያሌ ‹‹ሙጄሌ›› ተብሎ እንደተጠራ በተለያዩ ወገኖች ሲነገር ይሰማል። ዶ/ር ሃራልድ የሚነግረንን ስንሰማ ግን ከነበረው ይለያል። እሱ ‹‹ቡጄሌ›› ብሎ ይጠራታል፡ ፡ ‹‹ቡጄሌን የሚያመጡት ተባዮች በዓይን የማይታዮ ጥቃቅን ናቸው።

ከደቡብ አሜሪካ በ1880ዎቹ ወደ አፍሪካ የተዛመቱ ናቸው። ይህ ተባይ እንደ ቁንጫ መሳይ ሲሆን፤ ሴቴ ፆታ ያላት ቡጄሌ በእግርና በጣቶች ቦርቡራ በመግባት እንቁላሏን ትጥላለች። ብዙውን ጊዜ አርበኞቹንም ሆነ ሌላውንም ሰው እግራቸውን ታጠቃለች። አቢሲኒያውያን ተባዩን በመርፌ በማውጣት የተካኑ ናቸው። ችግሩ ግን ኢንፌክሽን ያስከትልና ያስቸግር ነበር። በዚህ ተባይ የተያዘ ሰው መራመድ ያቅተዋል። እኔ ራሴ በዙሁ በሙጄሌ ህመም አንድ ሳምንት የአልጋ ቁራኛ ሆኛለሁ። ጦርነቱ ለጥቂት ወራት ቢራዘም አንድ ሶስተኛ የሚሆነው ሰራዊት በቡጄሌ ምክንያት ለመዋጋት አይችልም ነበር›› ይለናል ዶ/ር ሀራልድ።

አርበኞች ቡጄሌን አማክለሽ ድንቁ ብለው እንደሚጠሯትና ስለሷም የተገጠመውን ሀራልድ እንዲህ ያስነብበናል።

አማክለሽ ድንቁ ነብስሽን አይመሬው

እግሬ ቆሞ ቀረ መሄድ እያማረው፤

ቡጄሌን በደንብ ፊልፍሎ ማውጣት ሳይቻል ሲቀር የሚገጠመውን ደግሞ

በዱማ መርፌ ቁልፍ ሲገፉኝ ሲገፉኝ

ባለ ደረባ ቤት ባለፎቅ አረጉኝ፤ በማለት ይነግረናል።

## እንዳባጉና

የደጃዝማች አያሌው ብሩ ጦር በእንዳባጉና ባደረገው ጦርነት ‹‹እንዳባጉና›› የተባለውን ቦታ ከፋሺስት ጣሊያን አስለቅቋል። በዚህ ውጊያ ታንክ የማረኩት የመጀመርያው አርበኛ ባለምባራስ ተሰማ ናቸው። ባላምባራስ ተሰማ በአርበኝነት በአምባ ጊዮርጊስ አካባቢ በጠላት ላይ ጉዳት አድርሰዋል። በዚህ ጀግንነታቸው የፊታውራሪ ማዕረግ አንደተሰጣቸውም ዶ/ር ሀራልድ በመጽሐፉ ጠቅሷል።

በጦርነቱ ካመለጡ የኢጣሊያ ወታደሮች አንዱ የሆነው አስር አለቃ ቡርና የሚባለው ወታደርም ታንኮቹ የማይረቡ ናቸው ብሎ እስከማማረር ደርሶ እንደነበርም ገልጹዋል። ይህንንም በሰባስትያን ኦኬሊ ‹‹A true story of Love and War in Abysinia›› ላይ ተጠቅሷል።

ዶ/ር ሀራልድ እንደሚለው ከፋሺስት ጣሊያን ጋር የመጀመርያውን ጦርነት ያካሄደው የደጃዝማች አያሌው ጦር ከሆነ፤ በዚህ ጦርነት ታንክ የተደመሰሰ ከሆነና ታንክ የማረከው የመጀመርያው ኢትዮጵያዊ ሊሆን የሚችለው ባላምበባራስ ተሰማ ነው። ይህንን ግን የታሪክ ባለሙያዎች ይነጋገሩበት ሲል ዶ/ር ሀራልድ ሀሳብ ይሰጣል። የፊታውራሪ ሽፈራውና የባላምባራስ ተሰማ ገድል ‹‹Haileselassie's War›› በሚለው የአንተኒ ሞክለ መጽሐፍ በተመሳሳይ መልኩ መጠቀሱንም ያስቀምጣል።

ሌላኛው ጉዳይ ደግሞ የአበሾች ከአውሮፕላን ራሳቸውን የመከላከል ጥበብና ጥንቃቄ እጅግ አስገራሚ መሆኑ ነው። ቀኑን ሙሉ ሰራዊቱም ሆነ ሌላውም የአውሮፕላኑን ጥቃት ሽሽጽ ተደብቆ ነው የሚውለው። ‹‹እንደዚህ ያለ የተጠናከረ የአውሮፕላን ጥቃት የመከላከል ስልት በአቢሲኒያውያን እንዴት ሊታወቅ ቻለ? ከዚህ በፊት የአውሮፕላን ጥቃት ምን እንደሆነ አያውቁም። እንዴት እንዳወቁ ወታደሮቹን ስጠይቃቸው መልሳቸው ‹‹ያሳወቁን ጀግናው ጌታችን ደጃዝማች አያሌው ናቸው። እኛ ምንም ነገር አናውቅም። አውሮፕላን አይተን አናውቅም። ነገር ግን አዛገሮችን እንደሚያውቁ ስለምናውቅ የታዘዝነውን መፈፀም ነው፡ ፡ ትዕዛዙን የማያከብር ወታደርም ሆነ ሌላ አገልጋይ በጦሩ ፊት አርባ ጅራፍ ይቀጣል።›› ሲል ዶ/ር ሀራልድ ያስረዳል።

## የከምባታ ጦር

በራስ ሙሉጌታ ሰራዊት ስር የነበሩ የከምባታ ተወላጅ ወታደሮች መቀሌ በሚገኘው የጣሊያን ካምፕ ዋሻ ብዙ ቀለብና ሌላም ንብረት እንዳለ ይሰማሉ። ከአዛገሮቻቸው ፍቃድ ሳይጠይቁ በሌሊት ሾልከው በፋሺስቶች ‹‹ፓውዛ›› የሚሽፈነውን አንድ ማይል ርቀት በደረታቸው ተለጥፈው በማሳለፍ ወደ ካምፑ ከመድረሳቸው በፊት ነጋባቸው። ይሁንና ካምፑ ጋ ሲደርሱ በሽቦ ዙርያውን ታጥሯል፡ ፡ መቁረጫ መሳሪያ ስላልነበራቸው ምን እንደሚያደርጉ ግራ ገባቸው።

አርበኞቹ ትንሽ ከተዋያዩ በኋላ በመቶዎች የሚቆጠሩ እጆች ከሽቦው ሥር ያለውን መሬት መቆፈር ጀመሩ። ብዙም ጊዜ ሳይፈጁ በቆፈሩት መሬት ስር እየተሳቡ ማለፍ ጀመሩ። ጠመንጃቸውን ትከሻቸው ለይ አድርገው፤ ጩቤዎቻቸውን በጥርሶቻቸው ነክሰው እየተሳቡ ጋራውን መውጣት ቀጠሉ፡ ፡ የዋሻውን ጋራ አንዱ በአንዱ ትከሻ መሰላል በመስራት በጩቤዎቻቸው ጠባቂ ፋሽስቶችን ጭጭ አረጓቸው። ዋሻው ወስጥ ገብተው ዱቄት፣ ስኳር፣ ዘይት ጥይቶችና ሌላም ጠቃሚ ነገሮችን ይዘው በመጡበት መንገድ ተመልሰው ሲሄዱ ቀን ስለሆነ ይታያሉ። በዚህ ሁኔታ ከሞት ሊያመልጡ አይችሉም።

ስለዚህም ያለው አማራጭ ቀኑን ተደብቀው በማሳለፍ ምሽት እስኪመጣ መጠበቅ ነው፡ ፡ ቀኑን ሙሉ ጥይት እየወረደባቸው ዱቄቱን መከታ አድርገው ዋሉ።

ምሽቱ ሲመጣ እየተሳቡ በመጡበት መንገድ ሳይሆን በጋራው በስተጀርባ አድርገው እያደቡ ሲሄዱ፤ በሽቦ ስለታጠረ በእጃቸው ቆፍረው ማለፍ ጀመሩ። የመጨረሻው ሰው ተስቦ ሲያልፍ ተነቃባቸው። ወዲያው የአውቶማቲክ መሳሪያና የመድፍ ውርጅብኝ ዘነበባቸው፡ ፡ ይሁንና እግሬ አውጭኝ ብለው መጠነኛ ጉዳት ደርሶባቸው ወደ ወገን ጦር ተመለሱ። ከጣሊያኖቹ የተዘረፈው ስንቅ በወቅቱ በችግር ላይ ለነበረው ጦር ወሳኝ ነበር።

ታሪክ ፀሀፊዎች ከዶ/ር ሀራልድ ጥቆማ በመነሳት የከምባታ አርበኞችን ታሪክ በመጽሐፍ መልክ ቢያስነብቡን የተሟላ ስዕል ይሰጠናል። ‹‹የሀበሻ ጀብዱ›› በሚል በቼክ ተወላጁ አዶልፍ ፓርለሳክ የተፃፈው መጽሐፍ ተወዳጅነትን ያገኘው ከሰላሴ ስለዘመተው አብቹ በስፋት በመተረኩ ነው።

## ባለውለታችን

ዶ/ር ሀራልድ ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት በአዲስ አበባ እስከ 105 ጋዜጠኞች ከመላው ዓለም ለመዘገብ ተገኝተው እንደነበር ጠቅሷል፡ ፡ በወቅቱ የፋሺስት ወረራን ኢትዮጵያውያኑ ለመዋጋት ያደረጉት ዘመቻ የዓለምን ቀልብ ስቦ እንደነበርም ያስረዳል።

ዶ/ር ሃራልድ ከጦርነቱ በኃላ ከባሌቤቱ ማርታ ሳፍል ጋር ጋብቻ ፈፅሞ ሁለት ልጆች አፍርተዋል። በ1928 ኢ.ኢ.አ የክብር ዘበኛ ሀኪምም ሆኖ ነበር። በዚህ ሙያውም ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ስትወር አገሩን ለመከላከል ከደጃች አያሌው ብሩ ጦር ጋር በመሆን ወገኖቹን በህክምና ታድጓል።

ሀራልድ ከጦርነቱ በኂላ ወደ ሲዊዲን በመመለስ እስከ 1945 በስዊዲን የህክምና ስራ ሲሰራ ቆይቷል። በ1945 ወደ ትውልድ ቦታው በመመለስ በአድዋ የመንግስት ሥራም ላይ ተሰማርቷል። ለ12 ዓመታት በአሰላ ሆስፒታል ከማገልገሉም በላይ የአሩሲ ጠቅላይ ግዛት የጤና ጥበቃ ቢሮ ሃለፊ ሆኖም ሰርቷል፡ ፡ አስራ ሁለት ቋንቋ በመናገር ችሎታውም ዝናን አግኝቷል። ሀራልድ ህይወቱ እስከታልፍ ድረስ በአዋሳ በሰራው ቤት ይኖር ነበር።

ይህ የአገር ባለውለታ ያየውንና የኖረበትን ታሪክ በመጽሐፍ መልክ አሳልፎልን አልፏል።


ይህን ‹‹የተደበቀው ማስታወሻ›› የሚሰውን ድንቅ መጽሐፍ የዘመኑ ወጣቶች ቢያነቡት እጅጉን ይጠቀማሉ። በዚህ አጋጣሚ ‹‹የተደ በቀው ማስታ ወሻ›› በሚል ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ የመለሱትን ዶ/ር ገበየሁ ተፈሪና አቶ ደስአለኝ አስመ እንዲሁም ከስዊዲንኛ ወደ እንግሊዘኛ የመለሱት ዶ/ር ቶማስ ፒ ኮልማን ሊመሰገኑ ይገባል።



ብሩክ መኮንን

# ካርል ጉስታቭ ቮን ሮሰን

## ስዊዲናዊው የኢትዮጵያ አየር ኃይል መስራች!



ካርል ጉስታቭ ቮን ሮሰን

በብዙዎች ዘንድ አወዛጋቢ ስብዕና እንዳለው የሚነገርለት፣ ለኢትዮ ጵያና ኢትዮጵያውን ልዩ ፍቅር እንደነበረው የሚመሰከርለት ካርል ጉስታቭ ቮን ሮሰን የአየር ኃይላችን መስራች እና የኢትዮጵያ ባለውለታ የነበረ ሰው ነው።

ካርል ጉስታቭ ቮን ሮሰን በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቀ ሀገር አሳሽ፣ የስዊድን ናሽናል ሶሻሊስት ብሎክ መሥራች ከነበሩት ኮንት ኤሪክ ቮን ሮሰን እና የናዚ ጀርመን አየር ኃይል አዛዥ ከነበሩት የሔርማን ጎሪንግ የእህት ልጅ ከሆኑት ባሮንስ ሜሪ ፎክ በማዕከላዊ ስዊድን ኦገስት 19 ቀን 1909 ነው የተወለደው።

ሕፃኑ ቮን ሮሰን ገና ከልጅነቱ አንስቶ ነበር መኪናዎች እና አውሮፕላኖች የመንዳትና የማብረር ልዩ ፍላጎት ያደረበት። በዚህም የተነሳ በአዳሪ ትምህርት ቤት ትምህርቱን በተከታተለባቸው ዓመታት፣ ከትምህርት ቤቱ ተማሪዎቹ በሙሉ ዝቅተኛ ውጤትን ያስመዘገበ ሰነፍ ተማሪ ሆኖ ነበር።

እ.ኤ.አ ከ1920 እስከ 1926 በአዳሪ ትምህርት ቤቱ የነበረውን ቆይታ እንዳጠናቀቀ፣ በቀጥታ ኤ.ቢ.ኤር ማትሪል የአውሮፕላን መካኒኮች ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በመግባት የአውሮፕላን አብራሪነት እና የጥገና ሥራዎችን ለሶስት ዓመት ከተማረ በኋላ በ1929 ተመረቀ። የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ግዳጁን ለመወጣት በስዊድን ጦር ኃይል ውስጥ በነበረው ቆይታ፣ የጦር ኃይሉ የመጓጓዣ ክፍል ውስጥ በመካኒክ ሙያው በማገልገሉ የምክትል መቶ አለቃነት ማዕረግ አግኝቶ ግዳጁን ለማጠናቀቅ ችሏል።

የስዊድን አልጋወራሽ ከኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት ጋራ በነበራቸው ወዳጅነት ምክንያት የቤኔቶ ሞሶሎኒ ፋሺሽት ኢጣልያ ኢትዮጵያን በግፍ መውረሯን እና በወረራው እያደረሰችው ያለውን አሰቃቂ የአየር ድብደባ በማውገዝ ንግግር ሲያደርጉ በአጋጣሚ በስፍራው ተገኝቶ የነበረው ወጣቱ ቮን ሮሰን ወደ ኢትዮጵያ በመጓዝ ለኢትዮጵያ ሊሞት ወሰነ።

በርካታ ሲውድናዊያን የሕክምና ባለሙያዎች የሚገኙበት የሲውዲን ቀይ መስቀል የአንቡላንስ ቡድን አባል በመሆን ወደ ኢትዮጵያ ሲጓዙ፣ ቮን ሮሰንም የአምቡላንስ ቡድኑ መለስተኛ የመጓጓዣ አውሮፕላን አብራሪ ሆኖ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ቻለ።

ኢትዮጵያ ላይ ወረራ የፈፀመችው ኢጣልያ፣ በአውሮፕላን በታገዘ የመርዝ ጋዝ ጥቃት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ለጉዳት ስትዳርግ፤ ቮን ሮሰን በመርዝ ጋዙ የተለበለቡ ኢትዮጵያውያንን ሕይወት ለማትረፍ፣ የራሱን ሕይወት ለአደጋ አጋልጦ ተጎጂዎችን በአነስተኛ አውሮፕላን በማጓጓዝ አኩሪ ተግባርን ፈጽሟል።

ቮን ሮሰን አንድ ወቅት "በዚያ ቀውጢ ሰዓት ኢትዮጵያውያን የነበራቸውን ጂላቸር እና በጣት የሚቆጠሩ አውሮፕላኖች ከሚያበሩት ሚሽካ ባቢቼም አስፋው እና አሊ. ዌበር ጋር ጥብቅ ወዳጅነት መስርቼ ነበር። አንዳንዴም የጦር መማሪያ ጥይቶች፣ በአማርኛ የተዘጋጁ ስለጦርነቱ፣ ስለአየር ድብደባው፣ ስለቦንቡ፣ የመርዝ ጋዙ እና ስለታንክ ምንነት የሚያሳውቁ ጽሑፎችን፣ የሕክምና ባለሙያዎችን እና መድኃኒት ጭነው አውሮፕላን ሲያበሩ አብሬያቸው እጓዝ ነበር" ሲል ተናግሯል።

ቮን ሮሰን በኢትዮጵያ ለአንድ ዓመት ያህል በነበረው ቆይታ የኢጣልያ ጦር የበላይነቱን በመቀዳጀቱ ምክንያት ከስዊዲናውያኑ ባልደረቦቹ እና ከሌሎች የቀይ መስቀል የአምቡላንስ ቡድን አባላት ጋራ ከሀገር ለመውጣት ተገዷል። ይህንንም ተከትሎ ወደ ሀገሩ ስዊድን በመመለስም ስቴና ማሪያ ትሬሳ ከተባለች ጉብል ጋር ትዳር መስርቷል።

በኢትዮጵያ በነበረው ቆይታ ያሳየውን የአብራሪነት ችሎታውን በሚገባ የተመለከቱ ለተመሳሳይ እርዳታ ወደ ኢትዮጵያ ተጉዘው የነበሩ ሆላንዳውያን ወደ ሀገራቸው ሄዶ በዚያ ለታዋቂው "ኬል ኤል ኤም" አየር መንገድ በአብራሪነት እንዲሰራ ሁኔታዎችን አመቻቹለት።

በዚህ መሠረት ካርል ጉታቭ ቮን ሮሰን በኬል ኤል ኤም ውስጥ በመቀጠር፤ በሆላንድ የሀገር ውስጥ በረራ፣ እንዲሁም ከአምስተርዳም ወደ ደቾ "ኢንዲያ" በተባለች የሆላንዶች ቀኝ ግዛት በመዘዋወር ለዓመታት በአብራሪነት ሲሠራ ቆይቷል።

የኹለተኛው የዓለም ጦርነት መቀስቀስን ተከትሎ ከኬል ኤል ኤም የአየርመንገድ ኩባኒያ ዋና ሥራ አስኪያጅ አልበርት ፔስማን ጋር በመጣመር፤ ለፊላንድ አየር ኃይል አንድ ዳግላስ ዲሲ 3 አውሮፕላንን፣ የሆላንድ ጦር ሲገለገልባት የነበረች እና ያረጀች የቅኝት አውሮፕላን በማሻሻጥ የፊላንድ አየር ኃይል እንዲጠናከር አድርጓል። ከዚህ በተጨማሪ በፊላንድ የአየር ክልል በተካሄዱ የአየር ውጊያዎች አውሮፕላን በማብረር የጦርነቱ ተከፋይ ሆኗል። ለዚህ ተግባሩም የፊንላንድ መንግሥት የአብራሪነት ማረጋገጫ ባጅ፣ የፊላንድን የነፃነት መስቀል እና ሦስተኛ ደረጃ ኒሻንን ሸልሞታል።

እ.ኤ.አ በ1940 ጀርመን ሆላንድን ስትወር ቮን ሮሰን የሚሠራበትን ኤል.ኤል.ኤም አየር መንገድን ለቀቀ፣ ኤዚ ኤር ትራንስፖርት ለተባለ ኩባኒያ፣ የመንገደኞች ማመላለሻ አውሮፕላን አብራሪ ሆኖም ሠርቷል።

በሀገሩ ስዊድን ኤዚ ኤር ትራንስፖርት ኩባኒያ የመንገደኞች አውሮፕላን አብራሪ ሆኖ ሲሠራ ባሳየው ብቃት እና የተዋጣለት የአብራሪነት ችሎታው የስዊድን መንግሥት በአስቸኳይ ወደ ስዊድን አየር ኃይል አዘዋውሮት፣ በአየር ኃይሉ የአብራሪዎች ማሠልጠኛ ተቋም በመምህርነት እንዲሠራ አደረገው።

ኮንት ካርል ጉስታቭ ቮን ሮሰን በሲውዲን አየር ኃይል በሻምበልነት ማዕረግ ተሰጥቶት በሠራባቸው ጊዜያት፣ ከአስተማሪነቱ በተጨማሪ በተለያዩ ጊዜያት የስለላ ተግባራትን ለማከናወን ወደ ተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት የአየር ክልል አውሮፕላን እያባረረ በመግባት መረጃ የመሰብሰብ ተግባርም ያከናውን ነበር።

ሆኖም በ1944 (እ.ኤ.አ) መጨረሻ ላይ፤ በስቶክሆልም የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ፣ "ካርል ጉስታቭ ቫን ሮሰን ከናዚው የአየር ኃይል አዛዥ ከሔርማን ጎሪንግ ጋራ በመገናኘት፤ በርሊን ድረስ በመዝለቅ ናዚዎች ከአይሁዶች እና ከተለያዩ ሀገራት ባለፀጋዎች የዘረፏቸውን

ብዛት ያለው ገንዘብ፣ የተለያዩ ውድ ዋጋ የሚያወጡ የሥነ ጥበብ ሥራዎችን እና ጌጣጌጦችን ወደ ስዊድን በማጓጓዝ የናዚዎችን የዝርፊያ የተከማቸ ሐብት በማሸሽ፣ ሕጋዊ ለማድረግ ይንቀሳቀሳል" የሚል መረጃ ለስዊድን መንግስት አሳወቀ።

መረጃው ክፉኛ ያስደነገጣቸው የስውዲን ከፍተኛ አካላት ካርል ጉስታቭ ቮን ሮሰን በጥርጣሬ ስለተመለከቱት፣ ከሥራው አሰናብተው በአይነ ቁራኛ እንዲጠበቅ አደረጉ፤ በዚህም ምክንያት ለወራት ሥራ ፈትቶ ለመቀመጥ ተገድዶ ነበር።

የኹለተኛው ዓለም ጦርነት እንደተጀመረ ነፃነቷን የተቀዳጀችው እና "ኹለተኛዋ ሀገሬ" የሚላት ኢትዮጵያ፣ ንጉሠ ነገሥቷ በድል አድራጊነት ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ስልጣናቸውን እንደጨበጡ ወዲያውኑ ነበር ስዊድናዊው ኮንት ካርል ጉስታቭ ቮን ሮሰን ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጣ ጥሪ ያቀረቡለት።

የኢትዮጵያ መንግሥት ጥሪን ተቀብሎ በፍጥነት ወደ ሀገራችን የመጣው ቮን ሮሰን ተቀብለው ያነጋገሩት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የኢትዮጵያን የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲያስጀምር ፍላጎት እንዳላቸው እና ይህንንም በበላይነት እንዲሠራ አዘዙት።

ካርል ጉስታቭ ቮን ሮሰን የተሰጠውን ሓላፊነት ወደ ተግባር ለመቀየር ወደ ሀገሩ ወደ ስዊድን በማምራት ከስዊድን አየር መንገድ ኩባኒያ እና ሲፋ ኢንተርኮንትኔንታል ሉፋትራፋክ ኤቢ ከተሰኘ ኩባኒያ ጋራ ግኑኝነት በመፍጠር፤ የኢትዮጵያ ሲቪል አቬየሽን ተቋምን፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድን፣ የኢትዮጵያ አየር ኃይልን ለማቋቋም የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ጀመረ።

ሆኖም የአሜሪካው ትራንስ ወርልድ ኤር ላይንስ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ ባደረገው ስምምነት የኢትዮጵያ አየር መንገድን ለማቋቋም እንቅስቃሴ በመጀመሩ፣ ንጉሡ ቮን ሮሰን የኢትዮጵያ አየር ኃይልን በማቋቋም ላይ ብቻ እንዲያተኩር ተወሰነ።

ድርጊቱ በወቅቱ ያበሳጨው ቢሆንም፣ የተሰጠውን የኢትዮጵያ አየር ኃይልን የማቋቋም እንቅስቃሴውን ቀጥሎ በስዊድን አየር ኃይል ዋና አዛዥ ያልተቋረጠ ድጋፍ፣ የኢትዮጵያ አየር ኃይልን በሦስት ዘርፎች ማለትም በተዋጊ ቦንብ ጣይ አውሮፕላን ስኳድን ፣ በኹለተኛ ደረጃ የቅኝት የስለላ በረራዎችን የሚያካሂድ ክፍል፣ ሦስተኛውን የመጓጓዣ እና የሎጀስቲክ ዘርፍ አድርጎ አዋቀረው።

በሜይ 1947 ከሲውዲን መንግሥት በተገኘ ድጋፍ፣ ለኢትዮጵያ አየር ኃይል የመጀመሪያዋን ሲውዲን ሠራሽ ኤስ.ኤ.ሌ 914 ሳፊር አውሮፕላንን ከስቶክሆልም ከተማ ወጣ ብሎ በሚገኘው በሮማማ የአየር ኃይል ምድብ በማስነሳት፣ ራሱ ኮንት ካርል ጉስታቭ ቮን ሮሰን ለ31 ሰዓታት 6220 ኪሎ ሜትር ርቀትን የሸፈነ በረራ በማድረግ ወደ አዲስ አበባ ይዞ መጣ።

ከዚህ በኋላ ነበር የኢትዮጵያ አየር ኃይል በጥቂት ስዊድን ሠራሽ አውሮፕላኖች፣ ከ100 በላይ የሚሆኑ የስዊድን የበረራ፣ የጥገና፣ የቴክኒክ ባለሙያዎች እና አሰልጣኞችን በመያዝ ሥራውን የጀመረው።

የኢትዮጵያ አየር ኃይልን የማደራጀቱ ሥራ ላይ የአንበሳውን ድርሻ የወሰደው ቮን ሮሰን በሓላፊነቱ ግን ብዙም አልቆየም፡ ፡ ልክ እንደርሱ በጦርነቱ ዋዜማ "ለአቢሲኒያ እሞትላታለሁ" ብሎ ከአሜሪካ መጥቶ የነበረው ጥቁር አሜሪካዊ ኮሎኔል ጆን ሮቢንሰን ጋር በፈጠሩት አለመግባባት እና የሥልጣን ሽኩቻ ምክንያት ንጉሡ ከሓላፊነቱ ሊያነሱት ቻሉ።

አፄ ኃይለሥላሴ ከልጅነታቸው ጀምሮ በተካኑበት የከፋፍለህ ግዛው የፖለቲካ ስልት፣ ኹለቱን የአቬሽን ባለሙያዎች እስከ መደባደብ ያደረሰ ግጭት ውስጥ ቢያስገቧቸውም፤ መልሰው ግን ለአየር ኃይሉ አዛዥነት ኮሎኔል ጉስታ ሀርድ እና ሌሎች ኹለት ሲውዲናዊያን መኮንኖችን በመሾም ውዝግቡን እልባት ሊሰጡት ችለዋል። በድርጊቱ የተበሳጨው ካርል ጉስታ ቮን ሮሰን ወደ ሀገሩ ስዊድን በመመለስ፤ በዚያ ከሚገኝ ‹‹ትራንስ ኤይር›› ከተባለ ቻርተር የአየር ትራንስፖርት ኩባኒያ ጋር በመንገደኞች አውሮፕላን አብራሪነት ሥራ ተሠማራ። በመሀል የተባበሩት መንግሥታት

**ካርል ጉስታቭ ቮን ሮሰን የተሰጠውን ሓላፊነት ወደ ተግባር ለመቀየር ወደ ሀገሩ ወደ ስዊድን በማምራት ከስዊድን አየር መንገድ ኩባኒያ እና ሲፋ ኢንተርኮንትኔንታል ሉፋትራፋክ ኤቢ ከተሰኘ ኩባኒያ ጋራ ግኑኝነት በመፍጠር፤ የኢትዮጵያ ሲቪል አቬየሽን ተቋምን፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድን፣ የኢትዮጵያ አየር ኃይልን ለማቋቋም የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ጀመረ**

ድርጅት ኹለተኛው ዋና ጸሐፊ ዳማ ሔመር ሼልድ የሚገለገሉባት አውሮፕላን አብራሪ ሆኖ በተመድ በመቀጠርም ለወራት አገልግሏል።

እስከዛሬ ድረስ ስለአሟሟታቸው ይህ ነው የሚባል ትክክለኛ መረጃ ያልተገኘለት የተመድ ዋና ጸሐፊን ዳማ ሔመር ሾልድን ያሣፈረችው አውሮፕላን በኮንጎ ሰማይ ላይ በእሳት ተያይዛ ስትከሰከስ፤ ኮንት ካርል ጉስታቭ ቮን ሮሰን በሕመም ምክንያት በመኖሪያ ቤቱ ነበር።

አንዳንዶች እስከ አሁን ይህ ሚስጥራዊ ግድያ ላይ እጁ ይኖርበት ይሆን? ሲሉ ይጠይቃሉ። በዚያን ወቅት ኮንጎ ከቀኝ ገዥዋ ቤልጂየም ነፃ ወጥታ ብዙም ሳትቆይ በተቀሰቀሰው የእርስ በርስ ጦርነት፣ አወዛጋቢው ኮንት ካርል ጉስታቭ ቮን ሮሰን ትራንስ ኤየር የተሰኘ የሲውዲን ኩባኒያ ሹማምንት ጋራ በመመሳጠር ለኮንጎ አማፂያን የተለያዩ እገዛዎችን ያደርግ ነበር።

በዚህ ብቻ ያልተገታው ጀብደኛው ካርል ጉስታቭ ቮን ሮሰን "ቅጥረኛ" የሚል ቅጽል ያሰጠውን ሕገወጥ ተግባር፣ በናይጄሪያ ከአንድ ሚሊዮን እስከ 3 ሚሊዮን ሰዎችን ሕይወት ቀጥፏል በሚባለው እና አብዛኛውን የደቡብ ምስራቅ ናይጄሪያ ግዛት በመገንጠል "የቢያፍራ ሪፐብሊክ መሰረትን" ያሉ አማጺያንን በመወገን አምስት ስዊድን ሰራሽ ኤም ኤፍ 198 የተሰኙ አውሮፕላኖችን የሚያበሩ ሌሎች ቅጥረኛ ስዊድናውያን አብራሪዎች በማስተባበር፣ የናይጄሪያ ማዕከላዊ መንግሥት ጦርን በመውጋት የስንቅ ትጥቅ ክምችቱን በማውደም ተግባር ላይ በዋና አቀነባባሪነት ተሳትፏል።

በድርጊቱ በአፍሪካውያን ሁሉ የተወገዘው ኮንት ካርል ጉስታቭ ቮን ሮሰን ወደ ስዊድን በማምራት በተለያዩ ሀገራት የአውሮፕላን ግዢ ሻጮችን በማገናኘት የድለላ ሥራ ሲሠራም ቆይቷል። በ1974 በኢትዮጵያ በደረሰው ድርቅ መላው ዓለም የተጎጂዎችን ሕይወት ለመታደግ መረባረብ ሲጀምር "ኹለተኛዋ ሀገሬ ችግር ላይ ናት" በሚል ዕርዳታ አሰባስቦ፣ አንዲት አነስተኛ አውሮፕላን በማብረር ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ለሦስት ተከታታይ ዓመታት ዕርዳታ ከማድረሱ በተጨማሪ ሌሎች በጎ ተግባራትን ሲያከናውንም ቆይቷል።

በመላ ሀገሪቱ የተከሰተውን የረሃብ አደጋ በተመለከተ ተቋቁሞ የነበረው የዕርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ኮሚሽነር የነበሩት ክቡር አቶ ሽመልስ አዱኛ እና ሌሎች የተቋሙን የሥራ ሓላፊዎችን ያሳፈረችው አውሮፕላን እያበረረ፤ ጁላይ 13 ቀን 1977 ዓ.ም ወደ ጎዴ ሲያመራ፣ በጎዴ አቅራቢያ በወቅቱ ኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ከፍቶ በነበረው የሱማሊያ ጦር በተተኮሰ የአየር መቃወሚያ አውሮፕላኗ ተመትታ ስትከሰከስ፣ ተሳፋሪዎቹ ቀለል ያለ የመቁሰል አደጋ ቢደርስባቸውም፤ አወዛጋቢው፣ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ከፍተኛ ፍቅር ያለው ሲውድናዊ ካርል ጉስታቭ ቮን ሮሰን ግን በተወለደ በ67 ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ሊለይ ችሏል።

በኢትዮጵያ መንግሥት አምስት የሜዳሊያ ኒሻን የተሸለመው ሲውድናዊ አብራሪ ኮንት ካርል ጉስታቭ ቮን ሮሰን አስከሬን በአዲስ አበባ ጉለሌ ጴጥሮስ ወ ጳውሎስ ቤተክርስቲያን መካነ መቃብር በክብር አርፎ ይገኛል። ነሐሴ 19 ቀን 2019 ከተወለደ አንድ መቶ ዓመት የልደት ቀኑ የሚታሰበውን ሲውድናዊ የኢትዮጵያ ባለውለታ በእንዲህ መልኩ ዘከርነው።

# የ25 ዓመት ጉዞ

# “ስለ ሴቶች ብለን የጀመርነው ስራ ካሰብነው በላይ አስደንጋጭ ነገር ያየንበት ነው”



## *ወ/ሮ መቅደስ ዘለለው*

### *(የተቀናጀ የቤተሰብ አገልግሎት ድርጅት መስራችና ዳይሬክተር)*

*ወ/ሮ መቅደስ ዘለለው የተወለዱት ከአዲስ አበባ በብዙ ኪሎ ሜትሮች ርቀት ላይ በሚገኝ የገጠር ቀበሌ ነው፡፡ 23 የገጠር ቀበሌ ገበሬ ማኅበሮችን አቅፎ በያዘው ደቡብ ወሎ ዞን አምባሰል ወረዳ ውስጥ ተወልደው ዛሬ አንቱ ተብለው የሚጠሩበት ታላቅ ስብዕና ላይ ለመድረስ የቻሉት እኚህ እናት ያለፉበት የህይወት መንገድ በብዙ ውጣውረዶች የተሞላ፣ እጅግ ፈታኝና እልህ አስጨራሽም ነበር፡፡*

*ምንም ዓይነት የትምህርት ዕድል ባልነበረበት በዚያ አስቸጋሪ ዘመን ‹‹በሊሆ›› በምትባል የገጠር ቀበሌ የተወለዱት ወ/ሮ መቅደስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን የተከታተሉት አምባሰል ወረዳ ውስጥ በሚገኘው ውጫሌ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ሲሆን፣ በጊዜው የነበረው የአካባቢው ማኅበረሰብ ለዘመናዊ ትምህርት የነበረው አመለካከት ደካማ በመሆኑ በተገቢው የዕድሜያቸው ዘመን ወደ ት/ቤት እንዳይገቡ ብዙ ሳንካዎችን ፈጥሮባቸው እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡*

*በጊዜው የት/ሚኒስቴር ተጠሪ ይባል የነበረው የደሴ ትምህርት ቢሮ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወደ ወረዳቸው ዘልቆ ሰፊ ዘመቻ በጀመረበት ወቅት ብዙ ልጆችን በግል ያስተምሩ የነበሩትን ወላጅ አባታቸውን የመጽሐፍ ቅዱስና የግዕዝ መምህር አድርጎ መቅጠሩ ግን የነገሮችን መልክ ቀይሮ የዛሬዋ እንግዳችንና ሌሎች የገጠሪቱ ቀበሌ ተወላጆች ሳያንገራግሩ ወደ ት/ቤት እንዲገቡ ዕድል ፈጥሮላቸዋል፡፡*

*በውጫሌ እስከ 8ኛ ክፍል ተምረው የተቀረውን ለመቀጠል ወደ ደሴ ከተማ ለማቅናት የተገደዱት ወ/ሮ መቅደስ በደሴ ወ/ሮ ስህን ት/ቤት ትምህርታቸውን ለመቀጠል ስንቅ እየተላከላቸው በዘመድ ቤት ከመቀመጥ ውጪ ምርጫ አልበራቸውም፡፡ ካረፉበት የዘመድ ቤት እስከ ት/ቤቱ ለመድረስ በየቀኑ የ45 ደቂቃ የእግር መንገድ ከመጓዝ ውጪም ህይወት አማራጭ ዕድል አልሰጠቻቸውም፡፡ 45 ደቂቃ ተጉዘው ተምረው እንደገና በ45 ደቂቃ ጉዞ ከተመለሱ በኋላ ያረፉበትን የዘመድ ቤት በሥራ ማገልገልም ግዴታቸው እንጂ ምርጫቸው አልነበረም፡፡*

*በደሴ ወ/ሮ ስህን ትምህርታቸውን ከተከታተሉ በኋላ ወደ አዲስ አበባ በማቅናት ከህይወት ጋር ግብግብ የገጠሙት ወ/ሮ መቅደስ በሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ በኩል የመጡ የጀርመን በጎ ፈቃደኞች የሚሰጡትን የመዋዕለ ህፃናት መምህራን ስልጠና ተከታትለው የጨረሱት ከሠልጣኞቹ የተሻለ ውጤት በማምጣት በአንደኝነት ነበር፡፡ ይህም ከሥልጠናው በኋላ ቶሎ ስራ ለማግኘት ስላገዛቸው ደብረ ዘይት በሚገኝ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ሥራ ለመጀመር አስችሏቸዋል፡፡ በተፈጥሮ አዛኝና ሩህሩህ ልብ የተቸራቸው እኚህ እናት ትርፍ ጊዜያቸውን የአየር ኃይል ሠራተኛ ሚስቶች ማህበር እያገዧቸው ከችግረኛ ቤተሰብ ለመጡ ህፃናት ነፃ የማስተማር አገልግሎት ይሠጡ ነበር ፡፡*

*በምስራቅ ኢትዮጵያ በነበረው ጦርነት የተፈናቀሉና ወላጆቻቸውን በጦርነት ያጡ ህፃናትን በመቀበል የህይወት ታሪካቸውን በማጥናትና ጊዜአዊ እንክብካቤ በመስጠት ከቀይ መስቀልና ከሌሎች የስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን ሠፊ ስራ በመሥራት ወደ አዲስ አበባ ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲላኩ አድርገዋል፡፡ ወ/ሮ መቅደስ በተለያዩ አጋጣሚዎች የሠጡት እጅግ ሰብኣዊነት የተሞላው ግልጋሎትም አሁን ለሚገኙበት የታላቅነት ስብዕና መንደርደሪያ ሆኗቸዋል፡፡ ዛሬ ‹‹የተቀናጀ የቤተሰብ አገልግሎት›› የተባለውን ግብረሰናይ ድርጅት አቋቁመው የወገናቸው መኩሪያና የሺህዎች የነፍስ እናት ለመሆን የታደሉትን እኚህን ታላቅ እናት የግዮኑ ጋዜጠኛ ፍቃዱ ማህተመወርቅ በእንግድነት ጋብዞ እንደሚከተለው አነጋግሯቸዋል፡፡*

**ግዮን፡- ደብረ ዘይት በነበረው መዋዕለ ህፃናት በመምህርነት ከሰሩ በኋላ ወዴት ሄዱ?**

ወ/ሮ መቅደስ፡- ወደ ሐረር ተዛውሬ ነው የሄድኩት፡፡ ሐረር ውስጥ ኑሮ መስርቼ በነበረ ጊዜ ብዙም ሳይቆይ የሶማሌ ጦርነት መጣ፡፡ ሙያዬ ከህፃናት ጋር ስለነበር ሐረር ውስጥ ተፈናቅለው የሚመጡ ቤተሰቦችን በሚቀበል ትልቅ መጠለያ ውስጥ መሥራት ቀጠልኩ፡፡

ወላጆቻቸው እንዴት እንደሞቱና ስለገጠማቸው ችግር ስለህፃናቱ ጥናት እያነጋገርኩ ወደ አዲስ አበባ እልክ ነበር፡፡ ወደ ኩባ ፣ ራሺያ እና ጀርመን የሄዱት አብዛኞቹ ልጆች እኛ ከዚያ የምንልካቸው ነበሩ፡፡

**ግዮን፡- ወደፊት ወደኋላ እያልን ብንጨዋወት ቆይታችን አሰልቺ እንዳይሆን ይረዳል፡፡ እስቲ ወደ ኋላ ልመልስዎና በገጠር በነበሩ ጊዜ ከቤተሰባችሁ የትምህርት ዕድል ያገኙት እርስዎ ብቻ ነበሩ?**

ወ/ሮ መቅደስ፡- ወላጆቻችን አራት ልጆች ነው የወለዱት፡፡ አንድ ወንድና ሦስት ሴት ነበርን፡፡ ሴቶቹ በልጅነታቸው ትዳር ያዙ እኔና ወንድሜ ግን ትምህርታችንን አጠናቀን የመንግሥት ሥራ ያዝን ፡፡ ያደግንበት አካባቢ ለትምህርት ብዙም ቦታ የሚሰጠው ስላልነበር ያን ያህል በትምህርት ሊገፉ አልቻሉም፡፡

**ግዮን፡- ትዳር መቼ መሰረቱ?**

ወ/ሮ መቅደስ፡- በ1966 ነው ያገባሁት፡፡

**ግዮን፡- ባለቤትዎ ማንናቸው?**

ወ/ሮ መቅደስ፡- ባለቤቴ እዚያ ሐረር ውስጥ የአገር ውስጥ ገቢ ሀላፊ ነበሩ፡ ፡ ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ነው ወደ አዲስ አበባ የተዛወሩት፡፡ የእኔ ሙያ ግን ቦታው ለነበረው ሁኔታ አስፈላጊ ስለነበር ወደዚህ መዘዋወር አልቻልኩም፡፡ ባለቤቴ ልጆቹን ይዞ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ከዘመድ ጋር ማሳደጉን ቀጠለ፡፡ ጦርነቱ ካለቀና አካባቢው ላይ የመልሶ ማቋቋም ስራ ከተሰራ በኋላ እኔም በ1970 መጨረሻ ወደ አዲስ አበባ ተዛወርኩ፡፡

**ግዮን፡- አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ የት መስራት ቀጠሉ?**

ወ/ሮ መቅደስ፡- ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ውስጥ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ማገልገሌን ቀጠልኩ፡፡ ከዩኒሴፍም በተገኘ ድጋፍ ለቤተሠብ እድገት ፕሮጀክት ከ3 ዓመት ተኩል በላይ ለሚሆን ጊዜ ተመድቤ በጎጃም፣ በሐረር፣ በሸዋና ሌሎች አካባቢ እየተዟዟርኩ ከገበሬ ልጆች ጋር ሠርቻለሁ፡፡ የሠራሁትም ሥራ በቤተ ህፃናት ፕሮግራም ገበሬ እናቶች ወደ እርሻ ሄደው እስኪመለሱ ህፃናቱን የማቆየትና የመንከባከብ ሥራ እንዲሠሩ እናቶችን በሞግዚትነት የማሠልጠን ሥራ ነበር፡፡

**ግዮን፡- ስንት ልጆች ወለዱ?**

ወ/ሮ መቅደስ፡- አምስት ናቸው፡፡ ►

**ግዮን፦- ልጆችዎ በትምህርትም በሥራም ብዙ የተራመዱ እንደሆኑ ሠምቻለሁ። እስቲ ስለዚህ ሁኔታ ይንገሩን?**

ወ/ሮ መቅደስ፦- ጥሩ ናቸው። ሶስቱ ማስተርሳቸውን ይዘዋል። በተለይ አንዷ ሴት ልጄ የእኔን ሙያ የተከተለች ይመስለኛል። አሁን በፕሮጀክት ማኔጅመንት እየሠራች ነው። ዓለም አቀፍ ድርጅት ውስጥ ነው የምትሰራው። ሌሎቹም በሙያቸው የየራሳቸውን ይሰራሉ። ሁለቱ ኢንጂነሮች ናቸው። አንዱ አካውንታንት ነው። አንዱ ደግሞ እኔን በማገዝ ላይ ነው። በብዙ መልኩ እየረዳኝ ነው።

**ግዮን፦- በመንግሥት መ/ቤት ምን ያህል ዓመት ሰሩ?**

ወ/ሮ መቅደስ፦- በአጠቃላይ ወደ ሀያ አመት ሰርቻለሁ በመጨረሻም በአዲስ አበባ ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ የህፃናት ቡድን አስተባባሪ ነበርኩ። በ1987 የራሴን ድርጅት ካቋቋምኩ በኂላም በተለያየ ችግር ውስጥ ያሉ ህፃናትን ድጋፍ መሥጠት ጀመረ። ወላጆቻቸውን ያጡ፣ ኤች አይ ቪ በደማቸው ያለ፣ አካል ጉዳተኞች የሆኑ የተለያየ ችግር ያለባቸው ስለነበሩ እጅግ በጣም ሰፊና አድካሚ ስራ ነበር የምሰራው።

**ግዮን፦- አሁን እየሠሩ ያሉትን የተቀናጀ የቤተሰብ አገልግሎት ድርጅት ሲከፍቱ የነበረውን አጠቃላይ ሁኔታ ቢነግሩን?**

ወ/ሮ መቅደስ፦- ይህ ድርጅት በ13 ያህል ሠብሳቢና አሳዳጊ በሌላቸው ህፃናት ነው የተጀመረው። በህፃናት ቡድን አስተባባሪነት በምሰራበት ጊዜ ከለጋሾች ጋር በመነጋገር የራሴን ሥራ ብሰራ እንደፈለግኩት መጠን የራሴን ድርሻ ለመወጣት እንደምችል ስላመንኩ በ13ቱ ህፃናት ሥራውን ጀመርኩት። እንዳልኩህ ለጋሾችን ለማግኘት ብዙ ስላልተቸገርኩ የልጆቹ ቁጥር ወዲያው ነው የጨመረው። አንድ ሺጎ ስድስት መቶ የደረሱት ብዙም ሳይቆይ ነው።

**ግዮን፦- የተቀናጀ የቤተሰብ አገልግሎት ድርጅት ዋና ተግባር ምንድነው?**

ወ/ሮ መቅደስ፦- ህፃናቱ ከቤተሰቦቻቸው ወይም ከአሳዳጊዎቻቸው ጋር ሆነው አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ እንዲያገኙ ማድረግና ወላጆቻቸው የሙያ ሥልጠና አግኝተው ሰርተው ማደር እንዲችሉ ማስቻል ዋነኛ ተግባራችን ነው።የህፃናቱ ትልልቅ ወንድሞችና እህቶችም በመንጃ ፈቃድ ሥልጠና እና በሆቴል ሙያ እንዲሰለጥኑ እንረዳለን። በፀጉር ሥልጠና እና በሌሎችም የሙያ መስኮች ሰልጥነው ሥራ እንዲይዙ እናደርጋለን። በተለይ በምግብ ዝግጅት፣ ሆቴል ሙያና በህፃናት እንክብካቤ ላይ የከፈትነው ትልቅ ማሠልጠኛ ድርጅቱ ስለነበረው፣ በ10 ዓመት ውስጥ የኪስ ገንዘብ እየሰጠን ያስተማርናቸው ቁጥራቸው እጅግ ብዙ ነው። በጣም ጥሩ ማሠልጠኛም ነበር። ብዙዎቹ ጥሩ ደረጃ ደርሰዋል ፤ ውጭ ሀገር የሄዱም አሉ። ከአሜሪካ ጀምሮ ወደ ብዙ ሀገራት ሄደው ያገኘኂቸው የእኛ ልጆች አሉ። እስከ ትልቅ ኢንተርናሽናል ሆቴል ዋና ሼፍነት የደረሱም አሉ።

**ግዮን፦- በአሁኑ ወቅት ምን ያህል ህፃናት ናቸው ድጋፍ የሚረግላቸው?**

ወ/ሮ መቅደስ፦- በአዲስ አበባና በክፍለ ሃገር ያሉት ከስምንት መቶ በላይ ናቸው።

**ግዮን፦- ህፃናትን በማዕከል አድርጎ ማሳደግ ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝንም ያታመናል። እስቲ በሁለቱ ሁኔታዎች መካከል ያለውን ልዩነት ይንገሩን?**

ወ/ሮ መቅደስ፦- ህፃናትን በማሳደጊያ ማዕ ከል እንዲያድጉ ማድረግ በአሁኑ ጊዜ ብዙም አይመከርም። የመጨረሻ አማራጭ እንጂ ተመራጭ ዘዴ አይደለም። ዓለም ላይ ያለው አሰራርና እኛም የምንከተለው ህፃናቱ ከወላጆቻቸው ወይም ከአሳዳጊ ዘመዶ ቻቸው ጋር እንዲያድጉ ማድረግ ነው። በቤ ተሰብ ውስጥ የሚያድግ እና ያለቤተሰብ የሚያድግ ህፃን ብዙ ልዩነት አላቸው። ቀደም ሲል በነበረው ህፃናት አምባ ወይም “እኋለምውታን” በሚባለው ማዕከል እሰራ ስለነበር ልዩነቱንና ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በደንብ አውቀዋለሁ። በጊዜው ቤተሰቦቻቸው በጦርነት የሞቱባቸውን ልጆች በአንድ አሰባስቦ ለመርዳትና ለማሳደግ የተሰራው ስራ የመጨረሻ አማራጭ ቢሆንም በተቻለ መጠን ራሳቸውን እንዲያወጡ ተደርጓል። በአሁን ጊዜ ግን ይህን ማድረግ በጣም አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ በተቻለ አቅም ቤተሰብን ማጠናከር ወይም ልጆቹ ከማህበረሰብ ጋር ተቀላቅለው እንዲያድጉ ማመቻቸት ነው የተሻለ ሆኖ የተገኘው።

እናትና አባት ባይኖሩ እንኳን አጎትና አክስት ወይም ታላቅ እህትና ወንድም ሊኖሩ ይችላሉ። ስለዚህ ህፃናት በማሳደጊያ ማዕከል ከሚያድጉ ይልቅ የሩቅም ቢሆን ከዘመድ ጋር ቢያድጉ ነው የሚሻለው። በሥነልቦና ረገድ በጣም ብዙ ልዩነት አለው። ነገር ግን የመጨረሻ አማራጭ ከሆነ ምንም ማድረግ አይቻልም። ሜዳ ላይ ከሚወድቁ በሚል እንጂ በምንም መመዘኛ ተመራጭ አይደለም። የሚያሳድረው ሥነልቦናዊ ጫና በጣም ከባድ ነው።

**ግዮን፦- ስለህፃናቱ መደፈር ካነሱ ላይቀር እስቲ ይህን ችግርና በዚህ ላይ የእናንተ ተሳትፎ ምን እንደሚመስል ያጫውቱን?**

ወ/ሮ መቅደስ፦- ችግሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋና ወደ አስቸጋሪ ደረጃ እየደረሰ ነው። በዚህ ዙሪያ ከ15 ዓመት በፊት በራሳችን ተነሳሽነት ያደረግነው ጥናት አስደንጋጭ ውጤት ያየንበት ነበር። በችግሩ ላይ ለመስራት ፕሮግራም ቀርፀን ስንጀምር ከሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ጋር ትብብር ፈጥረን ነበር።

> ...በቤተሰብ ውስጥ የሚያድግ እና ያለቤተሰብ የሚያድግ ህፃን ብዙ ልዩነት አላቸው፡፡ ቀደም ሲል በነበረው ህፃናት አምባ ወይም “እጓለምውታን” በሚባለው ማዕከል እሰራ ስለነበር ልዩነቱንና ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በደንብ አውቀዋለሁ...

ስለሴቶቹ ህፃናት ብለን የጀመርነው ሥራ ግን ካሰብነው በላይ አስደንጋጭ ነገር ያየንበት ሆነ።

ይኸውም ለሴቶቹ ብለን ልንጀምር ያሰብነው ወንዶች ህጻናትንም ያካተተ ሆነ። ህፃናት ወንዶች ተደፍረው ለፖሊስ ተደጋጋሚ ሪፖርት እየደረሰ መሆኑን ስንረዳ ፕሮግራማችንን ለሁለቱም ጾታዎች ለማድረግ ተገደድን። እነዚህ የተደፈሩ ህፃናት የሥነ ልቦና እና ሌሎች ህክምናዎችን እያገኙ የሚቆዩባቸው ማዕከላት አቋቁመን መስራታችንን ቀጠልን። አሁን አንድ የሴት አንድ የወንድ ማዕከል ከፍተን በዚህ ላይ እየሰራን ነው። የፍርድ ሂደታቸው እስኪያልቅና ወደ ጥሩ መንፈስና አቋም እስኪመለሱ በእነዚህ ማዕከላት ቆይተው እንዲያገግሙ በድርጅቱ ባለሙያዎች አስፈላጊው ክትትልና ድጋፍ ይሠጣል።

በጎረቤት የተደፈረ ልጅ እዚያው ቤት እየኖረ ጉዳዩ በፍ/ቤት ቢታይ ጉዳቱ ከባድ ነው። ስለዚህ ይህን መሰል ሁኔታዎች እንዳይፈጠሩ ህፃናቱ እኛ ጋር እንዲቆዩ ይደረጋል። ትምህርቱን እየተማረ በሥነ ልቦና ባለሙያ እገዛ እየተደረገለት ይቆዩና የፍርድ ሂደቱ ሲያልቅና ነገሮች ሲረጋጉ ለቤተሰቦቻቸው የምክር አገልግሎት ሰጥተን ቀጣይ እገዛዎችን በማድረግ ወደ ቤተሰብ እንዲመለሱ እናደርጋለን። በዚህ መንገድ ትምህርታቸውን ቀጥለው እስከ ዩኒቨርሲቲ የደረሱ ብዙ ልጆች አሉ።

**ግዮን፦- የመደፈር ጥቃት የተፈፀመባቸው ዝቅተኛ የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ህፃናት እንዳሉ ይታወቃል። እንደው ግን እስከ ስንት ዓመት የሚደርስ ዝቅተኛ ዕድሜ ገጥሟችኋል?**

ወ/ሮ መቅደስ፦- ብዙዎቹ ምንም ነፍስ የማያውቁ ህፃናት ናቸው። ከሁለት ዓመት ተኩል ጀምሮ ያሉ ህፃናት ያጋጥማሉ።

**ግዮን፦- በወላጅ ወይም በአሳዳጊያቸው አካላዊ ጥቃት የደረሰባቸው ህፃናትም እንደሚመጡ ሠምቻለሁ?**

ወ/ሮ መቅደስ፦- አዎ! ብዙ አሉ። ለምሳሌ አንዲት የ10 ዓመት ህፃን እናስተምራታለን ብለው ባመጧት አሳዳጊ ዘመዶቿ “አጥፍተሻል” በሚል በተፈፀመባት ቅጣት አንድ እግሯ ተቆርጦ እኛ ጋር መጥታ ስትረዳ ቆይታለች። አርቴፊሻል እግርና ጫማ ተሠርቶላት የፍርድ ሂደቷ ሲያልቅ ከወላጅ እናቷ ጋር ወደመጣችበት እንድትመለስ አድርገናል። የፈላ ውሃ የተደፋባቸው፣ ሌላም ጥቃት የደረሰባቸው አሉ። ማዕከላችን አስገድዶ መድፈር ላይ ብቻ ሳይሆን አካላዊ ጥቃት ላይም ትረኩት ሰጥቶ ድጋፍ ያደርጋል።

**ግዮን፦- እናንተ ጋር የሚረዱ ህፃናት ከውጭ ሀገር ድጋፍ ሠጪዎቻቸው ጋር በተናጠል የሚገናኙበትና እርዳታ የሚያገኙበት ዕድል አለ?**

ወ/ሮ መቅደስ፦- ብዙዎቹ ማለት በሚቻል መጠን ህፃናቱ ከድጋፍ ሠጪዎቻቸው ጋር በተናጠል በደብዳቤ ሀሳብ ይለዋወጣሉ፣ አንዳድ ቤተሰቦችም መተው ይጎበኟዋችዋል። ፈረንጆቹ ብዙ ጊዜ የሚረዱት አንድ ለአንድ ስለሆነ በርከት ያለ ገንዘብ የሚልኩላቸው አሉ። በዚህ ገንዘብ የራሳቸውን ሥራ ሰርተው የተሻለ ህይወት የመኖርን ዕድል ያገኙም አሉ፤ ላፕቶፕ የሚገዛላቸው አልጠፉም። የኮንዶሚኒየም መኖሪያ ቤት ዕጣ ደርሷቸው የተከፈለላቸውም አሉ።

**ግዮን፦- በት/ቤቶች ምንድነው የምትሰሩት?**

ወ/ሮ መቅደስ፦- ትምህርት ቤቶች ላይ




ወ/ሮ መቅደስ ዘለለው

ብዙ ስራ ሠርተናል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በተለያዩ ክ/ከተሞች ውስጥ ከ1-4ኛ ክፍል የተለያዩ አማራጭ ት/ቤቶች ግንባታና እድሳት ሰርተናል፡፡ በተለያየ ወረዳዎች ሶስት የመዋዕለ ህፃናት ሠርተናል፡፡ እንዲሁም በአፋር ክልልና አማራ ክልል መዋዕለ ህጻናትና አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ገንብተናል፡፡ ት/ቤቶች በተለይም የችግረኛ ልጆች የሚማሩባቸው የመንግሥት ት/ቤቶች የኮምፒውተር፣ ማባዣ ማሽን፣ ፍሪጅና የመሳሰሉትን ዕገዛ እንዲያገኙ የማድረግ ሥራ ሰርተናል፡፡ ሚኒ ሚዲያዎች ተማሪውን በተገቢው እንዲያገለግሉ የሚያስችል እንደ ቴፕ እና ሌሎች መሠል መገልገያዎች የተሟሉላቸው እንዲሆኑ አድርገናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በየካ፣ ጉለሌ፣ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ሰባት ት/ቤቶችን ሰርተን አስረክበናል፡፡ ከግንባታና የመገልገያ ዕቃዎች ማሟላት በተጨማሪ ለተወሰነ ጊዜ የመምህራኑን ደሞዝ የመሸፈን ሥራም ሰርተናል፡፡

**ግዮን፡- በማኅበረሰብ ውስጥስ?**

ወ/ሮ መቅደስ፡- የመጠጥ ውሃ እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች ደግሞ ምንጮችን የማጎልበትና የየአካባቢውን ሕብረተሰብ የን ፁህ ውሃ ተጠቃሚ የማድረግ ሥራዎች ሰርተናል፡፡ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ችግረኛ ቤተሰቦችም የብድር አገልግሎት በማመቻቸት የሙያ ሥልጠና ወስደው ወደሥራ እንዲገቡ የማድረግ ሥራም ሰርተናል፡፡ ሕገወጥ ስደትን ለመከላከል የምንሰራው ሰፊ ሥራም አለ፡፡ ሄደው የመጡትን ተቀብሎ ወደራሳቸው እንዲመለሱና እዚሁ መስራት እንዲችሉ ከማድረግ ጀምሮ ዜጎች እንዳይሄዱ የማድረግ ሰፊ ሥራ እየሰራን እንገኛለን፡፡

ከባቢ አየር (ኢንቫይሮመንት) ላይ የተለያዩ ሥራዎች ሰርተናል፡፡ ለምሳሌ በየካና ጉለሌ ክ/ከተሞች በየዓመቱ 40 ሺህ ችግኞች ተተክለው እስከ 2006 ዓ.ም ድረስ ወደ ሁለት መቶ ሺህ ችግኞች እንዲተከል አድርገናል፡፡

ኢንጌጅ ዘቦይስ በሚል ፕሮግራም ደግሞ ወንዶችን እያሰለጠንን ሴቶችን እንዲያግዙ የማድረግ ሥራ ሰርተናል፡፡ ወንዶች የሴቶች ጥቃት እንዲያማቸውና የእሷ ጥቃት የእኔም ነው የሚል ስሜት እንዲያድርባቸው የሚያደርግ ሥራ ሰርተናል፡፡የሙዚቃ መሣሪያ ተገዝቶላቸው ወደ ሥራና ራስን ወደመቻል የተሻገሩም አሉ፡፡

**ግዮን፡- በቅርቡ በእናንተ ሲረዱ የቆዩ ወጣቶች ከዩኒቨርሲቲ መመረቃቸውን ምክንያት በማድረግ አንድ ደማቅ መርሃ ግብር አከና ውናችኋል፡፡ እስቲ ስለዚህ ሁኔታ ጠቅለል ያለ ሃሳብ ይስጡን?**

ወ/ሮ መቅደስ፡- ከሀገር አቀፍ ፕሮግራማችን መካከል በደቡብ ወሎ ዞን አምባሰል ወረዳ የሚገኘው ተጠቃሽ ነው፡፡ የአካባቢው መልክዐ ምድር ገደላማ በመሆኑ የአካባቢው ሕብረተሰብ በግብርና ሥራ ለመተዳደር በብዙ ይቸገራል፡፡ ገበሬው ለቤተሰቡ በማይበቃ የግብርና ምርት የሚቸገር በመሆኑ ልጆቹን ወደ ከተማ ልኮ ስንቅ እየሰነቀ ማስተማር ይከብደዋል፡፡ ብዙዎቹ የአካባቢው ተወላጆች እንደምንም ብለው እስከ 8ኛ ክፍል ቢማሩ እንኳ ዘጠነኛን ለመቀጠል ይቸገራሉ፡፡ ከ8ኛ ክፍል በላይ ለመማር የግድ ወደ ውጫሌ እና ሌሎች ትልልቅ ከተሞች ሄደው መኖር ይጠበቅባቸዋል፤ ይህ ደግሞ ብዙ ችግር ስላለው ትምህርታቸውን ከመቀጠል ይልቅ ወደ አረብ ሀገራት መሄድን አሊያም ሰው ቤት ተቀጥሮ መሥራትን ነው ምርጫቸው የሚያደርጉት፡፡ ትምህርት ጨርሰው ዩኒቨርሲቲ የመግባት ፍላጎት ቢኖራቸውም ይህን ለማድረግ አቅም ግን አይኖራቸውም፡፡ ይህንን በደንብ ካጠናሁ በኋላ ከአካባቢው አስተዳደርና ከሕብረተሰቡ ጋር በመነጋገር ችግሩን ለመቅረፍ የምንችልበት ፕሮግራም ቀርፀን ወደስራ ገባን፡፡

ጣሊያን ሀገር ከሚገኝ ቺፋ የተባለ ግብረ ሠናይ ድርጅት ጋር ተነጋግረን በአካባቢው የልጃገረዶች ማዕከል ተመሠረተ፡፡በዚህ ማዕከል ውስጥ ለመጀመሪያ 30 ተማሪዎችን ከሩቅ ቀበሌ ችግረኛ ቤተሰብ የመጡትን መርጠን በአዳሪ መልክ እንዲማሩ አደረግን፡፡ሁለት የምግብ ባለሙያዎች፣ አንድ የማኅበራዊ ግልጋሎት ባለሙያ፣ አንድ ሞግዚትና አንድ የፕሮግራም መሪ ቀጥረን የተሟላ ሁኔታ እንዲኖር በማድረግ ፕሮግራሙን ቀጠልን፡፡ የትርፍ ሰዓት አስጠኚ መምህራንን በመቅጠርም በትምህርታቸው እንዲተጉ የቻልነው ሁሉ አደረግን፡፡ በዚህ መልኩ ሁሉም የተሻለ ውጤት በማግኘት ዩኒቨርሲቲ ለመግባት ቻሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ 16ቱ ዘንድሮ በተሻለ ውጤት ከዩኒቨርሲቲ የተመረቁ ሲሆን 8ቱ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነው የተመረቁት፡፡

በፕሮግራማችን የታቀፉት 30ዎቹም ዩኒቨርሲቲ ገብተዋል፡፡ በተጨማሪም በሚቀጥለው ዓመት 27 ሴት ተማሪዎች ማትሪክ የሚወስዱ አሉ፡፡ እንደነገርኩህ 16ቱ ዘንድሮ ሲመረቁ፣ የተቀሩት 14ቱ ደግሞ በመጪው ዓመት ይመረቃሉ፡፡ ወሎ ዩኒቨርሲቲ የነበረች አንዷ ልጃችንም የተሻለ ውጤት አግኝታ እዚያው ቀርታለች፡፡ የሚገርምህ አብዛኞቹ ተመራቂዎቻችን ከ3.4(ሦስት ነጥብ አራት) እና 3.96(ሦስት ነጥብ ዘጠኝ ስድስት) ድረስ ነው ያስመዘገቡት፡፡ እንግዲህ ይህንን ሁኔታ መነሻ በማድረግ ነው ካደጉበት ማኅበረሰብ ጋር በመሆን በዘመዶቻቸው ፊት ምርቃታቸውን ለማክበር በቅርቡ የሄድነው፡፡ ቤተሰብ ደግሶ ደስታውን ለማጣጣም አቅም ስለሌለው ከወረዳው መስተዳደርና ከድጋፍ ሰጪዎቻችን ጋር በመሆን ሐምሌ 28 ቀን 2011 ዓ.ም ደስታውን በጋራ አከበርን፡፡ የወሎ ዩኒቨርሲቲ ም/ፕሬዚዳንት፣ የአካባቢው አስተዳደርና የደቡብ ወሎ ዞን የተለያዩ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ ሁሉም ተገኝተው ትልቅ የምረቃ በዓል ነበር ያዘጋጀነው፡፡ ወላጆችና የአካባቢው ሕብረተሰብ እጅግ የተደሰቱበት በጣም የሚያምር ፕሮግራም ነበር፡፡ ራዕያችን በመሳካቱ እኔም ደስታዬን መቆጣጠር አቅቶኝ ነበር፡፡

**ግዮን፡- በጣም ደስ ይላል! እንኳን ደስ ያለዎ!**

ወ/ሮ መቅደስ፡- እንኳን አብሮ ደስ አለን! ደስታው የሁላችንም ነው!

ግዮን፡- ከዚህም በተጨማሪ ሌሎች የእንስሳት እርባታ ድጋፎችን፣ ብዙ ሴቶች ተጠቃሚ የሆኑበት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (IT) ሥልጠናዎችና እጅግ ሰፋፊ የበጎ አድራጎት ተግባራት እንዳከናወናችሁና ባለፉት 25 ዓመታት ታላላቅ ስኬቶችን እንዳስመዘገባችሁ አውቃለሁ፡፡ ሁሉንም በዝርዝር እናውራው ብንል ጊዜው ላይበቃን ስለሚችል እንጂ ብዙ ያልተነሱ ጉዳዮች እንዳሉ እገነዘባለሁ፡፡ ይሁንና ሁሉንም መዘርዘር ባንችልም በስራዎ ያገኟቸውን ምስጋና እና ሽልማቶች ሳናነሳ ማለፍ ግን አንችልም፡፡ እስቲ ለዓመታት በዘለቀ በዚህ አድካሚ የስኬት ጉዞዎ ስላገኟቸው የእውቅና እና የምስጋና ሽልማቶች ይንገሩን?

ወ/ሮ መቅደስ፡- በጣም ብዙ ስለሆነ ሁሉንም መዘርዘር አዳጋች ነው፡፡ በክልሎች በተለይ በአማራ፣ በአፋርና ሌሎች ክልሎች በየዓመቱ የእውቅና ሰርተፍኬቶች ተሰጥተውናል፡፡ የበጎ ሰው ሽልማት ዕጩ ከመሆን ጀምሮ ከበርካታ ዓለም አቀፍ ተቋማት የእውቅና እና የምስጋና ሽልማቶች ተበርክተውልናል፡፡ አሜሪካ የሚገ ኘው የኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብ ሽልማት ድርጅት (SEED) የሰጠንን ታላቅ ሽልማት ጨምሮ ያገኘናቸው ሽልማቶች እጅግ ብዙ ናቸው፡፡

**ግዮን፡- በመጨረሻ ምን መናገር ይፈልጋሉ?**

ወ/ሮ መቅደስ፡- ይሄ ሁሉ ሥራ ሲሰራ ነገሮች አልጋ በአልጋ አልነበሩም፡፡ በመጀመሪያ ራዕዬን ያሳካልኝን ልዑል እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡ ይህን ሥራ ስንሰራ ከመጀመሪያው ጀምሮ አብረውኝ የነበሩ የድርጅታችን ሠራተኞችን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ ሌላ ጋር ቢሄዱ የተሻለ ነገር ማግኘት እየቻሉ ከእኔ ጋር አብረው የቆዩ በመሆኑ ደጋግሜ ከልቤ አመሰግናቸዋለሁ፡፡

‹‹የተቀናጀ የቤተሰብ አገልግሎት ድርጅት›› የሥራ አመራር ቦርድና ጠቅላላ ጉባዔ ከእኔ ጋር በብዙ የደከሙ በመሆኑ በጣም አመሰግናቸዋለሁ፡፡ ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርን፣ በገንዘብ የሚያግዙን ለጋሽ ድርጅቶቻችንን(ዶነሮቻችንን) እንዲሁም ከሀሳብ ጀምሮ በልዩ ልዩ ሁኔታ የሚያግዙን ግለሰቦችን፣ የመንግሥት ሥራ ኃላፊዎችና ተቋማትን በሙሉ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

**ግዮን፡- ከምንም ተነስተው አሁን ላሉበት ስብዕና እስኪደርሱ በፅናት መጓዝዎን በእጅጉ እያደነቅን፤ ስላደረጉት ነገር ሁሉ የመጽሔት ዝግጅት ክፍላችንም የላቀ ምስጋናውን ለማቅረብ ይወዳል፡፡**

ወ/ሮ መቅደስ፡- ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

# አዲሱ ደምሴ

## ኢትዮጵያዊው “የአሜሪካ የምርጫ ዘመቻ መሀንዲስ”

ብሩክ መኮንን

ስለልጅነቱና ስለዕድገቱ ብዙም የማያወራው፣ ከካናዳ ወደ አሜሪካ ከነቤተሰቡ በመግባት ኑሮውን በታላቂ አገር ያደረገው ትውልደ ኢትዮጵያዊ አዲስ ደምሴ፤ በመጪው ዓመት በምድረ አሜሪካ በሚካሄደው ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ፤ የሴናተር ብሪ ቡካር “የምርጫ አስተባባሪ” ሆኖ ተመርጧል፡፡

በአሜሪካ ምርጫ እ.ኤ.አ በ2004 እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ተኮሂዶ በነበረው ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ በዕጩነት ቀርበው የነበሩት ጆን ኬሪካ ጋር ባካሄዱት የምርጫ ዘመቻ ላይ በአስተባባሪነት በመሳተፍ ሥራውን የጀመረውና አንዳንዶች “የምርጫ ዘመቻ መሐንዲሱ” የሚል ስያሜ የሰጡት አዲሱ ደምሴ ማን ነው?

አዲሱ ደምሴ በታዋቂው የል ዩንቨርስቲ ሕግ ትምህርት ቤት በመግባት ትምህርቱን ተከታትሎ ሊመረቅ ችሏል፡፡ በካሊፎርኒያ ግዛት የሚገኙ ጠበቆች የሕግ አማካሪዎች ማኅበር አባል ከሆነ ጓደኛው ጋር “ግራስ ሩት አድቮኮሲ” የተባለ ተቋም መስርቶ ምክትል ፕሬዚዳንት በመሆንም አገልግሏል፡፡

በ28 ዓመቱ ከሚኖርበት አትላንታ ጆርጂያ ባራክ ሁሴን ኦባማ እና ሂላሪ ክሊንተን ለፕሬዝዳንትነት ያካሄዷቸው የምርጫ ዘመቻዎች ላይ የዘመቻዎቹ አስተባባሪ በመሆን በኔቫዳ፣ በአይዋ፣ በኬንታኪ፣ በኢንዲያ፣ በኦሀዮ፣ በዋሽንግተን እና በአካባቢው ግዛቶች በተካሄዱ የምርጫ ቅስቀሳዎች ውጤታማ ሥራዎችን ሠርቷል፡፡

አዲሱ ደምሴ ለመጀመሪያ ጊዜ በምርጫ ዘመቻ አስተባባሪነት መሥራት የጀመረው፤ በወቅቱ የዲሞክራቲክ ናሽናል ኮሚቴ ሊቀመንበር ከነበሩት ጆን ኬሪ ረዳትና ልዩ አማካሪ ከነበሩት፣ ታዋቂዋ ፖለቲከኛ የቴሪ ማክሊይፍ ረዳት በመሆን ነበር፡፡

በዚህ የጆን ኬሪ የምርጫ አስተባባሪነት ወቅት፣ ጆን ኬሪ በተፎካካሪያቸው ሄላሪ ክሊንተን እጅግ ጠባብ በሆነ ድምጽ ተሸንፈው ከውድድር ውጭ ሆኑ፡፡

አዲሱ ደምሴ በምርጫ ዘመቻ የማስተባበር ሥራው ወቅት ያየውን የተለያዩ ክፍተቶች በመገንዘብ በዋሽንግተን በሚገኝ ሕዝባዊ ጉዳዮች(Public Affairs) ላይ የሚሰራ ተቋም ውስጥ ተቀጥሮ መሥራት ቢጀምርም፤ በሀገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ አብዛኛው አፍሪካ አሜሪካውያን፣ ላቲኖች እና ሜክሲኮያውያን ድምፃቸው ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ ፣ ፖለቲካዊ መብታቸውን የሚያረጋግጡበት ዕድልን ተጠቃሚ ለማድረግ በሳንፍራንሲስኮ ውስጥ መሰረቱን ያደረገ፤ 50+1 የተባለ እና



አቶ አዲሱ ደምሴ

የፖለቲካ ፕሮግራም የሚያማክር የምርጫ ስትራቴጂ የሚነድፍ ተቋም መሠረተ፡፡ በዚህ ግብረ ኃይል ውስጥ በፖለቲካ ጉዳዮች ከፍተኛ ተሞክሮ ያላቸውና የፖለቲካ ዕውቀታቸውም የተመሰከረላቸው ባለሙያዎች ይገኙበት ነበር፡፡

በአሜሪካ የተለያዩ ግዛቶች በበርካታ ዘርፎች ለሚካሄዱ እና የሕብረተሰብ ተሳትፎን የሚጠይቁ እንቅስቃሴዎችን የሚያካሄዱ ኮርፖሬቶች፣ መንግስሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በእውቀት የዳበረ፣ በጥናት ላይ የተመሰረተ አሰራርን በማወቅ ረገድ አዲሱ ደምሴ እና ባልደረቦቹ በበርካታ ሥራዎቻቸው ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ መርጠዋቸዋል፡፡

በ2012 (እ.ኤ.አ) ያቋቋመውን ፋፋቲ ፕላስ ዋን ስትራቴጂስ ኤ ናሽናል ፖለቲካል ኮንሰልቲንግ ፎረም በዳይሬክተርነት እየመራ የሚገኘው አዲሱ ደምሴ፣ በአሁኑ ወቅት ነዋሪነቱን ያደረገው በኦክላንድ ካሊፎርኒያ ነው፡፡ በ2004 (እ.ኤ.አ) እንዲሁም በ2008 እና በ2016 በተካሄዱ የአሜሪካ ፕሬዝዳንታዊ የምርጫ ዘመቻዎች ፕሮግራሞች ላይ በአስተባባሪነት የተሳተፈው አዲሱ ደምሴ፤ በ2009 ፕሬዜዳንት ባራክ ኦባማ ለመጀመሪያ ጊዜ በፕሬዝዳንትነት ተመርጠው ሥልጣን ከያዙ በኋላ፤ ታዋቂው የዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ፣ “በፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ ፕሬዚዳንት ምርጫ ዘመቻ ወቅት ያንፀባረቁ አስር ምርጥ ወጣት ጥቁር አፍሪካ አሜሪካውያን የፖለቲካ አማካሪዎች” በማለት ስማቸውን ከዘረዘራቸው ግለሰቦች ውስጥ አንዱ አዲሱ ደምሴን ነበር፡፡

ፕሬዚዳንት ባራክ ሁሴን ኦባማ “ኦርጋናይዝንግ ፎር አሜሪካ” የተሰኘ ድርጅት ውስጥ፣ የመጀመሪያው የናሽናል ፖለቲካል ዳይሬክተር አድርገው አዲሱ ደምሴን በከፍተኛ ሓላፊነት ሾመውት ነበር፡፡

የኦርጋናይዚንግ ፎር አፍሪካ ናሽናል ፖለቲካል ዳይሬክተር ሆኖ በሰራባቸው ዓመታትም አዲሱ ደምሴ የዝቅተኛ የሕብረተሰብ ክፍል አባላት በአሜሪካ ኢኮኖሚ ቀውስ ሳቢያ ተጎጂ በሚያደርጋቸው የኢኮኖሚ እድገት ሳቢያ የሚከሰቱ ተግዳሮቶች ሰለባ የሚሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የሚታደግ መርሃ ግብር በመንደፍና በኢኮኖሚው ማገገምና መልሶ መዋዕለ ነዋይን የማፍሰስ እንቅስቃሴ ተጠቃሚ የሚያደርጉ አቅጣጫዎችን በመንደፍ በተግባር ላይ እንዲውሉ ቁልፍ ሚና መጫወቱ ይነገርለታል፡፡

ከነዚህ ተግባሮቹ ውስጥ በመላው አሜሪካ “የፌደራል ስቱደንት ሎን” የተባለ ለተማሪዎች የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርግ አሠራር በመዘርጋት፤ በዚህ የረዥምም ጊዜ ተከፍሎ ሚጠናቀቅ ብድር ተማሪዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል አሠራር እውን አድርጓል፡፡

“የምርጫ ዘመቻ መሐንዲስ” የሚል መጠሪያ ያገኘው፤ ትውልደ ኢትዮጵያዊው አዲሱ ደምሴ በሳንፍራንሲስኮ ከተማ ከንቲባነት የተወዳደሩት የዴቪድ ቱል የምረጡኝ ዘመቻን በበላይነት በመምራትም ለድል አብቅቷዋል፡፡

በዲሞክራቲክ ፓርቲ በመወከል ለካሊፎርኒያ ገዢነት ተወዳድረው ያሸነፉት የጋቪን አውሶም የምርጫ ዘመቻ ማናጀርም ነበር፡፡ አዲሱ ደምሴ በ2016 ለፕሬዝዳንትነት ተወዳደረው የነበሩት ሂላሪ ክሊንተን የምርጫ ዘመቻ ማናጀር በመሆንም ከማገልገሉም በላይ በምርጫ ዘመቻ ወቅት ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ፣ ለሂላሪ ክሊንተን ድምፁን እንዲሰጥ በማነቃቃት፣ የመብቱ ተጠቃሚ እንዲሆን የተፈጠረው መርሃ ግብር አንቀሳቃሽ ዳይሬክተርም ነበር፡፡

“የሁሉንም መራጭ ድምፅ ለማግኘት የሚያስችሉ መንገዶችን በጠቅላላ እጠቀማለሁ” የሚል አቋም ያለው አዲሱ ደምሴ፤ በ2013 ለሴናተርነት የዴሞክራቲክ ፓርቲን በመወከል በኒውጀርሲ የተወዳደሩት ኮሪ ቡከር በሴኔቱ አሸናፊ ሆነው መቀመጫ እንዲያገኙ፣ በእሱ የተመራው የምርጫ ቅስቀሳ ሚናው ጉልህ ነበር፡፡

በሴናተርነት መቀመጫ ያገኙት ሴናተር ኮሪ ቡከር፤ በቀጣይ ዓመት እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2020 ለአሜሪካ ፕሬዝዳንትነት ለመወዳደር ለሚያካሄዱት የምርጫ ዘመቻ፣ አዲሱ ደምሴን የምርጫ ዘመቻው አስተባባሪዎች ማናጀር አድርገው ሾመውታል፡፡

ትውልደ ኢትዮጵያዊው አዲሱ ደምሴ፤ ለኹለተኛ የሥልጣን ዘመን፣ በድጋሚ የአሜሪካ ሕዝብ ይመርጠኛል ብለው በእርግጠኛት እየተናገሩ ያሉት አወዛጋቢው ዶናልድ ትራምፕን፤ ከዋይት ሐውስ ለማባረር የሚቻለውን ሁሉ ለማድረግ ቃል የገቡት ሴነተር ኮሪ ቡከርን የምርጫ ዘመቻ ለመንደፍ፤ ላለፉት አራት ዓመታት የሴናተር ኮሀ ቡከር ዋና አማካሪዎች በመሆን ካገለገሉት ከማት ፕላከር እና ከመዲያ ቤትለር ጋር በመቀናጀት ከወዲሁ ትኩረት ሠጥቶ እየሠራ ስለመሆኑ ከአሜሪካ የሚወጡ ዘገባዎች ይጠቁማሉ፡፡

ትርፍ ጊዜውን ሶምሶማ ሩጫ መሮጥን የሚያዘወትረው እና የአሜሪካ ፉትቦል ጨዋታ ተመልካች እንደሆነ የሚናገረው አዲሱ፤ “አሜሪካውያን የሚያስፈልጋቸው መሪ ምን ዓይነት እንደሆነ ያውቃሉ፤ ያንን ሰው ፕሬዚደንታቸው አድርገው እንዲመርጡት የማድረጉን የማነቃቃት ሥራ እኛ እንሠራለን” ብሏል፡፡ ይህ እምነቱና አቋሙ እንደሌሎቹ ሁሉ በዋሽንግተንም ይሳካለት ይሆን? ጊዜ ምላሽን ይሰጣል፡፡



(ኤርሚያስ አመልጋ ከቂሊንጦ እስር ቤት)

# “አዲሱ ኢህአዴግ እኔን ማጥቃትና ሥራዎቼን ማሰናከልን ተልዕኮው አድርጓል”

የማይሰበረው ኤርሚያስ” በሚል ርዕስ ሠሞኑን በገበያ ላይ የዋለው የመጽሐፍ ምረቃ ላይ መገኘት ያልቻሉት ታዋቂው ባለሀብት እና የቢዝነስ ሰው አቶ ኤርሚያስ አመልጋ፤ ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ያላቸውን ፍቅር እና አክብሮት፣ መጸሐፋቸው የተዘጋጀበትን ሂደት እንዲሁም አጠቃላይ የዕስር ሕይወታቸውን በተመለከተ ከሚገኙበት ቂሊንጦ በወኪላቸው አቶ ሄኖክ ተድላ አማካይነት ለግዮን መፅሔት ይድረስልኝ ባሉት መሠረት በዚህ መልክ ጽፈው አድርሰውናል፡፡

## አልሆነም!

ይህቺን ምሽት ቂሊንጦ ማረሚያ ቤት ውስጥ እንጂ በመካከላችሁ እገኝ ዘንድ አልቻልኩም፡፡ ይህን መልዕክትም በደብዳቤ አደርሳችሁ እንጂ እ ንጂ በአንደበቴ አስደምጣችሁ ዘንድ አልሆነም፡፡

ያም ሆኖ ግን ፤ በዚህ ወቅት ምሽት ከእናንተ ጋር በሰፊ አዳራሽ ውስጥ ለመታደም፣ የሕይወት ታሪኬንና ሥራዎቼን የሚዳስሰውን መጽሐፍ አብሪያችሁ በማስመረቅ ደስታዬን ለመጋራት ባለመታደሌ ቅር ቢለኝም፣ ቂሊንጦ ማረሚያ ቤት ቅጽር ግቢ ውስጥ በሚገኝ ጠባብ ክፍል ውስጥ ይህንን ደስታዬን የሚጋሩ የዕስር ቤት ጓዶችን በዙሪያዬ ባለማጣቴ መጽናናቴ አልቀረም፡፡

ዓመታትን የፈጀው ይህ መጽሐፍ በይፋ የሚመረቅባትን ይህቺን ልዩ ምሽት፣ በዕስር ቤት ሳይሆን በመካከላችሁ ተገኝቼ በፍንደቃ እንደማሳልፋት ተስፋ አድርጌ ነበር፡፡

በ”አክሰስ ሪልስቴት” ጉዳይ በማዕከላዊ ዕስር ቤት ለ128 ቀናት አስሮ ሲያሰቃየኝ ቆይቶ፣ ድንገት እንዳሰረ ድንገት ፈትቶ የለቀቀኝ መንግስት፣ ብዙም ሳይቆይ ነበር ከኢምፔሪያል ሆቴል ሽያጭ ጋር በተያያዘ፤ ባልሠራሁት ወንጀል እንደልማዱ ከስምንት ወራት በፊት መልሶ ያሰረኝ፡፡ ሊያስጠይቀኝ የሚችል ወንጀል እንዳልሰራሁ አውቅ ነበርና፣ ሕግ እስከተከበረ ድረስ ነጻ እንደምወጣ እርግጠኛ ሆኜ ነበር ወደ ቂሊንጦ የገባሁት፡፡ የተፋጠነ ፍትህ አገኛለሁ ብዬም ተስፋ አድርጌ ነበር፡፡ ጉዳዩ ቢበዛ በ3 ወራት ጊዜ ውስጥ እልባት ያገኛል ብዬ ጠብቄ ነበር፡፡ የጠበቅኩት ግን አልሆነም፡፡ ከዛሬ ነገ ፍትህ አገኛለሁ በሚል ተስፋ ጊዜያትን ብገፋም፣ ይህ ነው የሚባል ፍትህ ሳላገኝ ይሄው በዕስር እየማቀቅኩ 8 ወራትን አሳለፍኩ፡፡ እነሆ ዛሬም ታሪኬን የያዘው መጽሐፍ እኔ ባለታሪኩ በሌለሁበት እየተመረቀ ነው፡፡

መንግስት የዋስትና መብቴን ነፍጎ ወህኒ ከወረወረኝ በኋላ፣ በቂሊንጦ ጠባብ ክፍል ውስጥ ባሳለፍኳቸው ስምንት ወራት ውስጥ ብዙ ነገሮች ተበላሽተዋል፡፡ አገርን ሊለውጡና ተጨባጭ ለውጥ ሊያመጡ ከሚችሉት ጅምር ፕሮጀክቶቼ መካከል አብዛኞቹ፣ ዕስር ቤት በመግባቴ ሳቢያ ተሰናክለው ቀርተዋል፡፡ ከአፍሪካው ቁጥር አንድ የኢንቨስትመንት ባንክ ጋር አጋርነት በመፍጠር ላቋቁመው ያቀድኩት አዲስ የኢንቨስትመንት ባንክ ከንቱ ሆኖ ቀርቷል፡፡ ትልቅ ህልም ያነገበን ሰው ሰበብ ፈልጎ ማሰር የማይደክመው መንግስት፣ እኔን ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም በሊደርሺፕ እና ማኔጅመንት መስክ የካበተ ልምድ ካለው አንድ የውጭ ኩባንያ ጋር በመቀናጀት በመስኩ ደረጃውን የጠበቀ ስልጠና የሚሰጥ፣ አገራዊ ፋይዳው የጎላ ኩባንያ ለማቋቋም የወጠንኩትን ትልቅ ህልምን ጭምር ነው እስር ቤት ያጎረው፡፡

ከፍተኛ ጥረት በማደረግ ከዓለም አቀፉ ኩባንያ “አሊባባ” ጋር በኢትዮጵያ ተግባራዊ ላደርገው ያቀድኩት ትልቅ ፕሮጀክትም ቢሆን፣ በመታሰሬ ሳቢያ የተወሰነ ቢጓተትም አበቃለት የሚባል ጉዳይ አይደለም፡፡ ኩባንያው አሁንም ድረስ እኔ ከዕስር ተፈትቼ ፕሮጀክቱን በጋራ ተግባራዊ ማድረግ የምንችልበትን ቀን በትዕግስት እየተጠባበቀ ይገኛል፡፡ በነገራችን ላይ የአሊባባን ፕሮጀክት ባሰብኩ ቁጥር ሁሌም ግርም የሚለኝ አንድ ነገር አለ፡፡

የአገሬ መንግስት፣ “አገርና ህዝብን የሚጎዳና ዋስትና የማያሰጥ ከፍተኛ ወንጀል ፈጽሟል፤ የዋስትና መብቱ ተከብሮለት ከእስር ቤት ቢወጣ ወንጀሉን ለመሸፋፈን ይሞክራል፤ ከህግ ተጠያቂነት ለማምለጥ አገር ጥሎ ይጠፋል፤ ስለማላምነው ዋስትና አልሰጠውም” ያለኝን እኔን፣ ዓለም አቀፍ ዝናን ያተረፈው የባዕድ አገሩ ኩባንያ አሊባባ ግን፣ “ለአገር ለወገን የሚጠቅም ፕሮጀክት አብሮኝ ሊተገብር የተነሳ፣ የምተማመንበትም የማምነውም ሰው ነውና ከእሱ ጋር ያለኝን አጋርነት አላፈርስም” በሚል ጽኑ አቋም የምፈታበትን ዕለት በትዕግስት ለመጠባበቅ መፍቀዱን ሳስብ ሁሌም ግርም ይለኛል፡፡

የጀመርኳቸውን ሰፋፊ ፕሮጀክቶች ሜዳ ላይ በትኜ ቂሊንጦ እንድወርድ ቢወሰንብኝም፣ እኔ ግን ዕስር ቤት ሆኜም ስራ አልፈታሁም፡፡ በዚህች ምሽት በምትመርቁት መጽሐፍ ውስጥ እንደተጠቀሰው፣ መንግስት አካሌን እንጂ አእምሮዬን ማሰር የሚችልበት አቅሙም ችሎታውም የለውም፡፡ የእኔ ቢሮ ያለው አእምሮዬ ውስጥ ነው፡፡ እሱን ይዤ ነው ቂሊንጦ የወረድኩት፣ ቢሮዬን ይዤ ነው የታሰርኩት፡፡ በግንብ አጥርና በፍርግርግ ብረት ብታጠርም፣ ከቅዳሜና እሁድ በስተቀር ሳምንቱን ሙሉ ሥራ ላይ ነኝ፡፡ አዳዲስ የቢዝነስና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ሐሳቦችን አፈልቃለሁ፡፡ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ የተለያዩ ጽሑፎችን አዘጋጃለሁ፡፡ ከአዲስ አበባ ግርግር ወጣ ብዬ በዕስር ባሳለፍኳቸው ያለፉት ስምንት ወራት ኹለት መጽሐፍትን ጽፌ ያጠናቀቅኩ ሲሆን፣ የሌሎች 3 መጽሐፍትን ንድፍ በማጠናቀቅ ከሰሞኑ ጽሑፍ ለመጀመር እየተዘጋጀሁ ነው፡፡

የምፈልገውን ያህል ባይሆንም አነብባለሁ፡፡ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ጋዜጦችና መጽሔቶች እንዲገቡልኝ ለፍርድ ቤት አቤቱታዬን አቅርቤ ነበር፡፡ ፍርድ ቤት ተገቢነት ያላቸው የህትመት ውጤቶች እንዲገቡልኝ ለማረሚያ ቤቱ አስተዳደር ትዕዛዝ አስተላልፎ ነበር፡፡ ያም ሆኖ ግን ወዳጅ ዘመዶቼ በብዛት ከሚልኩልኝ በርካታ መጽሐፎች፣ መጽሔቶች፣ ጥናቶችና ሪፖርቶች መካከል የማረሚያ ቤት ፖሊሶችን ግምገማ አልፈው ከእጄ የሚደርሱት እጅግ በጣም ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ በዕስር ቤት ቆይታዬ ከፖሊስ ግምገማ አልፈው የገቡ ከ20 በላይ መጽሐፍትን አንብቢያለሁ፡፡ ሁሌም በየሳምንቱ የማይቀርብኝና ሳላቋርጥ የማነብበው ዘ ኢኮኖሚስት መጽሔት ብቻ ነው፡፡ ከዚያ ውጭ ግን ከታሰርኩበት ዕለት አንስቶ የአገር ውስጥ መጽሔቶችና ጋዜጦችን አንብቤ፣ ሬዲዮም ሰምቼ አላውቅም፡፡

በቂሊንጦ ማረሚያ ቤት ዞን 4 ውስጥ በሚገኘውና 80 ስኩየር ሜትር ያህል ስፋት ባለው ክፍል ውስጥ እኔን ጨምሮ 16 እስረኞች እንኖራለን፡፡ የኢንሳው ቢኒያም ተወልደ፣ ከብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር በተያያዘ የታሰሩ 8 ሰዎች፣ ሰኔ 16 ቀን በመስቀል አደባባይ በተፈጸመው የቦንብ ፍንዳታ በቁጥጥር ስር የዋሉ 5 ሰዎች፣ እንዲሁም በሞተር ብስክሌት ከተፈጸመ ወንጀል ጋር በተያያዘ የታሰሩ 2 ፖሊሶች፡፡

ማንበብ፣ መጻፍና ስፖርት መስራት የዕለት ተዕለት የዕስር ቤት ህይወቴ ውስጥ የማይጓደሉ ሦስት ነገሮች ናቸው፡፡

የኔ ነገር፤ የረሳሁት አራተኛ ነገር አለ፤ ካቦነት! በዞን አራት ክፍል ውስጥ አብረውኝ የታሰሩትን 15 ሰዎች የመቆጣጠር ሥልጣን የተሰጠኝ፣ ከፍተኛ ባለስልጣን ሆኜ በካቦነት ተሹሜላችኋለሁ፤ ሹመት ያዳብር አትሉኝም? መሳቅ ነው የሚሻለው፤ እየሳቁ የሚሆነውን ሁሉ መታዘብ ነው እንግዲህ፡፡

እውነቱን ለመናገር ግን፣ በአንድ በማላውቀው ምክንያት እንደ አሮጌው ኢህአዴግ ሁሉ፣ አዲሱም ኢህአዴግ እኔን ማጥቃትና ሥራዎቼን ማሰናከልን ተልዕኮው ያደረገ ይመስለኛል፡፡ ሲሆንብኝ የኖረውና እየሆነብኝ ያለው ነገር ሁሉ በግለሰብ ላይ ከሚፈጸም ግፍና በደል ባለፈ በአገሪቱ የፖለቲካና የህግ ስርዓት ላይ ጥቁር ጥላውን የሚያሳርፍ ኢ ፍትሃዊነት ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ እርግጥ የሚደረገው ሁሉ የሚደረገው በእኔ ላይ ብቻ አለመሆኑን አውቃለሁ፡፡ አገራቸውን ሊጠቅሙና ተጨባጭ ለውጥ ሊፈጥሩ የሚችሉ ሌሎች ግለሰቦችም፣ የኢህአዴግ አባል ለመሆን ወይም ስርዓቱን ለመደገፍ ባለመፍቀዳቸው ብቻ እንደጠላት እየታዩ፣ ሲበደሉና በፍትህ እጦት ሲንገላቱ ማየት የተለመደ ክስተት ሆኗል፡፡

መንግሥት ላለፉት 20 አመታት ሰበብ እየፈለገ ያለአግባብ ሲፈጽምብኝ በቆየው መልከ ብዙ በደልና ጥቃት በቢዝነሴ፣ በመልካም ስምና ዝናዬ፣ እንዲሁም በቤተሰቤ ላይ እጅግ ከፍተኛ ጥፋትና ኪሳራ አድርሶብኛል፡፡ ይህን ልክ የለሽ ጥፋትና ኪሳራ፤ ራሱ መንግሥትም ሆነ ማንም ሰው በምንም ሊያካክስልኝ አይችልም፡፡

ደስ የሚለው ግን፣ በደል እየቆጠረ የማይቆዝም፣ ጥቃትን ፈርቶ የማይርድ ልብ መታደሌ ነው፡፡ በተመታ ቁጥር የሚጠነክር፣ በተገፋ ቁጥር የሚጸና፣ በታጠፈ ቁጥር የሚ ቃና፣ የማይበገር መንፈስ ነው የተሰጠኝ ፤ የማ ይሰበር!


ብታውቁኝም ባታውቁኝም፣ በችሎት አዳራሽ እየተገኛችሁ አጋርነታችሁን ስታሳዩኝ፣ በማህበራዊ ድረገጾች ስለእኔ ፍትህ ስትጮሁ፣ ስለእኔ በትጋት ስትጽፉና ስትዘግቡ፣ ቂሊንጦ ድረስ እየመጣችሁ ስትጎበኙኝ የከረማችሁ፤ እንዲሁም በመጽሐፉ ምርቃት ላይ የታደማችሁ፣ የተሰባሰባችሁ፣ የማውቃችሁም፣ የማላውቃችሁም በሙሉ አንድ ነገር በእርግጠኝነት ልነግራችሁ እፈልጋለሁ፤ ዕስር ቤት ሆኖ ይህን ደብዳቤ እየጻፈላችሁ የሚገኘው የአሁኑ ኤርሚያስ፣ በደልና ጥቃት ቅስሙን ሰብሮት ተስፋ የቆረጠ ሳይሆን፣ ከመቼውም ጊዜ በላይ ጠንካራ ልብ፣ ከምንጊዜውም የተሻለ ጽኑ መንፈስ የተላበሰ ኤርሚያስ ነው፡፡

በግፍ ከተወረወረበት የቂሊንጦ ቅጽር ግቢ የበለጠ ጠንክሮ ለመውጣት የተዘጋጀ፣ ከምንጊዜውም በላይ ከፍ ብሎ፣ ከመቼውም በላቀ ተስሎ አዲስ ታሪክ ለመስራት የሚያኮበኩብ አዲስ ኤርሚያስ ነው ይህን ደብዳቤ ልኮ፣ እንኳን ለዚህች ዕለት አደረሰን፣ አደረሳችሁ የሚላችሁ፡፡

**ነሐሴ 15 ቀን 2011 ዓ.ም**

**ኤርሚያስ አመልጋ (ከቂሊንጦ ማረሚያ ቤት)**

# ሳውዲ አረቢያ የፉትቦል ጦርነት ጀምራለች



ፍቅሩ ኪዳኔ

በሐብትም የምትሞላቀቀው ሳውዲ አረቢያ እስካሁን ከአሜሪካ፣ ፈረንሳይና እንግሊዝ የገዛችውን የጦር መሳሪያ እንዳይበሰብስ ድሃና ደካማ ፊልጋ የመንን አግኝታ ይሄው ሕዝቡን በቦምብ ትደበደባለች:: በሌላ በከኩል ደግሞ ኳታርን እንደ ጠላት በመቁጠር ከአካባቢው አገሮች አጣልታ ለአይድ ኤል ከቢር በዓል እንኳን ሕዝብዋ ወደ መካ ሄዶ እንዳይሰግድ ከልክላለች:: እስካሁን ብዙዎቹን የዓለምና የአውሮፓ አገሮች እግር ኳስ ሻምፒዮኖች በቴሌብቨዥን ለማስተላለፍ መብቱን የገዛው ‹‹ቢኢንስፖርት›› የተባለው የኳታር ድርጅት ነበር:: ይሄን ኩባንያ ለመቃረን ‹‹ቢአውት ኪው›› የሚባል የቴሌቪዥን ጣቢያ ፕሮግራም ማሰራጫ በሳውዲ አረቢያ ተቋቁሞ በአረብሳት ሳተለይት በመጠቀም ያላንዳች ፍቃድ በመንጠቅ የሥርቆት ሥራዋን እያራመደች ነው:: ፊፋም ሆነ የአውሮፓ እግር ኳስ ፌዴሬሽኖች ማህበር የስፓኒሽና የእንግሊዝ ፕሪሚይር ሊግ ግጥሚያዎቻው እንዳይሰረቅ አቤት ቢሉም የሚሰማቸው ስምምነት ተፈራርሟል:: የሳውዲዎች ምኞት ይህንንም ኮንትራት ለማክሸፍ ነው:: በዓለም ውስጥ የተደነገጉት ሕጎች በሙሉ ቢጣሱ ግድ የላቸውም:: የኳታር ቢኢንስፖርት የአፍሪካ ዋንጫን ውድድሮች የሚሳልፍ ዓለም አቀፍ መመሪያዎችን የሚያከብር ድርጅት ነው:: የሳውዲ አረቢያ በተንኮል የተሞላ ክስ በሼርያ ሕግ መሰረት ሳይሆን አይቀርም:: የእግር ኳስ ጨዋታ እንዲህ በመንግሥት ደረጃ የፖለቲካ መሣሪያ የሆነው አገሪቱ ውስጥ ሌላ መዝናኛ ስለሌለ ነው::

የእንግሊዝ ፕሪሚዬር ሊግ ግጥሚያዎች እንዲሁም የስፓኒሽና የጣሊያኑ ውድድሮች እንደ ሆሊውድና ቦሊውድ ፊልሞች ስለሚቆጠሩ ነው:: ሳውዲ አረቢያ 25 ቢሊዮን ዶላር ገቢ የሚያመነጭ የዓለም የክለቦች ሻምፒዮና ከፊፋ ጋር ለማዘጋጀት ሀሳብ ማቅረብዋ ይታወሳል:: ዳሩ ግን የአውሮፓ ክለቦች ውድድሩን እንደማይፈልጉ አስታውቀዋል:: የፊፋም ፕሬዚዳት ኢንፋቲኖ አፉን ዘግትዋል:: እስካሁን የሚደግፉት አፍሪካውያኖቹ ናቸው::

**...የገነቧቸው የስፖርት ስታዲየምና ስፍራዎች ተጠቃሚ በማጣት ሣር ያበቀለበት ሲበዛ አንዳንዶቹን ለሙዚቃ በዓል ዝግጅት ለማከራየት በሚደረገው ጥረት ትርፍ ሲገኝ አልተቻለም...**

አጥተዋል:: የሳውዲ አረቢያም መንግሥት ዝም ብሎ ዓለም አቀፍ ሕጎች ሲጣሱ ይመለከታል:: ለግዜው ለአውሮፓ ኮሚሽን ከማስታወቅ፣ ሌላ ዘዴ እየፈለጉ ነው::

ከዚህም አልፎ ተርፎ የኳታሩ በኢንስፖርት ኩባንያ በሳውዲ አረቢያ ያለውን ቢሮ እንዲዘጋና እስካሁን ያተረፈውን ገንዘብ እንዲመልስ በተጨማሪም ሁለት ሚሊዮን ዶላር መቀጮ እንዲከፍል ተፈርዶበታል:: በሌላ ምዕራፍ ደግሞ ኳታር እ.አ.አ በ2022 የምታዘጋጀውን የዓለም ዋንጫ እግር ኳስ ውድድርን ለመቆጣጠር ወይም ለማሰናከል እንዲመቻቸው ሳውዲዎች እየለፉ ነው:: ዓላማው የእስያን ፉትቦል ፌዴሬሽኖችን በሙሉ በመቆጣጠር ኳታርን ለብቻዋ ለማስቀረት ነው:: ሳውዲዎች በንግድ መስክ እነ ቻይና፣ ጃፓን፣ ኮሪያን በማስፈራራት ፍላጎታቸውን ለማሟላት ይችሉ ይሆናል::

ኳታርን ለማዳን ግን የሚችል የአረቦቹ ወዳጅ አሜሪካ ብቻ ነች:: ዶናልድ ትራምፕ እንቆቅልሽ መጫወቻ ያገኘ ይመስላል:: የኳታሩ በኢንስፖርት የቴሌብቨዥን ጣቢያ ከእስያ ፉትቦል ኮንፌደሬሽን የሁለት ቢሊዮን ዶላር እነርሱም ፍሉስ የሚያገኙ መስሎአቸው ነው:: የዚህም ሀሳብ ጥንስሳ ከኳታር ጋር ለመወዳደር ነው:: ሳውዲ አረቢያ የፖለቲካ ጥላቻዋን ወደ ፉትቦል ጦርነት ለመቀየር ቆርጣ ተነስታለች:: በፊፋ ኮንግረስ ላይ እ.አ.አ በ2026 የዓለም ዋንጫን የሚያዘጋጀው አገር ምርጫ የአረብ አገሮች ድምፅ የሰጡት ለእስላሙ አገር ለሞሮኮ ሳይሆን ለአሜሪካ ነው:: ሰባት የአፍሪካ አገሮችም አሜሪካንን መርጠዋል:: አሁን ሳውዲዎችን ደስ ያላቸው ነገር ቢኖር አንድም ሳንቲም ሳይከፍሉ የዓለምን እግር ኳስ ግጥሚያዎች በወንበዴ ስነ - ስርዓት እየጠለፉ የሚያስተላልፍ ድርጅት በማግኘታቸው ነው::

ይልቁንም ሴቶቻቸው ለመጀመሪያ ጊዜ መኪና መንዳት በመቻላቸውና ለብቻቸው ያለ ወንድ ፈቃድ መጓዝና መንሸርሸር ስለተፈቀደላቸው እኛም ደስ ብሎናል:: ለሰባዊ ፍጡር ርህራሄ የሌላቸው በሼሪያ ሕግ መሰረት እጅና እግር የሚቆርጡና የሚሰቅሉ ሳውዲዎች የዓለምን ፉትቦል ለማበጣበጥ ታጥቀው ተነስተዋል::

ይሄ ሁሉ ጉድ የተፈጠረው አንድ ጎልማሳ ወጣት አልጋወራሽ መሀመድ ቢን ሳልማን የተባለ ከተሾመ በኋላ ነው:: የሳውዲን ንጉሠ ነገሥት ቤተሰብ ተችቷል በማለት ነው ጀማል ኮሽጊ የተባለውን ጋዜጠኛ ያስገደለው:: የአሜሪካው ኤፍቢአይ ማስረጃ አለኝ ይላል:: ለማንኛዋም አውሮፓውያኖች ተሰባስበው በጠበቆቻቸው ኃይል የቴሌቪዥኑን ፕሮግራም ጠለፋ እናስቆማለን በማለት ሕጋዊ መንገድ እየፈለጉ ነው:: ይልቁንም የቀድሞው የፊፋ ፕሬዚዳንት ሴፕ ብላተር ሥልጣን ላይ በነበረበት ወቅት ስለ ኳታር የዓለም ዋንጫ ዝግጅት ጉዳይ ሀሳቤን አካፍዬው ነበር::

ኳታር ትንሽ አገር ስለሆነች ስድስት ስታዲዮም ባንድ ከተማ ውስጥ ከመገንባት ይልቅ ውድድሩን ከጎረቤት አገሮች ብትካፈል ጥሩ ነው የሚል ሀሳብ ነበር:: ለምሳሌ ኳታር የመክፈቻውንና ፍፃሜውን በመሀሉ አንዱ የሩብና የግማሽ ፍፃሜ ግጥሚያዎችን ካገኘች ሳውዲ አረቢያ ባህሬን ኢምሬት ኩዌት ኦማን የቀሩትን ግጥሚያዎች ሊያዘጋጁ ይችላሉ ባይ ነበርኩ:: እነኚህ አገሮች ሁሉም ስታዲዮሞችና ሆቴሎች የአየር መንገድ ስላላቸው ወጪ ከመቀነሱም በላይ በቂ ተመልካቾች ሊሰቡ እንደሚችሉ ግልፅ ነው:: እንደሰማሁት ከሆነ ኳታር ራስዋ ነች የማትፈልገው ተብያለሁ:: ያለ ሳውዲ አረቢያ በስተቀር ሁሉን ዘንድ ቢራ ይገኛል::

ያለ ቢራ የዓለም ዋንጫ ውድድር አይሳካም:: በዚህ እንቅፋት የተነሳ ሳውዲ የሚሄድ ቲፎዞ አይገኝም ይሆናል:: እነኚህን የዓረብ አገሮች በሥራ ጉዳይ ተመላልሼ ጎብኝቻለሁ:: የኳታር ዋና ከተማ ዶሃ በፎቅ ቤቶች አጊጣለች:: ከዚያ በቀር የሚያፏጭ ወፍ የለም:: ለዓለም ዋንጫ የምታስገነባውን ስታዲዮሞች አወላልቃ ለታዳጊ አገሮች አበረክታለው ብላለች:: ገንዘብ መበተን የሚወዱት ኳታሪዎች በበጋ ወራት በጣም ስለሚሞቅ ስታዲዬሞቹ ውስጥ ማቀዝቀዣ እናስገባለን ይላሉ:: በተራ የስፖርት አገልግሎቶች ከኦሎምፒክ ጨዋታ አንስቶ የዓለም ዋንጫ ውድድር ያዘጋጁ አገሮች እንደ ግሪክ፣ ደቡብ አፍሪካ ዓይነቶቹ ኪሳራ ውስጥ ገብተዋል::

የገነቧቸው የስፖርት ስታዲየምና ስፍራዎች ተጠቃሚ በማጣት ሣር ያበቀለበት ሲበዛ አንዳንዶቹን ለሙዚቃ በዓል ዝግጅት ለማከራየት በሚደረገው ጥረት ትርፍ ሊገኝ አልተቻለም:: የኳታርም ስታዲዮሞች ከእ.አ.አ 2022 የዓለም ዋንጫ ፌሽታ በኋላ ምን ዕጣ እንደሚገጥመው አላህ ያውቃል:: ያገራቱም ሕዝብ አነስተኛ ስለሆነ እስካሁን ባዘጋጁት አህጉር ወይም ዓለም አቀፍ ውድድሮች ስታዲዬሙ ባዶ እንዳይሆን ባገሪቱ ውስጥ የሚገኙትን የፓኪስታንና ባንግሌዳሽ ቀን ሠራተኞች ገንዘብ በመክፈል ሄደው እንዲያጨበጭቡ ያደርጋሉ:: ድንገት በ2022 ዓለም ዋንጫን ውድድር በነፃ ለማየት ሳይቻል አይቀርም::

# “በሰማይ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ በምድር ዛይ ራይድ አፍሪካን ይቆጣጠራሉ”

## አቶ ሐብታሙ ታደሰ /የዛይ ራይድ መሥራችና ዋና ሥራ  አስኪያጅ/

በ“ዛይ ራይድ” አፕሊኬሽን አማካይነት ወደ ሥራ ከገቡ  አራት ዓመት ሲሞላቸው ጥቂት ወራት ቀርተዋል፡፡ ተሳፋሪዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ከማድረግ ባሻገር፤ ቀደም ሲል በግምት ይሠራ የነበረውን የሂሳብ አወጣጥ፣ መንግሥት ያወጣውን ተመን ተመስርተው ወደ ኪሎ ሜትር በመቀየር እና ዋጋን ርካሽ በማድረግ አዲስ መንገድ ይዘው የመጡ ግለሰብ ናቸው፡፡ በዚህ መልክ የትራንስፖርቱን ዘርፍ ዘመናዊ ለማድረግ እየሠሩ ያሉት አቶ ሐብታሙ ታደሰን የግዮን ጋዜጠኛ ሙሉጌታ አክሊሉ አነጋግሯቿል፡፡




አቶ ሐብታሙ ታደሰ

**ግዮን፡- የዛይራይድ የታክሲ አጠቃቀም ሥራውን እንዴት እየሰራችሁት ነው?**

አቶ ሐብታሙ፡- ዛይራይድን የምንሰራው በኹለት ዓይነት መልኩ ነው፡፡ በዛይራይድ አፕልኬሽንን ወደ ስልክ በማውረድና በመመዝገብ ታክሲዎችን መጥራት የምንችልበት መንገድ አንደኛው ሲሆን፤ የጥሪ ማዕከላችን 6303 ላይ በመደወል ደንበኛው ያለበት ቦታ ድረስ ታክሲን በማዘዝ ደህንነቱ የተጠበቀ የታክሲ አገልግሎትን ማግኘት ሌላኛው የጥሪ አማራጫችን ነው፡፡

**ግዮን፡- ዛይራይድ ከአነሳሱ ጀምሮ አሁን ላይ የደረሰበትን  ለውጥ ቢነግሩን?**

አቶ ሐብታሙ፡- ዛይራይድ ሲመሰርት በእኛ ስር 17 አሽከርካሪዎች ብቻ ነበሩ፡፡ በአሁኑ ሰዓት ግን 3000 አሽከርካሪዎች ከእኛ ጋር እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ከ70 ሺህ በላይ ደንበኞችም አሉን፡፡ ቀደም ሲል አገልግሎቱን መስጠት ስንጀምር የጥሪ ማዕከል አልነበረንም፤ አሁን ትልቅና ዘመናዊ የሆነ፣ ሙሉ ታክሲዎቻችንን የምንቆጣጠርበት የጥሪ ማዕከሎች አሉን፡፡

**ግዮን፡- የንግድ ውድድሩ ከታክሲ ማኀበራት ጋር ጤናማ ነው ይላሉ?**

አቶ ሐብታሙ፡- ከታክሲ ማኀበራት ጋር እኛ ችግር የለብንም፡፡ ምክንያቱም ስማችን ሚዲያ ላይ በክፉ ሲነሳ የማይሰማው ሕግን ስለምንከተል እና ታክሲዎችን ብቻ ስለምናሰራ ነው፡፡

**ግዮን፡- የትኞቹን ታክሲዎች ነው የምታሰሩት?**

አቶ ሐብታሙ፡- ቢጫ ቅብ ያላቸውን ታክሲዎች ብቻ ሳይሆን፣ ሰማያዊ በነጭ የተቀቡ ወይም በተለምዶ “ላዳ” የምንላቸው ታክሲዎችን አቅፈን ነው ሥራችንን የምናካሂደው ፤ ምክንያቱም እነርሱን ጥለን የትም መሄድ አንችልም፡፡ የምንወስደው ኮሚሽን 10 በመቶ ብቻ ነው፡፡ ሌሎች ድርጅቶች ጋር ብትሔዱ የእኛን እጥፍ ከ10 በመቶ በላይ ነው የሚቀበሉት፡፡ እንዲሁም ታክሲን ለመመዝገብ ፍላጎት የላቸውም፡፡ ከታክሲ ማኀበራት ውጪ  ተመሳሳይ ቴክኖሎጂ ይዘው የመጡ ድርጅቶች አሉ፤ ጤናማ የሆነ ውድድር ውስጥ የገቡ እንዳሉ አሉ፡፡ በአዲስ አበባ ውስጥ በቀን 3.5 ሚሊዮን ህዝብ ይመላለሳል፡፡ እኛ ብንደመር ከ15ሺህ ሰው በላይ በቀን አናመላልስም፡፡ ስለዚህ በጣም ሰፊ ማርኬት(ገበያ) እያለ በተንኮል ማለፍ የሚፈለጉ ሰዎችን ተመልክተናል፡፡

**ግዮን፡- የዛይራይድ  አገልግሎትን እንዴት ይገልጹታል?**

አቶ ሐብታሙ፡- በዛይራይድ አንድ ሰው 6303 በመደወል የሚገባበትን የታክሲ ዓይነት፣ የአሽከርካሪውን ሥም፣ ፎቶና ታርጋ የሚያይበት፣ ደህንነቱ ተጠብቆ፣ ምንም ሥጋት ሳይኖርበት ለ24 ሰዓት 7ቱንም ቀን የሚያገለግልበት አፕልኬሽን ነው፡፡ የዋጋ ክርክር የለውም፣ ደንበኛው ዕቃውን ታክሲው ውስጥ ቢረሳ፣ ዕቃውን በቀላሉ ማግኘት ይችላል፡፡ የአሽከርካሪው ማንነት ይታወቃል፣ ለአሽከርካሪውም የተሳፋሪውን ማንነት በስልክ ቁጥሩ ይደርሰዋል፡፡ ደህንነቱ ተጠብቆ፣ ማን እንዳሳፈረው አውቆ፣ ገንዘብ ቆጥቦ ተጠቃሚ ሆኖ መኖር የሚችልበት አሠራር ነው ያለን፡፡ በዚህ አካሄድም አሽከርካሪዎቻችን እስከ 3እጥፍ ድረስ ገቢያቸውን ጨምረዋል ፤ ኑሮዋቸውንም አሻሽለዋል፡፡

**ግዮን፡- ላዳ ታክሲዎችን በጥራት ከማሳደግ አኳያ ምን አስባችኋል?**

አቶ ሐብታሙ፡- ላዳ አሽከርካሪዎች ቢጫ ታክሲዎችን ያልገዙት ስላልፈለጉ ሳይሆን አቅማቸው ስላልፈቀደና ስላልቻሉ ነው፡፡ እነርሱን ታሳቢ ያደረገ ፊያት ታክሲዎችን፣ ከታክሲ ማኀበራትና ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር ተነጋግረን ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ በማድረግ ላይ ነን፡፡ ስለዚህ የሰማያዊ በነጭ ታክሲ ባለንብረቶች 30 በመቶ ብቻ በመክፈል 20 በመቶ በባንክ ብድር የአዳዲስ ታክሲዎች ባለቤት እንዲሆኑ እያደረግንላቸው ነው፡፡ ሌላው ለሴቶች ትኩረት እየሰጠን 30 በመቶ ቅድሚያ በመክፈል 70 በመቶውን በአምስት ዓመት ብድር እንዲጠቀሙ፣ የአውሮፓ መኪኖች ባለቤት ሆነው እንዲሰሩበትና ቤተሰቦቻቸውን እንዲያስተዳድሩ የሚያደርግ መንገድም አምጥተናል፡፡

**ግዮን፡- ከኢትዮጵያ ውጭ እንቅስቃሴ እያደረጋችሁ መሆኑን ሰምተናል፤ የትኞቹ አገራት ነው ይሄንን ሥራ ለመሥራት ያሰባችሁት?**

አቶ ሐብታሙ፡- ከኢትዮ ጵያ ውጪ በቅድሚያ እየሠራን ያለነው ላይቤሪያ ነው፡፡ በላይቤሪያ ሁሉንም ነገር ጨርሰን፣ ሹፌሮች መንገድ ላይ ወጥተው “ቴስቲንግ” እየሰሩ ነው ያሉት፡፡ በቀጣይ አይቮሪኮስትና ጊኒቢሳው እየገባን ነው፡፡ እንዲሁም ዌስት አፍሪካ ኤክስፓንድ እያደረግን ነው፡፡ ስለዚህ በሰማይ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ በምድር ደግሞ ዛይራይድ አፍሪካን ይቆጣጠራል ማለት ነው፡፡

**ግዮን፡- ተወዳዳሪነትን ለማስፋት ምን ታስባላችሁ?**

አቶ ሐብታሙ፡- ሰው ምን ይፈልጋል? የሚለውን ጥያቄ አጥንቶ ምላሹን በአግባቡ መስጠትና ሲስተሙ ውስጥ መክተት ነው፡፡ አንደኛው የአገልግሎት አሰጣጡን ማስተካከል፤ ዋጋ መቀነስና የተሻለ ቴክኖሎጂን ይዞ መምጣት ነው፡፡ ስለዚህ አፕሊኬሽናችንን ኢትዮጵያዊ /ሐገርኛ/ ማድረግ ነው፡፡ ሰው የእኔ ብሎ የሚቀበለው ነገር መሆን አለበት፡፡ ያንን እየሰራን ነው፡፡ ታች ድረስ ወርደን ከማኀበረሰቡ ጋር እየሠራን ነው ያለነው፤ አሸናፊ እንደሆንንም አንጠራጠርም፡፡

**ግዮን፡- ትንሽ ስለ አፕልኬሽን አጠቃቀሙ የሚነግሩን ካለ?**

አቶ ሐብታሙ፡- ሁለት አይነት አፕልኬሽን አለ፡፡ አንደኛው አሽከርካሪው የሚመዘገብበትና የሚጭነው አፕልኬሽን አለ፡፡ ቢሮ መጥቶ ሲመዘገብ የመኪናውን ኢንሹራንስ፣ አጠቃላይ የመኪናውን ይዘት አይተን የምንመዘግበው ነው፡፡ ኹለተኛው  የአይፎን ተጠቃሚ ከሆነ App Google ውስጥ ገብቶ ማውረድ ይችላል፣ የአንድሮይድ ሥልክ ተጠቃሚ የሆኑ ደግሞ ‹‹ZAYRIDE›› ብሎ በመፈለግ(ሰርች በማድርግ) Passenger ZAYRIDE App የሚለውን በስልኩ ላይ ያወርድና ስሙን፣ የአባቱን ስም፣ የስልክ ቁጥሩን ያስገባል፣ ኢሜል እና ለዛይራይድ የሚሰጠውን ፈቃድ Password ካስገባ በኋላ አፕልኬሽኑ ውስጥ ይመዘገባል ማለት ነው፡፡ ወዲያውኑ በApp በኩል ታክሲ “ሪኩዌስት” አድርጎ የሚሄድበት ቦታ መኳዝ ይችላል ማለት ነው፡፡

**ግዮን፡- ማስተላለፍ የምትፈልጉት መል ዕክት ምንድን ነው?**

አቶ ሐብታሙ፡- ብዙ ጊዜ ጠጥቶ ማሽከርከር ይታያል፤ ሰዎች ጠጥተው ከሚያሽከረክሩት ይልቅ ደህንነቱ የተጠበቀ ታክሲን ቢጠቀሙ ሰው ላይ ጉዳትን ከማድረስ ባሻገር ራሳቸውም ከአደጋ ይድናሉ፡፡ ሌላው በዛይራይድ ሥር የሚሰሩ ቤተሰቦችን የጥሪ ማዕከላችንን (Call Center) 6303 ላይ የሚሰሩ የታክሲ አሽከርካሪዎችን እና የስልክ ጥሪ የሚያነሱትን በሙሉ በጣም ማመስገን እንፈልጋለን፡፡ ለመላው የዛይራይድ ቤተሰቦችም ሆነ ተጠቃሚዎችም  ልባዊ ምስጋናችን ይድረሳቸው፡፡

**ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡**

# ታላቁ አፍሪካዊ የስፖርት ሰው ይድነቃቸው ተሰማ



**ጴጥሮስ አሸናፊ**

የዓለም አቀፉ እግር ኳስ ማኅበር (ፊፋ) የሥራ አስፈፃሚ አባልና የረጅም ጊዜያት የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) ፕሬዚዳንት የነበሩት ክቡር አቶ ይድነቃቸው ተሰማ በሞት ከተለዩን እነሆ 32 አመት ሆነ። ጋሽ ይድነቃቸው ያረፉት በዕለተ ደብረ ታቦር (ቡሄ) ነሃሴ 13 ቀን 1979 ዓ/ም ነበር። በዘንድሮው የደብረታቦር በዓል አፅማቸው ባረፈበት በቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ፀሎተ ፍትሀተ እየተደረገላቸው ይገኛል።

ክቡር አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ከአባታቸው ከታዋቂው የሙዚቃ ሰው፤ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ መካኒክ፣ ሾፌር እና የስነ ጽሑፍ ባለሙያ ከነጋድራስ ተሰማ እሸቴ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ሙላቷ ገብረስላሴ በጅማ ከተማ በዘመን መለወጫ መስከረም 1 ቀን 1914 ዓ.ም ተወለዱ።

አባታቸው ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ፣ በልጅ እያሱ ጊዜ የቴሌግራም እና የፖስታ ሚኒስቴር ሆነው በማገልገላቸው፤ አፄ ኃይለሥላሴ ስልጣን ሲይዙ በግዞት ወደ ጅማ በላኳቸው ወቅት ነበር ይድነቃቸው እዚያው የተወለዱት።

ይድነቃቸው ተሰማ እንደጊዜው ልጆች ሁሉ በቤት ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ እና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን የተከታተሉ ሲሆን የፈረንሳይኛን ቋንቋንም በአሊያንስ፣ በምንሊክ እና በተፈሪ መኮንን ት/ቤቶች ተምረዋል።

በ1928 ዓ.ም ወደ ፈረንሳይ አገር ለመሄድ ከተመረጡት ኹለት ጎበዝ ተማሪዎች መሀከል አንዱ በመሆን ዝግጅታቸውን ያጠናቀቁ ቢሆንም፣ አገራችን በጣሊያን በመወረሯ ምክንያት ጉዞአቸው አልተሳካም። በጠላት ወረራ ዘመንም በጊዜው ለኢትዮጵያውያን የሚፈቀደውን ትምህርት በጣሊያን ት/ቤት ተከታትለዋል።

በ8 ዓመት ዕድሜያቸው የስፖርት ዓለም ተሳትፎን የጀመሩት ይድነቃቸው ተሰማ፤ በ14 ዓመታቸው ደግሞ "የአራዳ ልጆች" በመባል የሚታወቁት አቶ አየለ አትናሽ እና ጆርጅ ዱካስ የመሰረቱትን የዛሬውን ዝነኛ እና ባለታሪክ ቅዱስ ጊዮርጊስ ፣ የዛኔውን የሰፈር ቡድን ተቀላቀሉ።

ይድነቃቸው ተሰማ በ1936 ዓ.ም ከወሮ በዛብሽ ተክለማርያም ጋር ትዳር መስርተው እስከ እለተ ሞታቸው ለ43 ዓመት ያህል አብረው ኖረው 11 ልጆችን አፍርተዋል።

በዚያው አመት የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽንን ከመመስረት ባሻገር በሀገሪቱ የክለቦች ውድድር እንዲጀመርም አድርገዋል። ቀጥሎም የኢትዮጵያ ብሔራዊ እግር ኳስ ቡድንን በመመስረት ካፕቴን በመሆን ያገለገሉ ሲሆን፣ ለ15 ጊዜ ያህል ተሰልፈው ተጫውተዋል።

ሁለገብ ስፖርተኛ የነበሩት ይድነቃቸው ተሰማ በአጭር ርቀት ሩጫ፣ በቦክስ እና በብስክሌት ስፖርተኝነትም የታወቁ ነበሩ። ለክለባቸው ቅዱስ ጊዮርጊስ በአንድ የወድድር ዘመን በ47 ጨዋታዎች 43 ጎሎችን በማስቆጠር እስከ አሁንም ድረስ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ባለ ክብረ ወሰን ናቸው።

በ1940 ዓ.ም የመጀመሪያው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጸሐፊ በመሆን የተመረጡ ሲሆን በ1953 ዓ.ም የኢትዮጵያ ስፖርት ኮንፌዴሬሽን ዋና ጸሐፊ ሆነው ተመርጠዋል።

በ1953 የዓለም አቀፍ ኦሎምፒክ ኮሚቴን መስፈርቶች በሙሉ እንዲያሟላ አድርገው የኢትዮጵያ ብሔራዊ የኦሎምፒክ ኮሚቴ የመሠረቱ ሲሆን፤ የኮሚቴው ፕሬዚዳንት በመሆን ከምስረታው እስከ 1973 ዓ.ም ድረስ አገልግለዋል።

በተጨማሪም የ1952 የሮም፣ 1956 የቶኪዮ፣ እና የ1960 የሞስኮ ኦሎምፒኮች የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ቡድን መሪ ነበሩ። በዓለም አቀፍ የስፖርት ደረጃ ደግሞ ይድነቃቸው ተሰማ በተጨዋችነት፣ በቡድን መሪነት፣ የአሰልጣኝነት የኢትዮጵያን ቡድን ይዘው ከ1940 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ የአፍሪካ፣ አውሮፓ ሀገሮች የተዘዋወሩ ቢሆንም፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያን ወክለው በዓለም አቀፍ የስፖርት ጉባዔ ላይ የተካፈሉት ግን በ1949 ዓ.ም በሱዳን ካርቱም ከተማ የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን መስራች ጉባዔ ላይ ነበር።

ከዚህ ጉባዔ በኂላ በአደራጅ ኮሚቴነት፣ በምክትል ፕሬዝዳንትነት፣ እና በፕሬዝዳንትነት የአህጉሩን ኮንፌዴሬሽን ለ30 ዓመታት በታላቅ ትጋት፣ ብልህነት እና ቆራጥነት በአመራርነት አገልግለዋል። በተጨማሪ ይድነቃቸው ተሰማ በሚከተሉት አለም አቀፍ ተቋማት ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ በማገልገል ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለሀገራቸው እና ለወገኖቻቸው አኩሪ ታሪክ ጽፈዋል።

- በአፍሪካ ብሔራዊ ኦሎምፒክ ኮሚቴ በመስራችነት እና በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት፣
- በአፍሪካ የስፖርት ኮንፌዴሬሽኖች ኅብረት ውስጥ በመስራችነት እና በፕሬዝዳንትነት፣
- በአፍሪካ የብሔራዊ ኦሎምፒክ ኮሚቴዎች ማኅበር ውስጥ በመስራችና በክብር ፕሬዝዳንትነት
- በአፍሪካ የስፖርት ሚኒስትሮች ካውንስል ውስጥ በቋሚ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት
- በዓለም አቀፉ እግር ኳስ ማህበር (ፊፋ) የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት
- የዓለም አቀፉ ኦሎምፒክ ኮሚቴ አባልነት እና
- የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን ፕሬዝዳንት በመሆን ምሳሌነቱ አቻ የማይገኝለት አገልግሎት ሰጥተዋል።

